# የእግዚአብሔር ሕዝብ እረኛ ለመሆን መጠራት

በቴልማ ብራዩን

## ለተቀናጀ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች
## 200 የሚያህሉ ትምህርቶች



“እኔ መልካም እረኛ ነኝ፣
መልካም እረኛ ነፍሱን
ስለ በጎች ያኖራል”

አናሲሞስ አገልግሎት

# የእግዚአብሔር ሕዝብ
# እረኛ ለመሆን መጠራት

## ለተቀናጀ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤቶች
## 200 የሚያህሉ ትምህርቶች

በተልማ ብራዩን የተጻፈ

EVANGELISM RESOURCES

425b Epworth Avenue
Wilmore, KY 40390, USA

ተርጓሚና አሳታሚ ፡- አናሲሞስ አገልግሎት

@2014 ዓ.ም አናሲሞስ አገልግሎት መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው።

አዲስ አበባ ፣ ኢትዮጵያ

ከአሳታሚው ፍቃድ ባልተገኘበት ሁኔታ የዚህን መጽሐፍ የቱንም ክፍል መውሰድም ሆነ በየትኛውም መንገድ ማብዛትና ማሰራጨት በሕግ የተከለከለ ነው።

Onesimus Ministry
አናሲሞስ አገልግሎት
መስከረም 2014ዓ.ም
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ ቁጥር ፡- 1113491168

የአታሚው ስምና ድርጅት
ግሎሪ የህትመት አገልግሎት

**መታሰቢያነቱ**

**ለዛየር የተቀናጀ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ንቅናቄ**

**አባት ለሆነው ዊሊስ**

**በአፍሪካ ላለው አገልግሎት ፈጠራንና ደስታን በህይወታችን ላጎናጽፉ**

**ሶስቱ አስደናቂ ልጆቻችን!**

# ማውጫ

ማውጫ ........................................................................................ i

መቅድም ......................................................................................ii

መነሾ ........................................................................................iv

ክፍል አንድ

የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች .............................................................. 2

የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት............................................................. 2

የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት.............................................................. 20

ክፍል ሁለት

የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ........................................................ 35

ክፍል ሦስት

ሥነ-ስብከት ................................................................................ 71

ክፍል አራት

መንጋውን መጠበቅ ..................................................................... 84

ክፍል አምስት

የተቀደሰ አኗኗር.......................................................................... 114

ክፍል ስድስት

የአብያተክርስቲያናት ሕብረት ......................................................... 130

ዋቢ መጻሕፍት ............................................................................ 132

# መቅድም

ቤተክርስቲያን ኢየሱስ ክርስቶስ ራስና ሙላት የኾናት ህያው አካል ናት፡፡ የክርስቶስ እንደራሴ እንደመኾኗ መጠን የተሠጣትን ተልዕኮ በጥራትም በብዛትም ምንግዜም ልትከውን እንዲገባት የሚያሳስብ ወቅት ላይ እንገኛለን፡፡ ቤተክርስቲያን ተልዕኮዋን መወጣት የምትችለው እረኞች፣ መሪዎች እና አገልጋዮች በእግዚአብሔር ቃል ጤናማ አስተምህሮ እና የህይወት ምሳሌነት የእግዚአብሔርን ሕዝብ በቅጡ መመገብና ማብቃት ሲችሉ ነው፡፡

“የእግዚአብሔርን ሕዝብ እረኛ ለመሆን መጠራት” መጽሐፍ እረኞች ፣ መሪዎች ፣ አገልጋዮች እዲሁም ምዕመናን ራሳቸውን አስቀድመው እንዲያበቁ በማድረግ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሕዝብ በማብቃት ታላቁን ተልዕኮ እንድትፈጽምና እንድታስፈጽም ያስችል ዘንድ እንደ አንድ መሳሪያ ተሰናድቷል፡፡

ይህ ግሩም ወቅታዊ መጽሐፍ አንባቢያን ራሳቸውንና ሌላውን ከማብቃት አንጻር መጽሐፉ የተዘጋጀበትን ዓላማ እንዲመቱ ያደርጋቸዋል፡-

***መጽሐፍ ቅዱሳዊ*** ፡- ስድሳ ስድስቱ የብሉይና አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ፍቃድ ለሠዎች ተጽፎ የተገለጠበት መጽሐፍ አቻ የለሽ የእምነት መሰረትና የህይወት መመሪያ መሆኑን በመገንዘብ ቅዱሳት መጽሐፍቱን በሁለንተናው እንዲያነቡት፣ እንዲያጠኑት፣ አንዲታመኑት፣ እንዲታዘዙትና ለሌሎች አንዲያስተላልፉት ያግዛል፡፡

***አስተምህሮአዊ*** ፡- መሰረታዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮቶች ማለትም አስተምህሮተ እግዚአብሔር ፣ ክርስቶስ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ሰው፣ ድነት ፣ ቤተክርስቲያን ፣ መላዕክት፣ የመጨረሻው ዘመን የማሳሰሉትን በቅጡ በመረዳት ሌሎችን ማስረዳት የሚችሉ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

***ነገረ-መለኮታዊ*** ፡- የእግዚአብሔርን ህዝብ ከመመገብና ከማብቃት አንጻር ኢየሱስ ክርስቶስን (ቃሉን) ማዕከል ያደረገ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሰብከት አገልግሎት ፣ ዘላቂ የወንጌል ሥራ ባለአደራነትና መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲሁም የቅድስና ህይወት መገለጥ ወሳኝነት ነገረ-መለኮት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያስገነዝባል።

የአናሲሞስ አገልግሎት " በክፉ እስራት ያሉ ተጋላጭ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆችና ሌሎችን በወንጌል ሁለንተናቸውን በመድረስ የእግዚአብሔር መንግስት ወራሽ ሆነው የኢየሱስ ደቀመዛሙርት ጠቃሚ ዜጋ እንዲሆኑ እየሰራ ይገኛል ። በደቀመዝሙርነት፣ በአውዳዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ስብከት ዘዴ፣ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ፣ የወጣቶች ሁለንተናዊ ዕድገት ፣ ቤተክርስቲያን ተከላ እና ሚሲዮናዊነት ዙሪያም ውጤታማ ስልጠናዎችን ለተለያዩ ቤተ-ዕምነቶችና መሰል ድርጅቶች ሰጥቷል። ይህ መጽሐፍ የእግዚአብሔርን ህዝብ እረኛ ለመሆን የተጠራ መሪ፣ መጋቢ ፣ አገልጋይ እና ምዕመናን ሁሉ ከቤተክርስቲያን ተከላ ጀምሮ አካሉን በማብቃት የእግዚአብሔርን መንግስት ስራ በጥራትና በብዛት ከመቼውም ጊዜ በላይ ማስቀጠል ያስችል ዘንድ አይነተኛ መሳሪያ ሆኖ ተበርክቷል። የክርስቶስ ኢየሱስ ቤተክርስቲያናት መጽሐፉን ለማስተማሪያነት ጭምር እንዲጠቀሙበት እያበረታታን ስለሚያተርፉበት አስደናቂ ፍሬ ሁሉ ጌታን እንባርካለን።

መጽሐፉ በዚህ መልክ እንዲዘጋጅ የጽሑፍ ስራውን ወ/ሮ እመቤት ዳርጌ፣ ትርጉም አቶ ዳምጠው ከበደ እንዲሁም አጠቃላይ የአርትኦት አበርክቶ አቶ ተካ አምባቸው (ወ/ዊ) ከፍ ያለ ምስጋናችንን አቀርባለሁ። የትርጉም ስራው እንዲታተም በመፍቀድም የገንዘብ ድጋፍ በማድረግም ለተጉ ኢንቫጀሊዝም ሪሶርስ፤ የመጨረሻ ጽሑፍ ንባብ ስራ ለሰሩ እናት የትርጉም ስራ ብሎም ለግሎሪ ማተሚያ ባለቤት አቶ ኪሩቤል አለሙ፣ ለመላው አናሲሞስ ሰራተኞች፣ የቦርድ አባላት ፣ አጋር ቤተዕምነቶች እና ድርጅቶች ሁሉ የላቀ ምስጋና እነሆ!

***ዶ/ር ነጋ መዓዛ***

**የአናሲሞስ አገልግሎት መስራች መሪ**

# መነሻ

ይህ መጽሐፍ ለተለዩ ሰዎች፣ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ለሆኑት፣ በከተማና ገጠር መዳን ለሚያስፈልጋቸው፣ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ለሚሰብኩ ብሎም የኢየሱስ ክርስቶስን ተልዕኮ ለማገልገል ለተጠሩ ቡድኖች የተዘጋጀ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለለየህ አገልግሎት ለመዘጋጀት፣ ራስህንም ለመመገብ እንዲቻልህ ስምንት ሣምንታት ለጸሎት፣ ለጥናትና ለአገልግሎ ለይተህ መጠቀም አለብህ፡፡

በዚህ መጽሐፍ አርባ ክፍለ ጊዚያትን ለመማር በቀን የአምስት ሰዓት ጥናት ዝግጅት የሚጠይቁ ሁለት መቶ /200/ ትምህርቶች ይገኛሉ፡-

- *2፡00–2፡30*፡- የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት
- *2፡30–3፡40*፡- አስተምህሮ
- *3፡40–4፡30*፡- ሥነ-ስብከት
- *4፡30–4፡50*፡- ተልዕኮ
- *4፡50–5፡40*፡- መንጋውን መጠበቅ
- ***5፡40-6፡30፡- የተቀደሰ*** አኗኗር፣ የአብያተ ክርስቲያናት ግንኙነትና ሕብረት

ከሰዓትና ማምሻ አካባቢ ከጥናቶች የተነሣ በመነቃቃት የጥናቱን ሃሳብ በመወያየት ጠቃሚ የሚሆኑ ሐሳቦችን በመያዝ ወደ ተግባር ለመቀየር በትምህርት ቤት አካባቢ ሰዎችን የማጥመድ ሥራ መተግበር ይኖርብሃል፡፡ ይህ የተግባር ሥራ ከዕለታዊ ተግባራት ሁሉ የተሻለ ይሆናል፡፡ አንዳንድ ግብዓቶችን ለመስጠት ያህል፡- ከትምህርቶች መካከል የተወሰኑት ረዥም በመሆናቸው በአንድ ሰዓት ጊዜ ውስጥ አጥንቶ መጨረስ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል፤ የትምህርት ሐሳቡ በተመደበለት ቀን ፈታኝ በመሆኑ እያንዳንዱን ጠቃሚ ቀን መከታተል ቀላል ጠቃሚ ላይሆን ይችላል፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ያላለቀ ትምህርት ቢኖር ወደ ሚቀጥለው ቀን መሻገር ስለሌለበት በሰዓቱ መገባደድ ይኖርበታል፡፡

አርባ የጥናት ቀናት የእግዚአብሔርን ውድ ቃል ያጠናህባቸው፣ ለታማኝ አገልግሎት ራስህን ያዘጋጀህበት በመሆኑ በሕይወትህ ድንቅ የምትላቸው ቀናት ይሆኑልሃል፡፡ ከተመረቅህ በኋላ የተማርከውን ወደ ተግባር እንድትቀይረው፣ በአገልግሎት እንድትጠቀምበት፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንድትመራበት፣

# የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች

## መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ ብለን የምንጠራቸው ስልሳ ስድስቱ መጽሐፍት በስምንት ሳምንታት ውስጥ መልዕክታቸውንም ሆነ የያዙት ዋና ሐሳብ ለመረዳት ጊዜው ያጥራል፤ ሆኖም በዚህ መጽሐፍ አጭርና ግልጽ በሆነ መንገድ ስለቀረበ ለመተግበር አያዳግትም፡፡ ውጤታማ ጥናት ልማድ ማድረግን ይጠይቃል፡፡ ቃሉ "የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ" /2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15/ እንደሚል ቃሉን በጥልቀትና በትጋት ማጥናት ያሻል፡፡ ከቅዱስ ቃሉ ጋር በተጣበቅህ ቁጥር በጣም እየወደድከው ትሄዳለህ፣ ከፀሐፊው ጋርም እንዲሁ! ትልቁንም በረከት በሕይወትህና አገልግሎትህ ያጎናጽፋል፡፡

ጸሎቴም "የተወደድክ የሰማይ አባታችን ሆይ ይህንን አንባቢ ብርታት፣ ደስታና እርካታ በመስጠት በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት ስለ ተፃፈው የዘላለም እውነት ጥማትን በመፍጠር ባርከው" የሚል ነው፡፡

ይህን ማስታወሻ ለመጻፍ ሶስት ጠቃሚ መጽሐፍትን ተጠቅሜያለሁ፡- What the Bible Is All Abaout, by Henrietta C. Mears እና Briefing the Bible, by John Balchin ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውጭ የሚገኙ ሐሳቦች ለሁለተኛ ድግሪ በምዘጋጅበት ወቅት የተካተቱ ናቸው፡፡

# ክፍል አንድ
# የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች
# የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት

## የትምህርት 1:- መግቢያ

መጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎ ለሰዎች የተገለጠ የእግዚአብሔር ፈቃድ /የእግዚአብሔር ፈቃድ ለሠዎች ተጽፎ የተገለጠበት/ መጽሐፍ ነው፡፡ ዋና ማዕከላዊ መልዕክቱ መዳን በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል የሚል ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ 66 /ስልሳ ስድስት መጽሐፍቶች አሉት፡፡ በ1600 ዓመታት ውስጥ 40 /አርባ/ በሚሆኑ የእግዚአብሔር መንፈስ የመራቸው ፀሐፊያን ጽፈውታል፡፡ ብሉይ ኪዳን በአመዛኙ የተፃፈው በእብራይስጥ፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ በግሪክ ቋንቋ ተጽፏል፡፡ ፀሐፊዎቹ ነገሥታት፣ አለቆች፣ ገጣሚያን፣ ፈላስፋዎች፣ ነቢያት እና አገር መሪዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህም መካካል አንዳንዶቹ እውቀት ያላቸውና የተማሩ፣ ሌሎች ደግሞ ያልተማሩ ተራ አሣ አጥማጆች ነበሩ፡፡ በዚህ ወር የትምህርት ቤት ቆይታ የምናጠናው 39 /ሰላሳ ሰጠኝ/ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ነው፡፡ እነርሱም፡-

- 5/አምስት/ መጽሐፍት፡- ሕግ
- 12 /አስራ ሁለት/ መጻሕፍት፡- ታሪክ
- 5 /አምስት/ መጻሕፍት፡- ግጥም
- 17/አስራ ሰባት/ መጻሕፍት፡- ትንቢት /5 ዋና እና 12 አነስተኛ/

ለሰው ዘር የተዘጋጀ ትልቁ የእምነት መረጃ መሳሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ስለሆነ መነበብን፣ መጠናትን፣ መታመንን ይፈልጋል፤ መታዘዝንም እንዲሁ!

## ትምህርት 2፡- ዘፍጥረት

የመጀመሪያዎቹ አምስት መጽሐፍት የተፃፉት በሙሴ አማካይነት ነው፤ ፔንታቱክ ተብለውም ይጠራሉ፡፡ ዘፍጥረት የሚለው ቃል መጀመሪያ መወለድ የሚል ትርጓሜ አለው፤ ዘፍጥረት የነገሮች

መጀመሪያን የያዘ መጽሐፍ ነው፡- የአለም መጀመሪያ /1፡1-5/፣ የሰው ዘር /1፡26-27/፣ የኃጢአት መጀመሪያ በዓለም /3፡1-7/፣ የመዋጀት ቃል ኪዳን /3፡8–24/፣የቤተሰብ ሕይወት /4፡1–15/፣ የሰው ስልጣኔ/4፡16-9፡29/፣ የተለያየ የዘር ሐረግ /10-11/፣ የእብራውያን ወገን /12-50/፡፡

ዘፍጥረት የውድቀት ታሪክ የያዘ ነው፡፡ በእግዚአብሔር ይጀምራል፣ በሰው ሞት ይጨርሳል፡፡ መጽሐፉን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በዝርዝር ማየት ይቻላል፡-

II. የኃጢአት ወደ አለም መግባት /ምዕራፍ 1–11/

- ፍጥረት /ምዕ. 1- 2/
- ውድቀት /ምዕ. 3- 4/
- የጥፋት ውሃ /ምዕ. 5-9/
- የባቢሎን ግንብና ቋንቋ መደበላለቅ /ምዕ. 10- 11/

III. የመሲሁ መምጣት /የአዳኝ / መምጣት ዝግጅት /ምዕራፍ 12-50/

- የእምነት አባት አብርሃም / ምዕ. 12–23/
- የተወደደ ልጅ ይስሐቅ /ምዕ.9-24–26/
- በእግዚአብሔር የተወደደ ያዕቆብ /ምዕ. 27–36/
- በወንድሞቹ የተሸጠ መከራን በግሉ የተቀበለና ለእግዚአብሔር ታማኝ የሆነ ዮሴፍ /ምዕ 37–50/

## ትምህርት 3 ፡- ዘፀአት

ዘፀአት ማለት መውጣት ማለት ነው፡፡ ወደ ግብጽ የወረዱ የእስራኤል ልጆች 70 /ሰባ/ ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ የግብጽን ምድር ከመልቀቃቸው በፊት ወደ ሶስት ሚሊዮን ህዝብነት አድገው ነበር፡፡ ዘፍጥረት የሰውን ውድቀት ይናገራል፤ ዘፀአት ደግሞ የሉአላዊውን እግዚአብሔር የማዋጀት ሥራ ያሳያል፡፡ በጨለማና በትካዜ ይጀምራል፣ ነገር ግን በክብር ይጨርሳል፡፡ ዘፀአት ምዕራፍ 12 /አስራ ሁለት/ የፋሲካን አንጊ ታሪክ ያሳያል፤ የእያንዳንዳችን ድነት

በእምነት በክርስቶስ ደም በኩል እንደሚሆን በግልጽ የተገለጠበት ክፍል ነው፡፡

ቅደም ተከተሉ ከዚህ በታች ያለውን ይመስላል፡-

1. እግዚአብሔር ሙሴን ነፃ አውጭ አድርጎ ማዘጋጀት /ምዕራፍ.1–11/

2. ነፃ ማውጣት /በደመና በሀይሉ/ /ምዕ. 12-14/

ወደ ሲና ተራራ መጓዝና መንፈሳዊ ትምህርት /ምዕ.14–15/

3. የሕግ መስጠት /የእግዚአብሔር ምህረትና የሰው አመጽ /ምዕ. 19–24/

4. የቤተ መቅደስ ንድፈ አሳብና መገንባት፡- እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል እንዳለ ማረጋገጥ /ም.25-40/

## ትምህርት 4፡- ዘኅልቁ፣ ዘሌዋውያን፣ ዘዳግም

## ዘኍልቁ

እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት በመንፈሳዊ ስልጠና እንደረዳቸው በስእላዊ መንገድ የሚያሳይ መጽሐፍ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሥዕላዊ መግለጫ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ የሚያተኩር፣ የመሲሁን መጽሐፍ ወይም መስዋዕትነት በማቅረብ ነጻ መውጣትን ያመላክታል፡፡ አምስት አይነት መስዋዕቶች ተካተውበታል፡- የሚቃጠል፣ የምግብ፣ የሠላም፣ የኃጢአትና በዓላት መስዋእቶች ይባላሉ ፡፡ ስምንት በዓላት አሉ፤ አንርሱም፡- የሰንበት፣ የፋሲካ፣ የጴንጤቆስጤ፣ የመለከት፣ የመከራ፣ የቤተ መቅደስ፣ የሰንበት ዓመት እና መንፈሳዊ ጉዞ! መስዋዕቶቹ ያዳናቸውን ደም የሚያሳስቡ፣ በዓላቶቹ ደግሞ በበረሐ የበሉትን መና ያመለክታል፡፡

## ዘሌዋዊያን

ከሲና ተራራ እስከ ተስፋይቱ ምድር ከነዓን ጥግ ድረስ በበረሐ የተጓዙበትን መንከራተት የሚያሳይ መጽሐፍ ስለሆነ፣ አንዳንዴ የማጉረምረም መጽሐፍ ተብሎ ይጠራል፡፡ ዋና ሐሳቡ በመታረም ላይ ያነጣጠረ ነው፤ በአማኞች አኗኗር ላይ ያተኩራል፡-

ምዕራፍ 1-10፡- የመለከት ሕግ መሰጠት

ምዕ. 11-20፡- የእስራኤል እንደ ሕዝብ መወደቅ

ምዕ. 21–36፡- ወደ እግዚአብሔር የተመለሱትን መመዝገብና በምድረ በዳ የነበረው የመጨረሻው ድል

በመጽሐፉ ውስጥ ወሳኝ የሆኑ ሰዎች ሙሴ፣ አሮን፣ ማሪያም፣ ኢያሱና ካሌብ ናቸው፡፡

## ዘዳግም

ዘዳግም የማስታወስ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህም ሙሴ የመጨረሻውን ሰንበት ለእስራኤል ሕዝብ ያስተላለፈበት ንግግርና መዝሙር የያዘ መጽሐፍ ነው፡፡ መጽሐፉ በመታዘዝ የሚገኝ በረከት፤ አለመታዘዝ ደግሞ የሚያስከትለው መርገም ምን እንደሆነ ያሳያል፡፡ መጽሐፉ ለሙሴ ሰላሳ ቀን ገደማ የተለቀሰበትን ጨምሮ የሁለት ወር ቆይታን ያሳያል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከዘዳግም መጽሐፍ ብዙ ጊዜ ጠቅሶ ተናግሯል፤ ለሰይጣን መልስ ሲሰጥም የተጠቀሰው በዚሁ መጽሐፍ ነው፡፡ ዘዳግም የሰማይን ሕይወት እንድንቀምስ ያደርጋል፡፡

*ማጠቃለያ፡- በዘፍጥረት የሰው ክፋት ያሳያል፡፡ ዘፀአት የሰው መዋጀትን፣ ዘኀልቁ የሰውን አምልኮ፣ በዘሌዋውያን የሰውን አገልግሎትና በዘዳግም ሰው መታዘዝን ሲማር አይተናል፡፡*

# ትምህርት 5 ፡- ኢያሱ ፣ መሳፍንት፣ ሩት

## ኢያሱ፡-

የኢያሱ መጽሐፍ የታሪክ መጽሐፍት መክፈቻ ነው፤ መንፈሳዊ እውነታዎች፣ ማበረታቻዎችና ጥበባት የሞላበት መጽሐፍ ነው፡፡ ሙሴ ቢሞትም እንኳን ሕዝቡ ጉዞውን መቀጠል ነበረበት፤ ሙሴ የጀመረውን ኢያሱ ይጨርሳልና! መጽሐፉ በዚህ ታላቅ መሪ አማካኝነት የተሰራውን በሁለት አቅጣጫ ይስቀምጠዋል፡-

1. የተስፋን ምድር ማሸነፍ /ምዕራፍ. 1–12/
2. የተስፋን ምድር መውሰድ /ምዕ. 13–24/

## መሳፍንት

መሳፍንት የእስራኤልን ሕዝብ ጨለማ ዘመን የያዘ ነው፡፡ ሕዝቡ እግዚአብሔርን ትቷል /ምዕ. 2፡13/፣ እግዚአብሔርም ህዝቡን እንዲሁ /ምዕ. 2-23/! መሳፍንት ከታላቁ መሪ ኢያሱ ሞት በኋላ ያለውን ጊዜ በማካተት ከኢያሱ ሳኦል እስከ ነገሠበት ጊዜ ድረስ ያለውንም ጊዜ ይጠቅሳል፡፡ በእነዚያ 350 አመታት፣ በተስፋይቱ ምድር አንድም ንጉሥ ያልነገሠበት ጊዜ ነበር፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚነበበው ሐሳብ *"ሰው ሁሉ በፊቱ ደስ ያለውን ያደርግ ነበር"* የሚለው ነው፡፡ በመጽሐፉ የሰው ተደጋጋሚ ውድቀት፣ የእግዚአብሔርም ተደጋጋሚ ምህረት ተመልክቷል፡፡ በመጽሐፉ የሚገኘው ቅድመ ተከተል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡- ሰባት ክህደቶች፣ ለሰባት ሕዝቦች ሰባት ጊዜ ባሪያ መሆን እንዲሁም ሰባት ነፃ መውጣቶች!

## ሩት

የሩት መጽሐፍ ነፃ ያወጣንን፣ የዋጀንን ክርስቶስን የሚናገር ነው፡፡ መጽሐፉ ጨለማ ከሆነው የመሳፍንት ዘመን በኃላ ተስፋን የሚያሳይ፣ የተወደደውን ክርስቶስንና ቤተክርቲያንን የሚያመላክት፤ በጌዴዎንና ዮፍታሔ አገዛዝ የነበሩ ክስተቶችን የሚጠቁም ነው፡፡ ሩት የክርስቶስ የዘር ሐረግ የሆነው ዳዊት ቅድመ አያት ናት፡፡ መጽሐፉ የመሲሁን ቤተሰብ አጀማመርን ብሎም መሲሁ ሊወለድበት ያለውን ነገድ ያመላክታል፡፡ ሩት ወገኑ ከሎጥ የዘር ሃረግ፣ አርማዊ ከሆነው የመጣች ሞዓባዊት ስትሆን፣ ከአህዛብ ወገን ወደ ክርስቶስ ቤተሰብነት የሚጣራ የእግዚብሔር ፀጋ ምልክት ናት፡፡

## ትምህርት 6 ፡- 1ኛ እና 2ኛ ሳሙኤል

### 1ኛ ሳሙኤል

1ኛ ሳሙኤል ከስድስቱ የነገሥታት መጽሐፍት የመጀመሪያው ነው፡፡ ሁለት መጽሐፍት ያላቸው መጽሐፍት ሳሙኤል፣ ነገሥት እና ዜና ናቸው፡፡ በ1ኛሳሙኤል የተፃፈው የ115 አመታት ክስተት ነው፡፡ ይኸውም ከሳሙኤል መውሰድና የሳኦል የተዘበራረቀ ጊዜ አንስቶ እስከ ዳዊት ንግሥና ድረስ ያለውን ያካትታል፡፡ መጽሐፋም በሶስት ዋና ዋና የታሪክ ባለቤቶች ይከፈላል፡-

1. የእግዚአብሔር ነብይ ሳሙኤል /ምዕራፍ 1-7/
2. ለእግዚአብሔር የማይታዘዝ የወደቀው ንጉሥ ሳኦል /ምዕ.8-15/
3. የእግዚአብሔር ሰው ዳዊት /ምዕ.16-31/

### 2ኛ ሳሙኤል

2ኛ ሳሙኤል የንጉሥ ሳኦልን ውድቀት ጽፏል፡፡ 2ኛ ሳሙኤል በእግዚአብሔር የተሾመ የዳዊትን ንግስና እንዲሁም ወደ ፊት መሲህ የሚመጣበትን የዳዊት ቤት ማደራጀትን ይጨምራል፡፡ ዳዊት የእግዚአብሔር የልቡ ሰው ቢሆንም፣ ፍፁም ንፁህ ያልሆነ፣ ነገር ግን በውድቀት ጊዜ ንስሐ የሚገባ ነበር፡፡ ዳዊት በእረኝነት፣ በቤተ መንግሥት ሙዚቃ ተጫዋች፣ ወታደር፣ እውነተኛ ጓደኛ የተሰደደ መሪ፣ ንጉሥ፣ ዋና ጀኔራል፣ የተወደደ አባት፣ ገጣሚ፣ ኃጢአተኛ፣ በእርጅናው ልቡ የተሰበረ፣ ሁልጊዜ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ነበር፡፡ መጽሐፋ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡

1. የዳዊት ንግስና /ምዕራፍ. 1-10/
2. የዳዊት መከራ /ምዕ. 11-24/

## ትምህርት 7፡- 1ኛ ነገሥት፣ 2ኛ ነገሥት

እነዚህ መጽሐፍት በቀጥታ ከሳሙኤል መጽሐፍ የቀጠሉ ናቸው፡፡ መጽሐፉ የ400 ዓመታት ጊዜ ያለው የእስራኤል መንግሥት እንዴት እንዳደገ፣ እንዳሽቆለቆለ ብሎም እንደተከፋፈለ ይናገራል፡፡ የደቡብ መንግሥት ይሁዳ 20 ነገሥታትን ይዟል፡፡ የሰሜኑ መንግሥት እስራኤል ደግሞ 19 ናቸው፡፡

እስራኤልና ይሁዳ ሁለቱም ወደ ምርኮ ተወስደዋል፤ የእግዚአብሔር ድምጽ የነበሩት ኤልያስ የፍርድንና የሉአላዊነት ሰባኪ በ1ኛ ነገሥት፣ የፀጋ ትንቢት ተናጋሪ ኤልሳዕ በ2ኛ ነገሥት ላይ ይገኛሉ፡፡

በመጽሐፍቱ የሚገኙ ዋና ሐሳቦች እንደሚከተለው መረዳት ይቻላል፡-

1. የዳዊት መሞት /1ኛ ነገሥት 1-2/
2. የሰውን መንግሥትና ክብር /1ኛ ነገሥት 3-11/
3. የመግሥት መከፋፈል /1ኛ ነገሥት 12-2ኛ ነገሥት 16/
4. የእስራኤል በአሦር መማረክ /2ኛ ነገሥት 17/
5. የይሁዳ መድከምና በባቢሎን መማረክ /2 ነገሥት 18-25/

## ትምህርት 8፡-1ኛ ዜና፣ 2ኛ ዜና

መጽሐፈ ዜና በተመሣሣይ መንገድ የነገሥት መጽሐፍትን ሐሳብ አልያም ክስተት የያዘ ነው፤ ሆኖም ግን የሐሳብ ልዩነቶች አሉ፡፡ በነገሥት መጽሐፍት የሕዝቡ ታሪክ የሚወሰደው ከዙፋን ነው፤ በዜና መጽሐፍ ታሪኮቹ ከመሠዊያ ጋር ይያዛሉ፡፡ ነገሥት ቤተ መንግሥት፣ ዙፋን እና ፖለቲካ ነክ ላይ ሲያተኩር፤ ዜና በሃይማኖት ወይም መንፈሣዊ ጉዳዮች ላይ ያጠነጥናል፡፡ 2ኛ ዜና አምስት መነቃቃቶችን ይዟል፡- በአሳ /ም. 15/፣ ኢዮሳፍጥ /ም.20/ ኢዮአስ /23 እና 24/፣ ሕዝቅያስ /ም. 29-3 / እና ኢዮሲያስ /ም. 35/፡፡

**1ኛ ዜና ቅድመ ተከተል፡-**

1. የዘር ሐረግ /ም.1-9/
2. የሳኦል መንግሥት /ም. 10/
3. የዳዊት መንግሥት /ም. 11-29/

**2ኛ ዜና ቅደም ተከተል**

1. የሰለሞን መንግሥት / ም. 1-9/
2. የመንግሥት መከፋፈል እና የይሁዳ ታሪክ /ም. 10-36/

## ትምህርት 9 ዕዝራ፣ ነህምያ እና አስቴር

### ዕዝራ፣ ነህምያ

የዕዝራ እና የነህምያ መጽሐፍት የተመረጠው የእግዚአብሔር ሕዝብ ከባቢሎን ምርኮ የተመለሰበትን ታሪክ ይናገራሉ፡፡ ዕዝራ ካህን፣ ነህምያም ተራ ሰው ነበር፡፡ የመጀመሪያ መውጣት ለእሥራኤል ሕዝብ ከግብጽ በሙሴ አማካይነት የተደረገ ነበር፤ ሁለተኛው በዕዝራ አማካኝነት ከባቢሎን መመለስ! አንዳንድ አይሁዶች ከምርኮ የተመለሱ ነበሩ፤ ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ሲደርስ ከጠበቀው በተቃራኒ የከፋ ነገሮችን እግኝቷል፡፡ ይኸውም የእስራኤል ሕዝብ በምድሪቱ ካሉ አረመኔ ሰዎች ጋር የጋብቻ ትስስር ፈጥረው ነበር /9፡1-4/፤ በዚህም ዕዝራ ሐዘንተኛ ነበር /9፡1-15/፡፡ ህዝቡም ተሰብስበው ስለሠሩት ኃጢአት በአንድ ላይ ወደ ዕዝራ ቀረቡ /10፡1-44/፤ ዕዝራም ወደ ተቀደሰው የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን መራቸው፡፡ ነህምያ ከዕዝራ በኃላ 13 አመት ቆይቶ ወደ ኢየሩሳሌም ደረሰ፣ የኢየሩሳሌምን ቅጥር ለመገንባት ከፋርስ ንጉስ ሥልጣን ተቀብሎ ነበር የመጣው፡፡ እውነተኛ መቀደስ ስለነበር፣ ምንም ተቃውሞ ቢኖርም ሥራውን በ52 ቀን ጨርሷል፡፡

የሁለቱም መጽሐፍት ቅደም ተከተሎች እነሆ፡-

1. በዘሩባቤል እና ዕዝራ አማካይነት /መሪነት/ ከባቢሎን ምርኮ መመለስ /ዕዝራ 1-6/

2. በዕዝራ መሪነት ከባቢሎን ምርኮ መመለስ /ዕዝራ 1-7/

3. የቅጥሩ መገንባት /ነህምያ 1-7/

4. መነቃቃትና መታደስ /ነህምያ 8-11/

## አስቴር

በዚህ በጣም አስገራሚ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር የሚል ስም አልተጠቀሰም፤ ነገር ግን ከእያንዳንዱ ገጽ ቃላት ጀርባ ሆኖ የሚሠራ እግዚአብሔር ይገኝበታል፡፡ መጽሐፉ ስለ እግዚአብሔር አቅርቦት ይናገራል፤ እግዚአብሔር የአለም ሁሉ መሪ መሆኑን ያትታል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ክስተቶች ሁሉ በሶስት ግብዣዎች የተከፈለ ነው፡-

1. የፋርስ ንጉሥ የአርጤክስስ ግብዣ፣ የንግሥት አስጢን መወገድ እና በመርዶክዮስ ስር ያደገችውን አስቴር ንግሥት እንድትሆን ወደ ንጉሥ ፊት ማምጣት፣ ማስተዋወቅና በር መክፈት /ምዕ. 1-2/፡፡

2. አይሁድ ሁሉ እንዳይጠፉ በሐማ ከተደረገው አዋጅ የተነሣ ንጉሡን ለመጠየቅ አስቴር ያዘጋጀችው ግብዣ /ምዕ. 7-8/

3. አይሁድ ከሞት እና ከፍርሃት የዳኑበት የአዳር በዓል /ምዕ. 9/

## ትምህርት 10፡- ኢዮብ

ኢዮብ ከግጥም መጽሐፍት የመጀመሪያው ነው፡፡ መጽሐፉ ልባዊ ልምዶችን ይነግረናል፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ሁሉ የቀደመ እንደሆነም ይታሰባል፡፡ መጽሐፉም የእግዚአብሔር ሕዝብ ለምን መከራን ይቀበላል? ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል፡፡ ታሪኩ በሰማይ ያለውን ሁኔታ በማሳየት ይጀምራል፣ የኢዮብ ከብልጽግና ወደ ድህነት መውደቅ ይተርካል፣ በመቀጠልም የኢዮብና የወዳጆቹ ውይይትን /ንግግር/ ያሳያል፡-

1. ታሪኩ በሰማይ የተደረገውን ንግግር ያስቀድማል /ምዕ. 1፡1-12፣2፡1-6/
2. የኢዮብ ከብልጽግና ወደ ማዳን መውረድ /ም.1፡12-22፣2፡11-37፡24/
3. በኢዮብና በወዳጆቹ መካከል የተደረገ ከፍተኛ ውይይት /ም.2፡11-37፡24/
4. የታሪኩ ጡዘት የደረሰበት የእግዚአብሔር ንግግር /ም.38-42/

እግዚአብሔር ለኢዮብ ሰው እርሱን ሲያይ ሁልጊዜ አንድ ነገር እንደማይቀር ነገረው፡፡ የአምላክ ሰዎች መከራ እንዲቀበሉ ሲፈቅድ እራሳቸውን ከዚያም እግዚአብሔርን እንዲያዩ ነው አለማው፡፡ እግዚአብሔርም ያነሳቸዋል፡፡ እግዚአብሔር በሁሉ መከራ ውስጥ ጥበብን የተሞላ ዓላማ አለው፡፡ ወርቅ በእሣት እንደሚነጥር ነጥሮ ሊያወጣ ይፈልጋልና!

## ትምህርት 11:- መዝሙር ዳዊት

መዝሙረ ዳዊት የምስጋና የአምልኮ መጽሐፍ ነው፡፡ መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ከፍ ያደርጋል፣ ያመሰግናልም፡፡ የሰው ሁሉ ልማድ አምላካዊ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በአማኝ ሕይወት ያሉትን የደስታ፣ የሐዘን፣ የድል እና የመውደቅ ልምምዶችን እንደ ስዕል ገልጾ ያሳያል፡፡ መዝሙሮች ስለ ክርስቶስ በመጥቀስ የተሞሉ ናቸው፡፡ የክርስቶስን ሞትና መከራው በሚገባ ያብራራሉ፡፡ መጽሐፉ ከሕግ መጽሐፍት ጋር በማገናኘት የሚከተለውን ቅደም ተከተል አካቷል፡-

1. ***የዘፍጥረት ክፍል ከመዝሙር 1-41***፡- የሰው በረከት፣ የውድቀትና መልሶ ማገገም ሂደት
2. ***የዘፀአት ክፍል ከመዝሙር 42-72*** ፡- የእስራኤል መጎዳትና መዋጀት
3. ***የዘሌዋዊያን ክፍል ከመዝሙር 73-89***፡- በውድቅትና በጨለማ ጊዜ በእግዚአብሔር አደባባይ መሆን
4. ***የዘሌዋዊያን ክፍል ከመዝሙር 90-106***፡- በምድር አዳጋች ሁኔታዎችን መጠበቅ

5. ***የዘዳግም ክፍል ከመዝሙር 107-150፡-*** የእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛነትና ምስጋና

## ትምህርት12፡- ምሳሌ፣ መክብብ፣ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን

### ምሳሌ

ሰለሞን ታላቅ ንጉሥ በጥበቡና በሀብቱ ዝነኛ ነበር፡፡ 3,000 ምሳሌዎችን፣ 1,005 መዝሙሮችን ጽፏል /1ኛ ነገሥት 4፡31፣32/፡፡ ሰለሞን ፈላስፋ፣ ተመራማሪ ፣ ለአለም ተዓምር የሆነው ቤተመቅደስ መሐንዲስና ንጉሥ ነበር፡፡ ምሳሌዎች በጥበብ የተሞሉ ናቸው፤ እንደሚከተለውም መክፈል ይቻላል፡-

1. ለወጣቶች የተሰጠ ምክር /ምዕራፍ 1-10/
2. ለሁሉም ሰው የተሰጠ ምክር /ምዕ. 11-20/
3. ለነገሥታትና ለገዢዎች የተሰጠ ምክር / ምዕ.21-31/

### መክብብ

በመክብብ መጽሐፍ የሰውን ጉዳዮች መመዝገብ፣ የተፈጥሮና ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን ማጥናት፣ የሕይወት ግብና ትርጉም ምን እንደሆነ ተገልጿል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ የታዩ ክርክሮች አምላካዊ ክርክሮች ሳይሆኑ፣ እግዚአብሔር የሰዎችን ክርክር የገለጠበት ነው፡፡ ፀሐፊው ሰለሞን ነው፤ መጽሐፉ የሚጀምረው ሕብረቱ ከእግዚአብሔር ጋር በተቋረጠ ጊዜ የሕይወትን ተሞክሮና ልምዱን ወደ ኋላ ተመልሶ ይገልፃል፡፡ ሰለሞን ጠቢብ ቢሆንም፣ የራሱን የጥበብ መንገድ ያልተከተለ ሰው ነበር፡፡ በመጽሐፉ የሚገኙ ቁልፍ ቃሎች፡- ከንቱ፣ ትርጉም አልባ፣ ከፀሐይ በታች የሚሉት ናቸው፡፡ መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን የአማኞች የፍቅር መዝሙር ነው እየተባለ ሲጠራ ቆይቷል፣ አራት ዋና ዋና ትርጓሜዎች አንዳሉትም ይነገራል፡-

1. የጋብቻ ፍቅር ክብር ያስቀምጣል
2. ያህዌ ለእራኤል ያለው ፍቅር ይገልጻል
3. የቤተክርስቲያንና የክርቶስን ሥዕል ያሳያል

4. የክርስቶስና የአማኞች ህብረት ያሳያል /ዛሬ ክርስቶስን በግል መውደድ ለቤተክርስቲያን ያስፈልጋታል/።

## ትምህርት 13፡- ኢሳይያስ

ይህ መጽሐፍ ከ17 የትንቢት መጽሐፍት የመጀመሪያው ነው። ነቢያቶች በእስራኤል የጨለማ ዘመን እግዚአብሔር ያስነሳቸው ሰዎች ናቸው፤ የዘመኑ ወንጌላዊያንም ነበሩ። ጊዜውም ከ9ኛው እስከ 4ኛው ክ.ዘ.ቅ.ክ ያለውን 500 አመታትን ይዟል። እነዚህ ነቢያት ለነገሥታትና ለኃጢአተኞች ስለመውደቃቸው ያለፍርኃት ተናግሯል። የኢሳይያስ መጽሐፍ ሁለት ትኩረቶች አሉት ፡- የመጀመሪያው ክፍል ነቢያት ስለ እስራኤል ያሳዩበት ነው፤ ሁለተኛው ክፍል ክርስቶስ መከራ መቀበሉና ኃጢአታችንን መሸከሙን፣ መክበሩና ከፍ ከፍ ማለቱን ይገልጻል።

ኢያሳያስ ራሱን ችሎ ትንሹ መጽሐፍ ቅዱስ ሊሆን ይችላል። ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ 66 መጽሐፍት እንዳሉት ሁሉ፣ ኢሳይያስም 66 ምዕራፎች አሉት። ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች እንደሚከፈል ሁሉ ኢሳይያስም በሁለት ይከፈላል። የመጀመሪያው 39 ምዕራፎች፡- ከብሉይ ኪዳን 39 መጽሐፍት ጋር እኩል ናቸው፤ ሁለተኛው 27 ምዕራፎች እንደ አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት መውሰድ ይቻላል። መጽሐፉ ወንጌል በኢሳይያስ እይታ በሚል ይመደባል። መጽሐፉ ክርስቶስ ከድንግል መወለዱ፣ ባህሪያቱ፣ ሕይወቱ፣ ሞቱ ትንሣኤው፣ ሁለተኛ ተመልሶ መምጣቱ ግልጽ በሆነ መንገድቱ የታየበት ነው።

## ትምህርት 14፡- ኤርምያስ፣ ሰቆቃው ኤርምያስ

ኤርሚያስ የሚያለቅስ ነብይ ተብሎ ይጠራል፤ የተሰጠውም መልእክት የራሱን ልብ የሚሰብር፣ በሕዝቡም ተቀባይነት የሌለው መልእክት ያስተላለፈ ነብይ ነበር። ወደ ባቢሎን በምርኮ እንደሚወሰዱ በመናገሩ አስደንጋጭ ተብሎ የተጠራ ሲሆን /38፡17-23/፣ እስራኤል የቀራት የመጨረሻ እጣ ፈንታ አልፎ መስጠት ብቻ እንደሆነ ተናግሯል። የአህዛብ

ዘመን በባቢሎን እንደጀመረ በዳንኤል መጽሐፍ የታየው የወርቅ ራስ ያሳያል። ኤርምያስ የ70 አመት ባርነት በባቢሎን እንደሚቆይ የገለጸ ቢሆንም /25፡9-12/፣ ከጨለማው በኋላ ብርሃን እንዳለ ተረድቷል። ኤርምያስ ጨለማ እንደሚመጣ የተናገረ ነቢይ አልነበርም /23፡3-8፣30፣31፡33፡15-22/። ኤርምያስ ከእግዚአብሔር የተሰጠውን የተለያዩ ትምህርቶች ተጠቅሟል። መልእክቱ ከእውቅናው በላይ እንዲጠላ፣ በጠላቶቹም እስከሞት እንዲደርስ ዳርጎታል።

ሰቆቃው ኤርምያስ የፃፈው እራሱ ኤርምያስ እንደሆነ ይታሰባል። በአምስት የተለያዩ የግጥም ጽሑፎች የተዋቀረ ነው። ሁሉም ስለ ሐዘን ብቻ አያወሩም፤ ስለ ሕዝቡ ኃጢአት ደመና ጋርዶት እንደሚያለቅስ በሚያሳዩ ግጥሞች ውስጥ የእግዚአብሔር ፀሐይ በሕዝቡ ላይ እንዳልተቋረጠ ያሳያል /3፡22-27/።

## ትምህርት 15፡- ሕዝቅኤል

ሕዝቅኤል በባቢሎን ምርኮ ወቅት ነቢይ ነበር። እስራኤል ወደ ምርኮ ከተወሰደ በኋላ በአጭር ጊዜ ትመለሳላችሁ የሚለውን የሐሰት ተስፋ በማስወገድ ኢየሩሳሌም እንደምትወድም እርግጡን ተናግሯል።

የመልእክቱ ትኩረት የነቢያት መንፈሳዊነት ብሎም አምላካዊ ሰውነት ላይ ነው፣ የተናገረውም በእስራኤል የጨለማ ዘመን ላይ ነበር። ሕዝቡ መልእክቱን አልተቀበሉም ነበርና ነብዩ በሌላ ዘዴ መናገር ጀመረ /24፡24/። ሕዝቅኤል የእግዚአብሔር ክብር ተናጋሪ ነበር፤ አጠር ያለው የመጽሐፉ እይታ በእስራኤል ውድቀት ላይ አተኩሯል፡-

1. ከጦርነት በፊት /ምዕ. 1-24/፡- ሕዝቅኤል የኢየሩሳሌምን መውደቅ እርግጠኝነት አስቀድሞ ይናገር ነበር።
2. ጦርነት /ምርኮ/ /ምዕ. 25-32 /፡- ስለ ይሁዳ ጠላቶች፣ ስለ ክፋ አህዛብ መንግሥታት  መውደቅ እና መዋረድ ይተነብይ ነበር ።
3. ከምርኮ በኋላ ከጦርነቱ ምዕ 33-48፡- በመጨረሻም የይሁዳን መልሶ መመስረትና መታደስን ተናግሯል ።

## ትምህርት 16፡- ዳንኤል

ዳንኤል እግዚአብሔር ሚስጥር የገለጠለት ነቢይና ባለራዕይ ነበር። በሩቅ ሊሆን ያለውን የተናገረ፣ በራዕይ መጽሐፍ በብዛት የተጠቀሰ ነው። በአስራ ስድስት ዓመቱ አካባቢ ወደ ምርኮ ተወስዶ እስከ ዘጠና ዓመት ድረስ የኖረ ነበር። ምርኮኛ ቢሆንም በባቢሎን እስከ ጠቅላይ ሚኒስቴርነት አድጓል። ከዳንኤል አስገራሚው ነገር ሁልጊዜ ለእውነተኛ አምላኩ ታማኝ መሆኑ ነው።

የመጽሐፉ ቅድመ ተከተል፡-

1. የዳንኤል የግል ሕይወት /ምዕ. 1፡1-2፡3/
2. ማህበራዊ ሕይወት /ከአሕዛብ ጋር የነበረውን ግንኙት ያሳያል /ምዕ. 2፡4 7፡28
3. ትንቢታዊ ራዕይ /የሕዝቡን ትንቢታዊ ታሪክ ያሳያል /ምዕ. 8-12/

## ትምህርት 17፡- ሆሴዕ፣ ኢዮኤል፣ አሞፅ

### ሆሴዕ

ሆሴዕ ታናናሽ ነቢያት ከሚባሉቱ ከ12ቱ መጽሐፍት የመጀመሪያው ነው። ትንሽ የተባሉትም ይዞታቸው አነስተኛ ስለሆነ ነው። ሆሴዕ የስሙ ትርጉም ደኅንነት የሚል ነው። የሰሜኑ መንግሥት ኤርሚያስ ነው ይሉት ነበር። ሆሴዕ ተራ ሰው ሆኖ እግዚአብሔር እስራኤልን እንዴት እንደሚወዳት በግልጽ እንዲናገር /እንዲያሳይ/ በእግዚአሔር የተጠራ ነበር።

ሆሴዕ፡- ጋለሞታ ሴት እንዲያገባ ታዘዘ። ከእርሷም ሁለት ወንዶችንና አንድ ሴት ወልዷል። ሆኖም ግን ከሚስትነት ይልቅ እንደገና የግልሙትና ተግባር ፈፀመች፤ ሆሴዕም ከቤቱ አባረራት። እግዚአብሔር ግን መልሶ እንዲያገባትና እንዲወዳት አዘዘው።

መልእክቱ እስራኤል ለእግዚአብሔር ታማኝ አልነበረችም። ሆኖም እግዚአብሔር ይወዳታል፣ ወደ ምድሯም ይመልሳታል! የሚል ነው።

የመጽሐፉ ቅደም ተከተል፡-

1. ነቢዩና ታማኝ ያልሆነች ሚስት ጎሜር /ምዕራፍ. 1-3/
2. እግዚአብሔርና ታማኝ ያልሆነች እስራኤል /ምዕ.4-14/

## ኢዮኤል

ኢዮኤል የአንበጣ ወረርሽን በነበረ ዘመን ለይሁዳ ትንቢት የተናገረ ነቢይ ነው። ክስተቱን ወደፊት ሊሆን ካለው ፍርድ ጋር ያስተያየዋል። የእግዚአብሔር ቀን ብሎ አምስት ጊዜ ፍርድን በማስመልከቱ ተናግሯል። በኢዩኤል መጽሐፍ ትልቁ ተስፋ መንፈሳዊ ነፃ መውጣት ነበር። ኢዮኤል እግዚአብሔር በሥጋ ለባሽ ሁሉ ላይ መንፈሱን እንደሚያፈስ ለመናገር የታደለ ነቢይ ነበር /2፣28፡3፡18/። ይህም በጴንጤቆስጤ ተፈፅሟል/ ሐዋሪያት ሥራ 2፡16/።

## አሞፅ

አሞጽ እረኛ ነበረ፤ መልእክቱም የሚያተኩረው በሰሜኑ እስራኤል ላይ ነው። እግዚአብሔርን እንደሚፈራ ማንንም ፈርቶ አያውቅም። ስብከቱንም የጀመረው እግዚአብሔር በእስራኤል ዙሪያ ባሉት የአህዛብ መንግሥታት ላይ እንደሚፈርድ በማወጅ ነበር። በመቀጠልም እስራኤልና ይሁዳን በመቃወም ወደ መናገር

# ትምህርት 18፡- አብድዩ፣ ዮናስ እና ሚኪያስ

## አብድዩ

አብድዩ በብሉይ ኪዳን አንድ ገጽ እና 21 ቁጥሮች ያሉት አጭሩ መጽሐፍ ነው፤ ሆኖም ለዛሬ የሚጠቅም መልእክት አለው። አብድዩ ኤዶምን በመቃወም የተነገረ ትንቢት ሆኖ ሁለት ዋና ዋና መልእክቶች አሉት፡- ለትዕቢተኞች ጨለማ እንዲሁም ለቅኖች /ትሁታን/ ነፃ መውጣት እንደሚሆን የሚሉት ናቸው። ኤዶማውያን ቡኩርናውን የሸጠው የእስራኤል ጠላቶች የሆኑት የኤሳው ዘሮች ናቸው። አብድዮም እንደተናገረውም ከተማይቱ ተደምስሳለች።

አብድዮ እንደ ሌሎች ነብያት የእግዚአብሔርን ቀን እንደሚመጣ ብሎም የመሢሁ መንግሥት እንደሚመሠረት አስቀድሞ የተናገረ ነቢይ ነው።

## ዮናስ

ዮናስ ነቢይ ቢሆንም መጽሐፉ ትንቢት የያዘ አልነበረም። በዮናስ ሕይወት የተፈጠረውን ትልቅ ክስተት የሚያሳይ ነው። ይህም ለአለም ሁሉ ታሪካዊ

ክስተት የሆነውን የክርስቶስ ትንሣኤ ምልክት የያዘ ነው፡፡ በመጽሐፉ እግዚአብሔር አራት ነገሮችን ማዘጋጀቱን መረዳት ይቻላል፡- (1) ትልቅ አሣ /1፡17/፣ (2) ቅል /4፡6/፣ (3) ትል /4፡7/፣ (4) የምስራቅ ነፋስ /4፡8/ እና የራሱን ነብይ ዮናስን መንከባከብ ነበር፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ሁለት ታላላቅ ክስተቶች አሉ፡- ትልቁ አሣ ዮናስን መዋጡ እንዲሁም ታላቅና ክፉ የሆነ የነነዌ ከተማ በጥቂት ቀን ውስጥ እንደምትገለባበጥ ለአህዛብ ተልዕኮ መደረጉን! መጽሐፉ ውስጥ በሁለት ነገሮች ላይ ማተኮር አለብን፡፡ የመጀመሪያው ዮናስ በሞቱ፣ በመቀበሩና በመነሣቱ የክርስቶስ ተምሳሌት መሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛው ለእግዚአብሔር ያልታዘዘች፣ በዙሪያዋ ካሉት አህዛቦች ጋር ተደባልቃ የኖረች፣ ክርስቶስ ሲመጣ ነፃ የምትወጣ እስራኤል ተምሳሌት ነው፡፡ ከዚያም እስራኤል ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ምስክር ሆና እንደምትኖር ያሳያል፡፡

## ሚኪያስ

ሚኪያስ በኢየሩሳሌምና በእስራኤል ከተማ ላይ ፍርድ እንደሚወጣ ያውጅ ነበር፡፡ ሆኖም ሁለት የተስፋ ቃሎች እንደሚፋጠኑ ይናገራል፡፡ የተፈጥሮ ትእዛዝ ከሚኪያስ ሲወጣ በሶስት መልእክቶች "ስሙ" እያለ ይናገራል፡-

1. ምዕራፍ 1፡2፡- ሁሉንም ሕዝብ ያጠቃልላል
2. ምዕ. 3፡1፡- የእስራኤል መሪዎችን ያነሳል
3. ምዕ. 6፡1፡- በግል እስራኤል ወደ እግዚአብሔር እንድትመለስና ንስሐ እንድትገባ ያደረገው ልመና ነው፡፡

# ትምህርት 19፡- ናሆም ዕንባቆም እና ሶፎንያስ

## ናሆም

የናሆም ዋና ትምህርት ዮናስ ሲያስጠነቅቃት የነበረችው የነነዌ መውደቅ ነው፡፡ ናሆም የተፃፈው ከዮናስ መልእክትና ንስሐ 150 አመታት በኃላ ነው፡፡ ንስሐ ባለመግባቷ ከኃጢአት የተነሣ ነነዌ ተደምስሳለች /3፡1-7/፡፡ ነነዌ ጀርባቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ብዙ ሕዝቦችን ይወክላል፤ በገዛ ፍቃድ እግዚአብሔርን መተውና ጨለማን መምረጥንም ያሳያል፡፡

## እንባቆም

እንባቆም ጥያቄን ጠይቆ መልስ የተቀበለ ነቢይ ነው፡፡ ጥያቄው ኃጢአተኛ ለምን ይበለጽጋል? የሚል ነው፡፡ ባጋጠመው መከራ ሁሉ በፀሎት ወደ እግዚአብሔር የቀረበና የሚመልሰውን በትእግስት የጠበቀ ነው /2፡1/፡፡ ፀሎቱንም ከፀለየ በኋላ የእግዚአብሔር ክብር ተገለጠለት /3፡1-16/፡፡

ጻድቅ በእምነት በሕይወት ይኖራል የሚለው ቃል በለውጥ ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው /2፡4/፡፡ ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ጭምር ተጠቅሶ ይገኛል /ሮሜ1፡17፣ ገላ.3፡11 እና እብራውያን 10፡38/ ተጠቅሷል፡፡

## ሶፎንያስ

የሶፎንያስ መጽሐፍ በእግዚአብሔር ቁጣና ፍርድ የተሞላ ነው /1፡15፣ 3፡8/፡፡ በውስጡ የእግዚአብሔርን ፍቅር ይዟል /3፡17/፡፡ ሶፎንያስ የተለያዩ የጣኦት አማልክትን ይገልጻል፤ ምናልባት ከኢያሱ ጋር የተነቃቃ መንፈስ የነበረው ሊሆን ይችላል፡፡ መጽሐፉ በሐዘን ይጀምራል፣ በመዝሙር ይጨርሳል፡፡

# ትምህርት 20፡- ሐጌ፣ ዘካሪያስ፣ ሚልኪያስ

## ሚልኪያስ

ሚልኪያስ አብዛኛው የብሉይ ኪዳን ነቢያት የተነገሩት ከምርኮ በፊት ነው፡፡ ሕዝቅኤል እና ዳንኤል ሁለቱም የተነበዩት በምርኮ ውስጥ ሳሉ ነው፡፡ ሐጌ፣ ዘካሪያስና ሚልኪያስ ሶስቱም የተናገሩት ከምርኮ በኋላ ነው፡፡

የቤተመቅደሱ መልሶ መሠራትና መታደስ የሐጌ ትልቁ ምኞት ነው፡፡ ቤተመቅደሱን በመገንባት ሂደት ሲዘገዩ፣ ህዝቡን ገስጿል፡፡ በስራቸው ያበረታታም ይረዳም ነበረ፤ ሐዝቡም ተነስተው ቤተመቅደሱን መገንባት ጀመሩ /1፡12-15/፡፡ መጽሐፋ በአራት ወራት ውስጥ የተፃፈ አጭር መልእክቶችን የያዘ ነው፡፡

## ዘካሪያስ

ዘካሪያስ፡ ወጣት ነቢይ ነው፤ ከሐጌ ጋር በመሆን የእስራኤል ልጆች ቤተመቅደሱን ሲገነቡ ያበረታታል፣ ከዚህ በፊት አባቶቻቸው እግዚአብሔርን እንዳሳዘኑት እነርሱም እንዳይደግሙት ያስጠነቅቅ ነበር፡፡ በዚህም

በግድግዳው ላይ ወደፊት የሚመጣው የእስራኤል የበረከት ተስፋን የሚያመለክት ብሩህ ቀለም እንዲቀባ አድርጓል፡፡ ዘካሪያስ ከኢሳይያስ ቀጥሎ ስለ ክርስቶስ /አዳኝ/ መምጣት በብዛት የተናገረ ነቢይ ነው፡፡ የአዳኙን ውርደትና መከራ፣ ክብርና ታላቅነት አስቀድሞ የተመለከተ ነበይ ነው፡፡

## ሚልኪያስ

ሚልኪያስ በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን እንደ ድልድይ ሆኖ ይታያል፡፡ ከሚልኪያስ አንስቶ እስከ መጥምቁ ዮሐንስ የጌታን መንገድ አዘጋጁ እስከሚለው ደምፅ ድረስ 400 አመታት አስከትሏል፡፡

ብሉይ ኪዳን መርገም በሚለው ቃል ያልቃል፣ አዲስ ኪዳን ደግሞ በበረከት! ከመነቃቃት በኃላ /ነህምያ 10፡28-39/ ሕዝቡ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እየቀዘቀዘ፣ በሞራል እያሽቆለቆለ ነበር፡፡ ሚልክያስ የተሃድሶ ሰው ሆኖ በመምጣት ሕዝቡን ያበረታታና ይገስጽ ነበር፡፡ የሚጠበቀውን የክርስቶስ ዳግም መምጣት አብሳሪ የሆነውን ሚልኪያስ ማንበብ ያሻል /3፡16-4፡3/፡፡

# የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት

## ትምህርት 21፡- የወንጌላት መግቢያ

ወንጌል መልካም ዜና ማለት ነው፡፡ አራቱም ወንጌላት መልካም ነገር የሚያሰሙ ወንጌላዊያን ተብለው ይጠራሉ፡፡ ማቴዎስ፣ ማርቆስ እና ሉቃስ አንድ አይነት ጽሑፎች ናቸው፤ ምክንያቱም የዮሐንሰ ወንጌል የተለየ ሲሆን፣ ሁሉም ስለ ክርስቶስ ሕይወት ይተርካሉ፡፡ ሶስቱም ወንጌላት የኢየሱስ ክርስቶስን የገሊላ አገልግሎት በቀናት ሲተርኩ፣ ዮሐንስ የይሁዳ አገልግሎቱን ይተርካል፡፡ ሶስቱም ወንጌላት ተአምራቱን፣ ምሳሌዎቹን ብሎም ብዙ ሰዎችን እንደሚያገኝ ይናገራሉ፤ ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስን የጠለቀ ታሪክ፣ መለወጡንና ጸሎትን ይተርካል፡፡ ሶስቱም የክርስቶስን ሥራ ሲከትቡ፣ ዮሐንስ ግን ተመስጠውንና ፀሎቱን ያሳያል፡፡ ሁሉም ነቢያት የጌታን ምድራዊ ሕይወትና ሥራ ሲናገሩ፣ መልእክቶቹ ከእነርሱ ወጥተው ይቀጥላሉ፤ ወንጌላት መነሻ ናቸውና ፡፡

ወንጌላት ክርስቶስ መቼና እንዴት እንደመጣ ይናገራሉ፡፡ መልእክቶች ደግሞ ለምን እና ምን ሊሠራ እንደመጣ ይናገራሉ፡፡

## ትምህርት 22፡- ማቴዎስ

ማቴዎስ ኢየሱስን እንደ ንጉሥ ያቀርባል፤ የተፃፈውም ለአይሁድ ሆኖ ኢየሱስን የንጉሥ ዳዊት ልጅ አድርጎ ይገልጻል፡፡ የንግሥና የዘር ሐረግም ከአብርሃም ጀምሮ በምዕራፍ አንድ ላይ ተጠቅሷል፡፡ ከሌሎች ወንጌላት በላይ ከብሉይ ኪዳን የመሢሁ መምጣት ትንቢት የተፈፀመበት መጽሐፍ ነው፡፡ ማቴዎስ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲያገኘው፣ በሮም ግዛት ውስጥ ቆጳሮንየም በሚባል ቦታ ግብር ይሰበስብ ነበር /9፣9 እና 10፡3/፡፡ ሌላው ወንጌላዊ እንደተረከው፣ ማቴዎስ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ብዙ ነገሩን የተወ እንደ ነበር ማወቅ ይቻላል፤ ይህ ሰው ሁሉ ነገር ያለው እንደነበር መገመት አያጠራጥርም፡፡ ማቴዎስ እግዚአብሔር አብ የቀባው የመሢሁ ወንጌል ነው፤ ዐብይ መልዕክቱም ኢየሱስ ክርስቶስ ሙሴና ነቢያት የተናገሩለት የናዝሬቱ መሢህ እንደሆነ ማሳየት ነው፡፡

ከምስራቅ የሚጎበኙ ጠቢባን እንደጎበኙት የሚናገረው ማቴዎስ ብቻ ነው። የተራራው ስብከት፣ የመንግሥቱን መመሪያ ያስቀምጣል። የማቴዎስ ወንጌል የንጉሥ መልእክት ስለሆነ፣ መንግሥተ ሰማያት የሚል 55 ጊዜ ተጠቅሷል። ከዚህም ውስጥ ምዕራፍ 24 እና 25 በጣም የሚገልፁት የክርስቶስን ዳግም መምጣት ነው። የክርስቶስ ዕርገት በማቴዎስ አልተጻፈም ምክንያቱም ከክርስቶስ የተነሣ መጋረጃው መቀደዱን፣ የዳዊት ልጅ ወደ ንግሥና ክብር አለመምጣቱ ገና ስለሆነ ነው።

## ትምህርት 23፡- ማርቆስ

ማርቆስ ኢየሱስን እንደ አገልጋይ ያሳያል። በጽሐፋም ላይ የዘር ሐረግ ያልገለፀበት ምክንያት ዋና ትኩረቱ በዘር ሐረግ ላይ ስላልሆነ ነው።

ፀሐፊው ዮሐንስ ማርቆስ፣ የማሪያም ልጅ፣ የባርናባስ አክስት ልጅ ነው። ጳውሎስንና ባርናባስን ወደ አንጾኪያ የሸኘ፣ በመካከላቸውም ችግር እንዲፈጠር ያደረገ ነው /ሐዋሪያት ሥራ 12፡25፣13፡5/። ዮሐንስ የነበረውን ችግር መቋቋም ስላልቻለ ተለይቷቸዋል /ሐዋ. ሥራ 13፡13/፤ በመጨረሻም ለጳውሎስ ቀኝ እጅ ሆኖለት ነበር /ቆላ 41፡10፣ 11፣ 2ኛ ጢሞ 9፡11/። ጴጥሮስ ወደ ጌታ እንዲመጣ ምክንያት ሆኖለት ስለነበር ልጄ ብሎ ይጠራዋል /1ጳጥ 5፡13/። በዚህም የጴጥሮስን ተጽዕኖ በዚህ ወንጌል ውስጥ መመልከት ይቻላል። ወንጌሉ ከወንጌላት መጽሐፍት መካካል አጭር ነገር ግን በተግባርና አፈፃፀም ልዩ ትኩረት ያለው ነው።

ማርቆስ ወንጌሉን የፃፈው በሮም መሆኑ ከሮማዊያን ማስረጃ አለ። በጣም ባተሌ ስለነበሩ፣ የሚያምኑት በኃይልና በተግባር ነበር። ከቃል በላይ ለሥራ የሚያስቡ ናቸው። በመጽሐፉ ጥቂት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ተጠቅሷል፤ አራቱም ምሳሌዎች ተሰጥቷል። መግቢያው ረዥም አይደለም፤ ወዲያውኑ፣ በቀጥታ፣ በፍጥነትና በችኮላ የሚሉ ቃላት ለ40 ጊዜ ተጠቅሷል። የተፃፉት ተአምራቶች ብዛታቸው 20 ነው።

## ትምህርት 24፡- ሉቃስ

ሉቃስ ኢየሱስን እንደ ንፁህ ሰው ይተርካል። የፃፈውም ለግሪኮች ነው፣ የሚጀምረው እንደ ማቴዎስ ከአብርሃም ሳይሆን፣ ከመጀመሪያው ሠው አዳም ነው። እንደ ንፁህ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን መላእክት ሲያገለግሉት አይቷል።

ሉቃስ ሐኪምና የጳውሎስ አጋር፣ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ ጸሐፊ፣ ብቸኛው ከአህዛብ ወገን የሆነ፣ ተመራማሪ፣ የሐዋሪያት ሥራ ጸሐፊ ነው። ኢየሱስን እንከን የለሽ ሰዋዊ እንደ ሆነ ያሳያል። ይህ ለኃጢአተኛው ወንጌል ነው፡- ሰውን ለማዳን ሰው ሆኖ የመጣውን የክርስቶስን ርህራሄ ስለሚያሳይ!

ዶክተር ሉቃስ የኢየሱስ ክርስቶስን ተዓምራዊ መወለድን ሙሉ አድርጎ ያቀርባል። የእረኞችን ጉብኝት የፃፈው እሱ ብቻ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በ12 ዓመቱ በቤተመቅደስ ይተጋ እንደነበር ያሳያል፤ በመጽሐፋ ከሚገኙት ስድስቱ ተዓምራቶች አምስቱ የፈውስ ናቸው። የተቆረጠ ጆሮ መፈወሱን የሚጠቅሰው ሉቃስ ብቻ ነው /22፡51/።

## ትምህርት 25፡- ዮሐንስ

ዮሐንስ ኢየሱስን እንደ እግዚአብሔር ልጅ ያቀርባል። በወንጌሉ ውስጥ የተጠቀሱት ነገሮች ሁሉ የሚመስለውና የሚገልጠው ስለ አምላክነቱ ብቻ ነው። ጸሐፊው “የነጎድጓድ ልጅ የተባለው” ኢየሱስ ይወደው የነበረው ዮሐንስ ነው። አባቱ ሐብታም ዓሣ አጥማጅ የሆነው ዘብዴዎስ፣ እናቱ ደግሞ የተነቃቃች የኢየሱስ ተከታይ ሰሎሜ ፣ ወንድሙ ያዕቆብ ነበር።

ዮሐንስ ከሌሎች ወንጌላት በኃላ ያለውን ትውልድ ጽፏል። ኢየሱስ ሲጠራው 25 ዓመቱ ሲሆን የመጥምቁ ዮሐንስ ተከታይ ነበር። በመጨረሻም ዕድሜው በ80 እና 100 መካካል ሳለ ፍጥሞ ደሴት ተጥሎ ነበር። በዚህ ጊዜ ከእርሱ መጽሐፍት በቀር ሁሉም የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ተጽፈው ነበር።

ዮሐንስ ከሌሎች ወንጌላት የላቀ ድምጸት ያለው መጽሐፍ ነው። በዮሐንስ ወንጌል ብቻ ኢየሱስ አብን አባቴ ብሎ ይጠራዋል፤ 25 ጊዜ እውነት እውነት እላችኃለሁ እያለ በስልጣን ይናገራል።

ዮሐንስ ሲናገር ወንጌሉን የጻፈበት ምክንያት ሠዎች ጌታን ያምናሉ በማለት ነው፡፡ ለዚህም ሰባት ምስክሮችን ያቀርባል፡- 1፡34፣1፡49፣6፡69፣11፡27፣ 20፡28፣ 20፡31፣ እና 10፡36፡፡ ሰባት ተአምራቶችንም ጽፏል ፡- 2፡1-11፣ 4፡46-54፣ 5፡1-47፣ 6፡1-14፣ 6፡15-21፣9፡1-41፣ እና 11፡1-57፡፡ የክርስቶስ "እኔ" የሚለው አምላካዊ ቃል (መለኮታዊነት) የሚያሳይ ቃል 7 ጊዜ ተገልጿል፡፡

## ትምህርት 26፡- ሐዋሪያት ሥራ

ሉቃስ በወንጌል መጽሐፋ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የጀመረውን ያሳያል፡፡ በሐዋሪያት ሥራ ደግሞ በመንፈስ ቅዱስ አማካኝነት እንዴት እንደቀጠለ ያስቀምጣል፡፡ የክርስቶስ ዕርገት በሉቃስ መጽሐፍ መዝጊያ፤ በሐዋሪያት ሥራ ደግሞ መክፈቻ ነው፡፡ ሐዋሪያት ሥራ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በሐዋሪያት አማካኝነት የተደረገውን ትርክት ይገልጻል፡፡ ስሙም ከ70 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡ "ምስክርነት" የሚለው ደግሞ ከ30 ጊዜ በላይ ተገልጿል፡፡

መጽሐፉ የሚጀምረው በአይሁዶች እየሩሳሌም ነው፤ የሚያልቀው ደግሞ የአለም ሁሉ ቁንጮ በሆነችው በሮም ስብከት ነው፡፡ በአንድ ትውልድ ሐዋሪያት ወደ ሁሉም የአለም አቅጣጫ በጊዜው በታወቀው አለም ወንጌልን ሰብከዋል /ቆላ 1፡23/፡፡

በሐዋሪያት ሥራ 1 እስከ 12 ለአይሁዶች የጴጥሮስን ስብከት እናያለን፡፡ መልእክቱም "ንስሐ ግቡ" የሚል ነው፡፡ በሐዋሪያት ሥራ 13-28 የጳውሎስ ስብከት ለአህዛብ ሲሆን፣ መልእክቱም "እመኑ" የሚል ነው፡፡
የሐዋሪያት ሥራ ለወንጌል ሥርጭት ጥሩ መመሪያ ነው፤ የሚያሳየውም ወንጌል ሲሰበክ ሰዎች የመዳን እውቀት እንደሚሰጣቸው ነው፡፡ የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን ተነቃቅታ ለሕዝብ ወንጌልን የማድረስ ሥራ ሠርታለች፡፡ መመኪያቸው መንፈስ ቅዱስ ሆኖ፣ ቅንአት ነበረባቸው፡፡ የጳውሎስ ሶስቱ የወንጌል ጉዞዎች ለውጤታማ የወንጌል ተልእኮ ትልቅ ምሣሌ ነው፡፡

## ትምህርት 27፡- ሮሜ

የሮሜ መልእክት የመልእክቶች መጀመሪያ ነው። አሥራ ሶስቱ የጳውሎስ መልእክቶች ተብለው የተሰየሙት ጸሐፊያቸው ጳውሎስ ነው /ይህም እብራውያንን የካትታል፤ የእብራዊ ፀሐፊ ጳውሎስ መሆኑ ግን እርግጠኛ መሆን አይቻልም/። ጳውሎስ ከአይሁድ የተወለደ ነው። የሮሜ ዜግነቱ፣ የግሪክ እውቀቱ፣ የእብራውያን እምነቱ ለታላቅ ሥራ ብቁ እንዲሆን አድርጎታል።

ወደ ኢየሩሳሌም ለፋሲካ በአል የሚሄዱ የሮሜ ሰዎች በጴንጤ ቆስጤ ጊዜ ተቀይረው ወደ ከተማቸው በመመለስ የወንጌልን ዘር በመዝራት ቤተክርስቲያንን ተክለዋል። ከ28 አመት በኂላ ጳውሎስ ሊጐበኛቸው በኀኀ ጊዜ በ3ኛው የወንጌል ጉዞ ሶስት ወር ከቆየበት ቆሮንቶስ ይህን ደብዳቤ ጽፎላቸዋል።

የሮሜ መልእክት የሚያሳየው ኃጢአተኛውን ሰው ንፁህ ለማድረግ የእግዚአብሔርን መንገድ ያሳያል። ስለ መዳናችንም ትልቁ መረጃ ነው። የመጽሐፉ ቅደም ተከተል፡-

- ምዕራፍ 1-8፡- አስተምህሮ። የመጀመሪያ ሶስት ምዕራፎች (1፡8 እና 3፡20) በኃጢአት የተበላሸን ሰው ያሳያል። የእግዚአብሔር ቅድስና በጽድቅ መገለጡንም ይናገራል /3፡21-5፡11/። የፃድቃን መቀደስም ቀጥሎ ተመልክቷል /5፡12-8፡39/።
- ምዕራፍ 9-11፡- የእግዚአብሔር አላማ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ
- ምዕራፍ 12-16፡- የክርስትና እምነት ተግባር

## ትምህርት 28፡- 1ኛ እና 2ኛ ቆንቶስ

ሥጋዊ የሆነች ቆሮንቶስ በጳውሎስ ዘመን በሮሜ ግዛት የኃጢአት ማዕከል ነበረች። የሁሉም ግሪክ ዋና ከተማም ናት። የኃጢአት ብዛትዋ አስገራሚ፣ ግብረ ገብነቷም የተበላሸ ከቁጥጥርም ውጪ ነበር። በዚህ በተበላሸው ሁኔታ ውስጥ ጳውሎስ ወንጌልን ሰብኳል፤ ቤተክርስቲያንንም መስርቷል፣ ሁለት መልእክቶችንም ፅፏል።

የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ደብዳቤ በውክልና ልካ ስለነበር /7፡1፣16፡17/፣ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ መልእክቱ ስለ ቤተክርስቲያኒቱ ሁኔታ መልስ ይሰጣል። ሥጋዊነት ወደ ቤተክስቲያን ገብቶ ነበር፣ መከፋፈልም እንዲሁ! ቆሮንቶሳውያን አማኞች ወንድሞቻቸውን ወደ ሕግ ይወስዳሉ፣ የአመጋገብ ስርአታቸውም ሌሎችን የማያከብር ነበር። ሴቶቻቸው ልከኞች አይደደሉም፤ የቤተክርስቲያን መሪዎች በጋብቻና በመንፈሳዊ ስጦታዎች ዙሪያ ይከራከሩ ነበር። በምዕራፍ 15 ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤና የአማኞች አካል ከሞት እንደሚነሣ ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል።

ጳውሎስ 2ኛውን የቆሮንቶስ መልእክት ሲፅፍ፣ የመጀመሪያውን ደብዳቤ እንደተቀበሉ ሰምቶ ደስታውን ይገልፃል፤ ስለ ሐዋሪያቱም ይነግራቸዋል። በመልእክቱም ከሌላው ነገር ይልቅ ስለ ራሱ ጉዳይ ያተኩር ነበር። መልእክቱ የሚጀምረው “አፅናኑ” (1፡3) በሚል ሲሆን፣ የሚዘጋውም እንዲሁ “አፅናኑ” 13፡11 በሚል ሐሳብ ነው።

## ትምህርት 29፡- ገላቲያ

ጳውሎስ በ2ኛው የወንጌል ጉዞ በገላቲያ ገጠራማ አካባቢ ቤተክርስቲያን መስርቶ ነበር። የሕግ አዋቂዎች ከጳውሎስ በኋላ ገብተው መዳን በሥራ ነው እያሉ ያስተምሩ ነበር። የሐሰት አስተማሪዎች ሁሉንም የብሉይ ኪዳን ስርአት መጠበቅ አለባቸው እያሉ ሕዝቡን ያፈዙ ነበር። ጳውሎስ ግን የሐሰተኞች ትምህርት ከንቱ እንደሆነ ምንም ሥራ ወደ ክርስቶስ ሊያደርስ እንደማይችል እንዲያውቁ ይፈልጋል። መዳንም በክርስቶስ በማመን ብቻ እንደሚመጣ ይገልፅላቸዋል። ጳውሎስ የሐሰት አስተማሪዎች ሕዝቡን ለመማረክ እንደቀረቡ ባወቀ ጊዜ ደብዳቤውን በቶሎ ለመፃፍ ተገደደ /6፡11/።

ይህ መልእክት የአማኞች ነፃ የመሆን አዋጅ ነው። ይህም ፀጋንና ሕግን ያነፃፅራል። መልእክቱ የኃይለኛው፣ አስቸኳይና የተከበረ ሆኖ፣ ምንም አይነት የፍቅርና የምስጋና ይዘት የለውም፤ ማንም በስም አልተጠቀሰም። ጠንካራ ስሜትና ሐሳብ ያለበት የውጊያ መልእክት ነው፤ የማርቲን ሉተር የተወደደ መልዕክትም ነበር። ከመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ሁሉ በላይ መጽደቅ በእምነት ብቻ እንደሆነ የሚያስተምር ጠንካራ መልእክት ነው።

## ትምህርት 30፡- ኤፌሶን

ኤፌሶን ጳውሎስ በእስር ቤት ሆኖ ከጻፋቸው አራቱ መልዕክቶች (ፊልጵስዩስ፣ ቆላስይስ፣ ፊልሞና እና አፌሶን) አንዱ ሲሆን፣ የቤተክርስቲያንን ታላቅ ሚስጥር ያሳያል፡፡ መልእክቱ "የጳውሎስ ቅድስተ ቅዱሳን" ወይም "የጳውሎስ ሶስተኛ ሰማይ" ተብሎ ይጠራል፡፡

በጳውሎስ 2ኛ የወንጌል ጉዞ ኤፌሶን ታዋቂ በነበረችበት ጊዜ፣ ጳውሎስ ወደ ኢሲያ ሊሄድ አስቦ ሳለ መንፈስ ቅዱስ ከልክሎት ነበር፡፡ ወደ ኤፌሶን ለመሄድ ባሰበ ጊዜ ተመልሶ ወደ አውሮፓ የቆሮንቶስን ርቀት ያህል ሄዷል፡፡ በሦስተኛ ጉዞው ወደዚያ ሄዶ ወንጌልን በመስበክ ለሁለት አመታት ቆይቷል (ሐዋሪያት ሥራ 18፡19፣ 19፡8-10) ፡፡

የኤፌሶን ሰዎች ማንም ከነገራቸው በላይ ስለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ከጳውሎስ ሰምተዋል፤ በዚያም ተቃውሞ ቢገጥመውም እግዚአብሔር ጠብቆታል፡፡ የኤፌሶንን ቤተክርስቲያን ይወዳታል፡፡ ይህ የጠለቀ መንፈሳዊ መልእክት የሚከተለውን ቅደም ተከተል ይዟል፡-

1. በክርስቶስ በኩል በሰማያዊ ሥፍራ የአማኞች ቦታ (1-3)
2. የአማኞች አኗኗር (4-6)
3. የመጨረሻ ዘመን (ም.4)
4. ሥነ-ምግባር (ም.5)
5. ማህበራዊነት (ም. 5፡21-6፡9)
6. መንፈሳዊ ውጊያ (6፡10-24)

## ትምህርት 31፡- ፊልጵስዩስ፣ ቆላስይስ

እነዚህ ሁለቱ መልእክቶች እንደ ኤፌሶንና እንደ ፊልሞና ከእስር ቤት የተጻፉ ናቸው፡፡ የፊልጵስዮስ መልእክት የጳውሎስንና የጢሞቴዎስን ምስጋና ስለተቀበሉት መንፈሳዊ ስጦታ ተጽፎ በፊልጵስዮስ ላሉ አማኞች በኤጳፍራ አማካኝነት የተላከ ደብዳቤ ነው፡፡ ጳውሎስ በፊልጵስዮስ ላለች ቤተክርስቲያን የተለየ ፍቅር ነበረው፡፡ በአንድ ወንዝ አጠገብ ብዙ ሴቶችን አግኝቶ፣ በዚያም ሊዲያ የምትባል ጌታን አምና ነበር፡፡ ጳውሎስና ሲላስ ወደ እስር ተጥለው ስለነበር፣ በሌሊት እግዚአብሔርን በምስጋና በዝማሬ ሲያመሰግኑት ታላቅ የምድር መንቀጥቀጥ እሥር ቤቱን አናወጠው፡፡ የእስር

ቤቱ ጠባቂና ቤተሰቦች በጌታ አመኑ፣ ተጠመቁም (ሐዋሪያት ሥራ ም16) ፡፡ “ደስታ” የሚለው ሐሳብ የመጽሐፉ /መልእክቱ/ ትልቅ ትኩረት ነው፡፡ በመከራ ደስ ይበላችሁ /ም. 1/፣ በአገልግሎት ደስ ይበላችሁ /ም. 2/፣ በክርስቶስ ደስ ይበላችሁ /ም. 3/፣ እና በሁሉ ደስ ይበላችሁ/ም.4/፡፡

ጳውሎስ ቆላስይስን የጻፈው የሐሰት ትምህርት ስለሰሙ ለማቅናት አስቦ ነው፡፡ ግርዛትን መተግብር፣ በምግብ ሕግ መጠበቅ፣ በአላት ማክበር፣ በመላእክት አማላጅነት ዙሪያ አማኞችን ከተሳሳተ ትምህርት ይጠብቃል፡፡ የክርስቶስ አምላክነት አልተረዱም ነበርና ጳውሎስ አረማቸው፡-

1. እውነተኛ አስተምህሮ /ም. 1-2/
2. ተግባራዊ ሕይወት /ም. 3-4/

## ትምህርት 32፡- 1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄ

በጳውሎስ 2ኛ የወንጌል ጉዞ ከሲላስ ጋር ቤተክርስቲያንን መስርቷል /ሐዋሪያት ሥራ 17፡1-10/፡፡ ከአይሁድ ካጋጠማቸው የሕዝብ አመጽ የተነሣ አንድ ወር ሳልሞላ ጊዜ ተቀምጠዋል፡፡ ይህች ትንሿ ቤተክርስቲያን ጥንካሬ አሳይታለች፡፡ እነዚህ አማኞች ሁሉም በዋናነት ከባዕድ አምልኮ የተለወጡ አህዛቦች ነበሩ፡፡ በዚያም በጥላቻና በአረመኔነት ሁኔታዎች ተከበው ነበር፡፡ ጳውሎስ የእነዚህን አማኖች ሁኔታ ለማወቅ ይጓጓ ነበር፡፡ ጢሞቴዎስ ግን ስለተሰሎንቄ አማኞች መልእክት ነገረው /3፡6/፡፡ ጳውሎስም አምነታቸውን እንዲጠብቁ ያበረታታቸው ነበር፡፡

1ኛ ተሰሎንቄ ስለ አስተምህሮ አነስተኛ ሐሳብ ይዞ በአመዛኙ ትኩረቱ ማበረታቻ ነው፡፡ ለአማኞች ሕይወትና አገልግሎት ይረዳቸው ዘንድ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ዳግም መመለስ ተናግሯል /1፡10፣2፡19፣3፡13፣ 4፡16-18 እና 5፡23/፡፡

2ኛ ተሰሎንቄ የመጀመሪያው ከተጻፈ ብዙም ሳይቆይ በአጭሩ ተጻፈ፡፡ ዋና መልእክቱ የክርስቶስ ዳግም መምጣት ነው፤ አንዳንዶች የመጀመሪያውን ደብዳቤ ሊያርም ነው የጻፈው ይላሉ፡፡ ይህ ደብዳቤ የክርስቶስ መምጣት ቀድመው ስለሚከሰቱ ነገሮች እና አማኞች በመከራ አንዲጸኑ እንዲሁም የክርስቶስን መመለስ በትዕግሥት እንዲጠብቁ ማወጅና ማሳሰብ ነው፡፡

## ትምህርት 33፡- 1ኛ እና 2ኛ ጢሞቴዎስ

1ኛ፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ እና ቲቶ ሶስቱም የምጋቤ መልእክቶች በመባል ይታወቃሉ፡፡ ይህም ወጣቶች የሆኑ አገልጋዮችን የመምከርና የመኖር ሌሎችን የማብቃት ምክር የተሰጠባቸው ስለሆነ ነው፡፡

የጢሞቴዎስ አባት ግሪካዊ፣ እናቱ ደግሞ አይሁዳዊ ናት፡፡ ጢሞቴዎስ ጳውሎስ ልስጥራ የምትባል ከተማ በሄደ ጊዜ በአስራ አምስት አመቱ ወደ ጌታ የመጣ /ሐዋሪያት ሥራ 16፡1-3፣ 1 ጢሞቴዎስ 1፡2/፣ ከሰባት አመት በኃላም የጳውሎስ የወንጌል ጉዞ አጋር የሆነ ወጣት ነበር፡፡

## 1ኛ ጢሞቴዎስ

ጳውሎስ ከመጀመሪያው እስራት በኃላ ኤፌሶንን ጎበኘ፡፡ ከዚያም በወጣ ጊዜ ጢሞቴዎስን በአገልግሎት ተክቶ ነበር፡፡ ጢሞቴዎስም ዝምተኛ፣ ትኩረት ፈላጊ እና ብቻውን በመከራ የተከበበ ወጣት ነበር፡፡ ጳውሎስ ከቆሮንቶስ የሚያበረታታ እንዲሁም በተግባር የተደገፈ የምክር ደብዳቤ ጻፈለት፡፡ ቁልፍ ጥቅስ 3፡15፤ ለጢሞቴዎስ የሐሰት ትምህርቶችን እንዲያስወግድና በጸሎት እንዲጠነክር የተሰጠ ምክር ነው፡፡ በመልዕክቱ ለቤተክርስቲያን መሪዎች፣ ለጠንካራ አገልግሎት የሚጠቅም ግልጽ መመሪያ ተሰጥቷል፡፡

## 2ኛ ጢሞቴዎስ

የጳውሎስ የመጨረሻ ደብዳቤ ነው፤ በሮም እሥር ቤት ሆኖ የሚለይበት ጊዜ ቅርብ መሆኑን አስቦ የጻፈው ነው፡፡ በድንገት ንብረቱን፣ ካባውን፣ መጽሐፍቶቹን መያዝ በማይችልበት ሁኔታ ተይዞ ታሰረ / 4፡13/፤ ብቻውንም ስለነበር አንደሚገደል ይጠብቅ ነበር /4፡10-12/፡፡ ለጢሞቴዎስ አስቸኳይ መልእክት ሲጽፍ ማርቆስን ይዞ እንዲመጣ እና የራሳቸውን ዕቃዎች እንዲያደርስለት ይፈልጋል፡፡ ቁልፍ ሐሳቦች፡- መከራ፣ አገልግሎት፣ ክህነትና የእግዚአብሔር ቃል፡፡

## ትምህርት 34፡- ቲቶ፣ ፊልሞና

ቲቶ ከአህዛብ ወገን ሆኖ በጳውሎስ ስብከት የተቀየረ ሰው ነው /1፡4/። ጳውሎስ ቲቶን በቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለውን ችግር ለይቶ የማውጣት ከባድ ስራ ሲሰጠው ይታያል /2ኛ ቆሮ.7፡6-7/። ጳውሎስ በቀርጤስ ቢለየውም እንኳን የመሪነትን ኃላፊነት ሲሰጠው እንደሚወጣው በማመን ነበር /1፡5/። ቲቶ የማይቻል ሁኔታን በማስተካከል ችግር ገዳይ የተባለ አገልጋይ ነው። ቲቶ ከጢሞቴዎስ በላይ ጠንካራ እና በሳል ሰው ይመስላል። ደብዳቤው ስለ ስሕተት አስተምህሮ ትልቅ ማስጠንቀቂያና የተግባር ምክር ያዘለ ነው። የደብዳቤው ዋና መልእክት ከመልካም ስራ ጋር ስለ አገልግሎቱና አስተምህሮ ምክር ገለጻ የተደረገበት ነው።

ፊልሞና የምልጃ፣ የልመና እና የይቅርታ ሐሳብ የያዘ ነው። መልእክቱ ስለ አናሲሞስ ፊልሞና ከቤቱ ስለወጣ ይቅርታ እና መልሶ ማስታረቅን የያዘ ጥሩ መልእክት ነው። ፊልሞና ሐብታም ሰው ነው /5-7፣22/፤ ምናልባትም በጳውሎስ ስብከት የዳነ ሊሆን ይችላል /ቁ.19/፤ አናሲሞስ ከጌታው ቤት ጠፍቶ ወደ ሮም በመሄድ ጳውሎስን ካገኘው በኃላ ወደ ጌታ መጣ /ቁ.10/። ይህም የአናሲሞስ የመለወጥ ባህሪይ ብሎም ስለይቅርታ ያለውን ጉጉት የሚያሳይ ነው።

## ትምህርት 35፡- ዕብራውያን

ይህ ደብዳቤ የጸሐፊ አሻራ ወይም ፊርማ የለውም፤ ሆኖም ብዙዎች በጳውሎስ የተጻፈ እንደሆነ ይገምታሉ። በዋናነት የተጻፈው ለዕብራውያን አማኞች ሲሆን፣ አላማው በብሉይ ኪዳን የታየው የክህነት አገልግሎት ለአማኞች ምን ይመስላል የሚል ነው። ክርስቶስ ፍጹም ካህን እና ንጹህ መስዋዕት ሆኖ እንደነበር ያሳያል። የመጀመሪያ አስሩ ምዕራፎች የእግዚብሔር ልጅ ከመላእክት፣ ከሙሴ፣ ከኢያሱ፣ ከአሮን እና ከመልከጼዴቅ የበላይ እንደሆነ ያሣያሉ። ምዕራፍ 11-13 የአማኞች ሕይወት ምን እንደሆነ ይናገራል።

## ትምህርት 36፦ ያዕቆብ

ጸሐፊው በኢየሩሳሌም ቤተክርስቲያን መሪ የሆነ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንድም ያዕቆብ ነው፤ በ62 ዓ.ም ሰማዕት ሆኗል /ሐዋሪያት ሥራ 12፡17፣ 15፡13/፡፡ ደብዳቤው የተጻፈው ከተቀደሰው ምድር ውጪ ለሚኖሩ ከአይሁድ ዘንድ ለተለወጡ አማኞች ነው፡፡ ነገር ግን መልእክቱ ለሁሉም አመኞች የሚጠቅምና ተግባራዊ እንደሆነ የሚታወቅ ነው፡፡ ዋና መልእክቱ እውነተኛ ሐይማኖት የሚገለጠው በመልካም ሥራ ነው የሚል ነው፡፡ አንዳንድ መልእክቶች ለተወሰኑ ሁኔታዎች በአማኞች ሕይወት የሚተገበሩ ናቸው፦ በመከራ ላሉ /1፡2-4/፣ ለሃብታሞች /1፡9-11፣ 5፡1-6/ ፣ የቤተክርስቲያን አባላት አመለካከት /2፡1-9/፣ በመሪነት ላሉ /3፡1/፣ ለሚያመቻምቹ /5፡19-20/፡፡ ያዕቆብ ስለትምህርቱ ግልጽ የሆኑ ምሳሌዎችን ይጠቀማል /1፡6፣11፣17፣23፣26፣3፡3፣ 5፣7፣12፣4፡14፣5፡1-2፣7)፡፡

## ትምህርት 37፦ 1ኛ እና 2ኛ ጴጥሮስ

1ኛ ጴጥሮስ ከስደትና መከራ የተነሣ ግራ ለተጋቡት አማኞች የተፃፈ ነው፡፡ አፃፃፉም እውነተኛ፣ ልባዊ እና ስብከት ነክ ነው፡፡ ቁልፍ ቃሉ "መከራ" ከ15 ጊዜ በላይ ተጠቅሷል፡፡ ጴጥሮስ የሚናገረው ስለ ሹመቱና ኃላፊነቱ በአማኞች ሕይወት ስለተገለጠው ስለከበረው የክርስቶስ ማዳን ነው፤ የሚገልፀውም ስለ ሕብረተሰቡ ማህበራዊ ጉዳዮች፣ መልካም ዜግነትና በእምነት ስለተገኘው ሕይወት ሥራዎች ነው፡፡ ክርስቶስ የተስፋ ምንጭ /1፡3/፣ ህያው መስዋዕት /1፡19/፣ የማዕዘን ራስ /2፡6/፣ እውነተኛ ምሳሌ /2፡21/፣ መከራ የተቀበለ /2፡23/፣ ኃጢአትን የሚያስወግድ /2፡24/ ፣የነፍስ እረኛ /2፡25/ እና የከበረ ጌታ መሆኑን /3፡22/ ያብራራል፡፡

2ኛ ጴጥሮስ ፌዘኞችን ብሎም የተበላሹ አስተማሪዎችን በመቃወም ነው የፃፈው፡፡ ዋና ትኩረቱ በእግዚአሔር ቃልና መለኮታዊ ተስፋ መፈፀም ላይ ነው፡፡ እንደ 2ኛ ጢሞቴዎስ እና 2ኛ ጴጥሮስ ሁሉ የመጨረሻው ዘመን ቅርብ መሆኑን፣ ተጠባቂው የክብር ቀን ከቤተክርስቲያን ፊት እንዳለ ትኩረት ይሰጣል፡፡

የጴጥሮስ መልእክት ሰባት ውድ ነገሮችን ይጠቅሳል፡- ታላቁ መከራ /1፡7/፣ የክርስቶስ ደም /1፡19/፣ ሕያው ድንጋይ /2፡4/፣ ክርስቶስ /2፡6/፣ ቀንና ዝምታ መንፈስ /3፡4/፣ የአማኞች እምነት /2ኛ ጴጥ 1፡1/ እና መለኮታዊ ተስፋ /2ኛ ጴጥ 1፡4/።

## ትምህርት 38፡- 1ኛ፣ 2ኛ፣ 3ኛ ዮሐንስ

ዮሐንስ ሐዋሪያው ሶስት ደብዳቤዎችን ጽፋል፡-

## 1ኛ ዮሐንስ

ይህ መልእክት "የእርግጠኝነት መልእክት" ነው፤ ቁልፍ ቃላቶቹ፡- ብረት፣ እውቀት፣ ፍቅር ናቸው። ትኩረት አድርጎ የሚናገረው ለአማኞች ስለተገለጠው መንፈሳዊ እውቀት ነው። "እወቅ" የሚል ቃል ወይም ተያያዥ የሆነ ሐሳብ ከ30 ጊዜ በላይ ተጠቀሷል። ዋና ሐሳቡ፡-

1. እግዚአብሔር ሕይወትና ብርሃን ነው /ምዕ. 1-2/
2. እግዚአብሔር ፍፁም ፍቅር ነው /ምዕ .3-4/
3. ፍቅርና እምነት በአለም ላይ ያለውን ኃይልና ግጭት ሁሉ ይሸፍናል /ምዕ .5/

## 2ኛ ዮሐንስ

ይህ መልእክት የፃፈው ከሐሰት ትምህርት ለመጠበቅና ከሐሰት አስተማሪዎች ጋር ሕብረት ያላቸውን ለማስጠንቀቅ ነው /ቁ 7-11/። "ፍቅር" የሚለው ቃል አራት ጊዜ ፣ "እውነት" አምስት ጊዜ ተጠቅሷል።

## 3ኛ ዮሐንስ

መልእክቱ የተፃፈው ለበጎ ሥራ ለተሰጠው ለጋይዮስ ነው። መልእክቱም እሱንና ሌሎች ሁለት ሰዎችን ያማከለ ነው። እነርሱም የሚገሰጸው ዲዮጥሮጢስና መልካም ምስክርነት ያለው ዲሜጥሮስ ናቸው።

## ይሁዳ

ይሁዳ የተፃፈው በኢየሱስ ክርስቶስ ታናሽ ወንድም ያዕቆብ ነው። የተፃፈው ግራ በሚያጋቡና በሚከፋፍሉ ሐሰት አስተማሪዎች ለተቸገሩ አማኞች

ስብስብ ነው፡፡ የይሁዳ ትኩረት ይህንን አስተምህሮ መጽናት እንዲችሉ ማድረግ ነው፡፡

## ትምህርት 39፡- ዮሐንስ ራዕይ

መጽሐፉ የተፃፈው ዮሐንስ በፍጥሞ ደሴት ታስሮ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ መልዕክቱ የተፃፈው የአማኞች ስደት /2፡3/፣ ለመውጣት አስቸጋሪ /2፡10/ እና ክፉ የሮማውያን አምልኮ በነበረበት ወቅት ነው፡፡ መጽሐፉ ለቤተክርስቲያን ማበረታቻ ብሎም በመከራ እንዲፀኑ ለማድረግ ተፈልጎ የተጻፈው ነው፤ መልእክቱ ግን በጣም አስፈላጊ መልእክት ነው፡፡ ይህም ክፉ ሲፈረድበትና ክርስቶስ በዘላለማዊ የክብር መንግሥት ሲገለጥ፣ የትንቢት ሁሉ ፍጻሜ እንዴት እንደሚሆን የሚያሳይ ሥዕላዊ መግለጫ አለው፡፡ ይህ ለታማኝ አንባቢያን ልዩ ኪዳን ወይም ተስፋ ያለው፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ሁሉ የተለየ ብቸኛ መጽሐፍ ያደርገዋል /1፡3/፤ በቃሉ ላይ ለሚጨምሩ የታወጀ እርግማንንም ያሳያል /22፡18-19/፡፡

## ትምህርት 40፡- የራዕይ መጽሐፍ ቅደም ተከተል፡፡

1. መግቢያ /1፡1-20/
2. 7ቱ ደብዳቤዎች ለ7ቱ ቤተክርስቲያናት /2፡1-3፡22/
3. በሰማይ የታየ ራዕይ /4፡1-11/
4. ሰባቱ ማህተሞች /5፡1-8፡5/
5. ሰባቱ መለከቶች /8፡6-11፡19/
6. ሰባቱ ምልክቶች /12፡2-14፡20/
7. ሰባቱ ካህናት /15፡1-16፡21/
8. የክርስቶስ ተቃዋሚ መነሳትና መመታት /17፡1-20፡15/
9. የእግዚአብሔር ከተማ /21፡1-22፡5/
10. መዝጊያ /22፡6-21/

የራዕይ መጽሐፍ መዝጊያው ከዘፍጥረት መጀመሪያ ምዕራፎች ጋር ያለውን በማነፃፀር ይዘጋል፡፡ ዘፍጥረት ስለ ፍጥረት ጅማሮ፣ ኃጢአት፣ መርገም፣ የሰይጣን ድል፣ ከሕይወት ዛፍ መለየትን ይናገራል፡፡ የራዕይ መጽሐፍ ደግሞ ፀሐይ የሚያስፈልግ ቦታ መኖሩን፣ ኃጢአት የማይገኝበት፣ መርገም

የሚቆምበት፣ ሰይጣን የሚጣልበት እና የሕይወት ዛፍ የሚገኝበት መሆኑን ይናገራል፡፡

***” ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና!”***

# የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ

## መግቢያ

የዚህን ጥናት ርዕስ ባነበብክ ሰዓት ከባድም የማይገባም ነው ብለህ ወስነህ ይሆናል፡፡ ነገር ግን በዚህ ፈንታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተበተኑ እውነታዎችና የእምነታችን መሠረቶች ባገኘህ ጊዜ አመለካከትህ ይቀየራል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ ማለት “ትምህርት” ማለት ነው፤ ስለ አገልግሎትህ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ምን እንደሆነ፣ ሌሎችም ስለሚጠይቁህ ጥያቄ መልስ ይሰጣል፡፡ በጠለቀ ጥናትና እውቀት ስታስተምራቸው በሐሰት ትምህርት እንዳይወሰዱ እጅጉን ያግዛል /እብራውያን 13፡9/፡፡

***ማስታወሻ፡-*** በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ነገሮች በሙሉ የተወሰዱት ከሁለት መጽሓፍት ነው፡- 100 Bible Lessons, by Douglas Alban, Published by Gospel Litrrature Service in Bombay, India, and the great Doctrines of the Bible, by William Evans, Published by Moody Press in Chicago.

## የዚህ ትምህርት ጥናት ይዘቶች


ክፍል 1፡- አስተምሮተ እግዚአብሔር

ክፍል 2፡- አስተምህሮተ ኢየሱስ ክርስቶስ

ክፍል 3፡- አስተምህሮተ መንፈስ ቅዱስ

ክፍል 4፡- አስተምህሮተ ሰው

ክፍል 5፡- አስተምህሮተ ድህንነት

ክፍል 6፡- አስተምህሮተ ቤተክርስቲያን

ክፍል 7- አስተምህሮተ መጽሐፍ ቅዱስ

ክፍል 8- አስተምህሮተ መላዕክት

ክፍል 9- አስተምህሮተ ሰይጣን

ክፍል 10- የመጨረሻው ዘመን አሰተምህሮ

# ክፍል ሁለት
# የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ
# አስተምህሮተ እግዚአብሔር

## ትምህርት 1፡- ህላዌ እግዚአብሔር /የእግዚአብሔር መኖር/

እግዚአብሔር ስለመኖሩ የሚያስረግጡ ብዙ እውነታዎች አሉ፡፡ በዚህ ክፍል የተወሰኑትን እናያለን፡-

1. ***መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ፡-*** መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው በዘፍጥረት 1፡1 በእግዚአብሔር መኖር ነው፡፡ የእግዚአብሔርን መኖር የሚቃወም ሞኝ ነው /መዝሙር 14፡1/፡፡

*2. **የፍጥረት ማስረጃ፡-** የሰማይ ውበትና ክብር የእግዚአብሔርን መኖር ይናገራል /መዝሙር 19፡1/፤ ፍጥረት ዘላለማዊውን የእግዚአብሔር ገዥነት ያስተምራል /ሮሜ 1፡20/፡፡*

*3. **የህሊና ማስረጃ፡-** ሰው በፍጥረት ሁሉ ላይ የበላይ እንዲሆን ተደርጎ ነው የተፈጠረው፡፡.*

*4. **ሌሎች ማስረጃዎች፡-** የእግዚአብሔርን መኖር የሚያስረዱ ብዙ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ፡-*

- የአለም መኖር፡- ይህን አለም ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣ አንድ ኃይል አለ፡፡
- የዚህ ዓለም ቅንብር ወይም ቅርጽ አንድ ጥበበኛ አእምሮ የሠራው መሆኑን መረዳት አያዳግትም፡፡
- ሰው እውቀትና ሥርዓት ያለው ሆኖ መፈጠሩ የፈጣሪን ሕያውነት፣ አዋቂነትና ሥርአት ያስረግጣል፡፡
- ሕይወት ጅማሬ አለው፤ የመጣውም ዘላለማዊ ከሆነው ፈጣሪ መሆኑ ግድ ነው፡፡

***ማጠቃለያ፡*** ዕብራውያን 11፡6 "ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ፣ እርሱ እግዚአብሔርን ማመን ይገባዋል፡፡" በመጽሐፍ ቅዱስና በዘፍጥረት በተገለጠው እግዚአብሔር እንደ ልጆች በማመንና በእርሱ በመታመን ወደ እርሱ /እምነት/ እንምጣ፡፡

## ትምህርት 2፡- የእግዚአብሔር ማንነት

ስለ እግዚአብሔር እውነተኛ እውቀት እንድናገኝ የሚረዳን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ /ዮሐንስ1፡18፣ 1ኛ ዮሐንስ 4፡12/፡፡ ስለ እግዚአብሔር አንዳንድ እውነታዎችን እንመልከት፡-

1. ***ማንነቱ፡-*** የእግዚአብሔር ማንነት የሚገለጠው በእውቀት፣ በስሜትና በኃይሉ ነው፡፡ እግዚአብሔር ራሱን የቻለ ህያውና ትክክለኛ ባህሪያት ያሉት አምላክ ነው /ኤርሚያስ 10፡10፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡9/፡፡

2. ***ተፈጥሮ፡-*** እግዚአብሔር መንፈስ ነው፤ መንፈስ ደግሞ ሥጋም፣ አጥንትም፣ ደምም የለውም /ዮሐንስ 4፡24/፡፡

3. ***አንድነት፡-*** ከሌሎች ብዙኃን አማልክት ጋር ሲተያይ፣ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው /ዘዳግም 6፡4፣ ኢሳይያስ 44፡6/፡፡

***ማጠቃለያ፡-*** ስለ እግዚአብሔር በተማርን ቁጥር፣ አምላካችን ታላቅ አምላክ እንደሆነ የበለጠ እናውቃል፡፡

## ትምህርት 3፡- የእግዚአብሔር ባህሪያት

ባህሪይ የሚለውን ቃል መረዳት ያስቸግራልን? ቃሉ ጥራትን ወይም የአንድን ነገር ልዩ መለያ ማንነት ያመለክታል፡፡ በዚህ ክፍል የእግዚአብሔር ልዩ ባህሪያት እንመለከታለን፡-

1. ***ዘላለማዊነት፡-*** እግዚአብሔር እውነተኛ አምላክ ስለሆነ፣ መጀመሪያና መጨረሻም የለውም /መዝሙር 90፡2፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡17/፡፡
2. ***አይለወጤነት፡-*** /1ኛ ሳሙኤል 15፡29፣ ሚልኪያስ 3፡6/፡፡
3. ***ሁሉን*** ቻይነት፡- ሁሉንም ኃይል የሚቆጣጠር አምላክ ነው /ኢዮብ 42፡2 ፣ኤርሚያስ 32፡27/፡፡
4. በሁሉ ቦታ መገኘት ፡- በአንድ ጊዜ በሁሉ ሥፍራ ይገኛል /መዝሙር 139፡7-9/፡፡
5. ሁሉ አዋቂነት፡- እውቀት ሁሉ አለው /1ኛ ዜና 28፡9፣ 2ኛ ዜና 16፡9 ፣መዝመር 94፡11፣ ኢዮብ 42፡2፣ ኢሳይያስ 40፡28/፡፡

***ማጠቃለያ፡-*** ድሃና ተራ የሆነ ሰው እነዚህ ባህሪያት ያሉት ታላቅ እግዚአብሔር ሊኖረው ይገባል፡፡ ሁሉም ባህሪያት ለምን ለሰው አስፈላጊ ሆኑ?

## ትምህርት 4፡- የእግዚአብሔር ሥነ-ምግባራዊ ባህሪያት

እያንዳንቸው ባህሪያት የስብከት ርዕስ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

1. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው /ዘፀአት 15፡11፣ ኢሳይያስ 6፡3፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡16/
2. እግዚአብሔር ፃድቅ ነው /መዝሙር 116፡5፣ ዕዝራ 9፡15፣ ኤርሚያስ 12፡1/
3. እግዚአብሔር መኃሪ ነው /መዝ. 103፡8፣ ሮሜ 9፡18/
4. እግዚአብሔር ፍቅር ነው /1ኛ ዮሐንስ 4፡8-16፣ ዮሐንስ 3፡16፣16፡27/
5. እግዚአብሔር ታማኝ ነው /1ኛ ቆሮንቶስ 1፡9፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡13/

ከሳምንት በፊት የእግዚአብሔርን ሞራል ባህሪያትን አስታውስ፡- ***ክቡር*** /ዘጸአት 15፡11 *መዝሙር* 145፡5/፣ ***ቸር*** /ዘጸአት 34፡6፣ *መዝሙር* 116፡5/፣ ***ታጋሽ*** /ዘኁልቁ 14፡18፣ *ሚኪያስ* 7፡18/፣ ***ቀናተኛ*** /ኢያሱ 24፡19፣ ናሆም 1፡2/፣ ***ሩህሩህ*** /1ኛ *ነገስት* 8፡23/፣ ***ታላቅ***/ 2ኛ ዜና 2፡5፣ *መዝሙር* 86፡10/፣ ***የማይደረስ*** /ኢዮብ 11፡7፣መዝ 145፡3/፣ ***የማይታይ*** /ኢዮብ 23፡8-9፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡17/፣ ***መልካም*** /*መዝሙር* 102፡26-27/፣ ***ብርሃን*** /ኢሳይያስ 60፡19 ፣1ኛ ዮሐንስ 1፡5/፣ ***እውነት*** /ኤርሚያስ 10፡10/፣ ***ፍፁም*** /ማቴዎስ 5፡48/ ፣ ***ኃጢአት የሌለበት*** /ሮሜ 1፡23/፣ ***ሥጋ ለባሽ*** / 1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡17 6፡16/፣ ***የሚባላ እሳት፣*** /ኢዮኤል 12፡29/ እና ***እንደ እርሱ ያለ ማንም የለም*** /ዘጸአት 9፡14፣ዘዳ 33፡26/፡፡

***ማጠቃለያ፡-*** የእግዚአብሔር ቅድስና የኃጢአትን መቀጣት ይሻል፤ እግዚአብሔር እንዴት ነው በአንድ ጊዜ አፍቃሪም ቅድስና ፈላጊም የሚሆነው? ኃጢአተኛ ለሆነው ሰው እንዴት ነው መኃሪም ጻድቅ ፈራጅም ሊሆን የሚችለው?

*መልሱ ጎልጎልታ ነው፡- በኃጢአት ላይ የተገለጠው የእግዚአብሔር ቁጣና ኃጢአተኛውን የሚያድን የእግዚአብሔር ምህረት!*

## ትምህርት 5፡- ሥላሴ

ለሰዎች ራሱን በሶስት ስብዕና የገለጠው ዘላለማዊ የሆነ እግዚአብሔር አንድ አምላክ ነው። እርሱም፡- አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ ነው። ሥላሴን የሚያሳዩ /የሚያስረዱ/ ጥቅሶችን እንመልከት፡-

1. ***በኢየሱስ ክርስቶስ መጠመቅ /ማቴዎስ 3፡13-17/፡-*** አብ ከሰማይ ተናገረ ልጁ ተጠመቀ፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ መልክ በአዳኙ ላይ አበራ።
2. ***የጥምቀት ትዕዛዝ /ማቴዎስ** 28፡19/፡-* "በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኃቸው:" "ስም" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር አመልካች ነው።
3. **የጳውሎስ ቡራኬ /በ2ኛ ቆሮንቶስ 13፡19/፡-** "የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ የአግዚአብሔር ፍቅር፣ የመንፈስ ቅዱስ አንድነት።"
4. **በዘፍጥረት ላይ ሰው በተፈጠረ ጊዜ** የተጠቀሰው ብዙ ቁጥር /ዘፍ 1፡26/፡-"ሰውን በመልካችን በምሳሌያችን እንፍጠር።"

***ማጠቃለያ፡-*** ሰው እራሱ በሶስትነት ይገለፃል፤ ለምሳሌ ሶስት አካል አለው፡- ሥጋ፣ ነፍስ፣ መንፈስ ምክንያቱም በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል።

# አስተምህሮተ ኢየሱስ ክርስቶስ

## ትምህርት 6፡- የትንቢቶች መፈፀም

ከመቶ አመታት በኃላ በአዲስ ኪዳን የተፈፀሙ፣ በብሉይ ኪዳን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩ ብዙ ሐሳቦችን ማየት ይቻላል። እነዚህም አስፈላጊ እውነታዎች፡-

1. ክርስቶስ ከእስራኤል እንደሚመጣ /ናሆም 24፡17-19፣ ማቴዎስ 1፡17/።
2. ክርስቶስ ከይሁዳ ነገድ ከዳዊት ዘር እንደሚወለድ /ዘፍጥረት 49፡10 ፣ኢሳይያስ 11፣ ሉቃስ 1፡31-33/።
3. በቤተልሔም እንደሚወለድ /ሚኪያስ 5፡2 ፣ሉቃስ 2፡4-7/።
4. ከድንግል እንደሚወለድ /ኢሳይያስ 7፡14፣ ማቴዎስ 1፡18 22፡23/።

5. አመጣጡ ከነሱ በፊት ከነበሩት መነገሩ /ኢሳይያስ 40፡3 ፣ ማቴዎስ 3፡3/፡፡
6. መሲሁም አምላክ እንደሆነ /ኢሳይያስ 9፡6 ፣ዮሐንስ 1፡14/፡፡
7. የልጅነት ጊዜው በግብፅ እንደሚያሳልፍ /ሆሴዕ 11፡1፣ ማቴዎስ 2፡13-18/፡፡
8. ስለ ኃጢአት እንደሚሞት እና መከራ እንደሚቀበል /ኢሳይያስ 53፡46 ፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21/፡፡
9. ንጉሥ ክርስቶስ በአህያ ውርንጫ ተቀምጦ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚገባ /ዘካሪያስ 9፡9 ማቴዎስ 21፡2-5/፡፡
10. በሞቱ ጊዜ መስቀል ላይ መራራ ሆምጣጣ እንደሚያጠጡት /መዝሙር 69፡21 ማቴዎስ 27፡34/፡፡
11. እንደ ሮማውያን በስቅላት የመግደል ሥርዓት አንገቱ መስበሩ /መዝሙር 34፡30፣ ዮሐንስ 19፡33-36/፡፡
12. ሰዎች በልብሱ ላይ ዕጣ እንደሚጣጣሉ /መዝሙር 22፡18፣ ማቴዎስ 2713/፡፡
13. በመከራው ጊዜ የተወሰኑ ቃላት አንደሚናገር /መዝሙር 22፡22፡1፣ ማርቆስ 15፡34/፡፡
14. ከሞት እንደሚነሣ /መዝሙር 16፡10፣ ሐዋሪያት ሥራ 2፡ 13/
15. ማጠቃለያ፡- እነዚህ እያንዳንዳቸው ትንቢቶች በኃይና ሁሉን ቻይነቱ ሌላው ማስረጃዎች ናቸው፡፡

## ትምህርት 7፡- የኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት

ኢየሱስ ክርስቶስ ለአምላክ ብቻ የሆኑት ባህሪያት ስላሉት፣ አምላክ መሆኑን እናውቃለን፡፡ ይህን የሚያሰረግጡ ጥቅሶች እንመልከት፡-

1. ***ዘላለማዊነት*** /ሚኪያስ 5፡2፣ ዮሐንስ 8፡58፣ ቆላስይ 1፡17፣ ራዕይ 1፡8/፡፡
2. ***አይለወጤነት*** /ኢዮብ 8፡24/፡፡
3. ***ሁሉን ቻይነት*** /ሉቃስ 8፡24፣ ማቴዎስ 28፡18/፡፡
4. ***በሁሉ ሥፍራ መገኘት*** /ማቴዎስ 18፡20፣ ዮሐንስ 1፡48፣ ዮሐንስ 3፡13/፡፡

5. ***ሁሉን አዋቂነት*** /ማር 11፡2-6 ዮሐንስ 2፡2 /4-25 ሉቃስ 5፡22 ማቴዎስ 24፡3-31/።

6. ***ቅድስና*** /ማርቆስ 1፡24፣ ኃጢአት የሌለበት /1ኛጴጥሮስ 2፡22፣ ዩሐንስ 19፡4/።

7. ***ጻድቅ ፈራጅ*** /ዮሐንስ 2፡14-17/፣ ቤተመቅደስን ያነፃ /ሐዋሪያት ሥራ 17፡31/፣ ቅዱስ ፈራጅ

8. ***አፍቃሪ*** /ዮሐንሰ 15፡13፣ ዮሐንስ 11፡36/።

9. ***መኃሪ*** /ቲቶ 3፡5 ፡- ስለ አኛ ሞተ/

10. ***ታማኝ*** / 2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡13/

አምስቱም የአምላክ ሥራዎች ከክርስቶስ ጋር ተጠቅሷል፡- ***ፍጥረት*** /ዮሐንስ 1፡33/፣ ***ጥበቃ*** /ኢዮብ. 1፡3/፣ ***ይቅርታ*** /ሉቃስ 7፡48/፣ ***ከሞት ማስነሣት*** /ዮሐንስ 6፡39/ እና ***ፍርድ*** /ዮሐንስ 5፡22/።

***ማጠቃለያ***፡- የኢየሱስ ከሞት የመነሣቱ እውነታ የአምላክነቱ አይነተኛ ማረጋገጫ ነው!

## ትምህርት 8፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ሰዋዊነት

አዳኝ ለመሆን አምላክ ብቻ መሆን ሳያበቃ ከድንግል መውለድና እውነተኛ ሰው መሆን አስፈልጎታል /1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡5/። ሰብአዊነቱን የሚያስረዱ ማስረጃዎች፡-

1. በሰው ስም መጠራቱ /ማቴዎስ 1፡21/፣ ለ77 ያህል ጊዜ የሰው ልጅ ተብሎ ተጠርቷል።

2. የዘር ሐረጉ ከሰው መሆኑ /ማቴዎስ 1፡1-16/።

3. እንደ ሰው መራቡ /ማቴዎስ 4፡2/፣ መጠማቱ /ዩሐንስ 4፡7 19፡28/።

4. እንደ ሰው መልበሱ /ዩሐንስ 4፡6/፣ ማንቀላፋቱ /ማቴዎስ 8፡24/።

5. መውደዱ /ማርቆስ 10፡21፣ ዮሐንስ 11፡36/፣ ርኃራሄ ያለው መሆኑ /ማቴዎስ 9፡36/።

6. ማልቀሱ /ዮሐንስ 11፡33/፣ መቆጣቱ /ዮሐንስ 11፡33/፣ ማዘኑ /ዮሐንስ 26፡35፣ ሉቃስ 19፡41/።

7. አቃስቷል /ዮሐንስ 11፡33፣ አልቅሷል /ማርቆስ 3፡4/።

8. ስጋ ለብሷል /ዩሐንስ 1፡14/፣ ነፍስ /ማቴዎስ 26፡38/ እና መንፈስ /ሉቃስ 23፡46/

***ማጠቃለያ*** ፡- አምላክ እና ሰው፣ ተመስገን እንዴት ያለ አዳኝ ነው!

## ትምህርት 9፡- የክርስቶስ ሕይወት /ክፍል አንድ/

ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ምድራዊ ኑሮ ብዙ ዝርዝር ነገሮች ተጽፈዋል፡፡

1. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ሆኖ ለዘላለም ይኖራል፤ ከሁሉም በፊትም ነበር፡፡
2. ከድንግል መወለዱ በማቴዎስና በሉቃስ ተጽፏል፡፡
3. በስምንት ቀኑ ተገርዟል /ሉቃስ 2፡21/፡፡
4. በ12 ዓመቱ ወደ ቤተመቅደስ ተወስዷል /ሉቃስ 2፡41-48/፡፡
5. ቀዳሚ ዕድሜውን በአናፂነት በናዝሬት አሳልፏል /ማርቆስ 6፡3/፡፡
6. የመጀመያው አገልግሎት ጅማሬ ለስድስት ወራት በይሁዳ፣ ሰማሪያ እና ገሊላ ነበር፡፡
7. ሁለተኛው አገልግሎቱ ከስድስት እስከ ስምንት ወራት ያለው ጊዜ የስብከት፣ የፈውስ፣ በቆጽሮንየምና ገሊላ ተአምራት ያደርግ ነበር፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ተአምራት ወሰኖች፡-

ሀ. በተፈጥሮ ላይ /ማቴዎስ 8፡26-27/፡፡

ለ. በሰይጣን ላይ /ማርቆስ 5፡12-13/፣ ማቴዎስ 8፡28-32፣ 9፡32-33፣15፡22-28፤ 17፡14-18፣ ማርቆስ፣ 1፡23-27/

ሐ. በበሽታ ላይ፡- የሽባው መፈወስ /ማርቆስ 8፡13፣ ማርቆስ 9፡6/፣ መራመድ የማይችለው ሰው ፈውስ /ዮሐንስ 5፡9/፣ ከድካም መንፈስ ነጻ የሆነች ሴት /ሉቃስ 13፡12/፣ ደም የሚፈሳት ሴት ፈውስ /ማቴዎስ 9፡22/፣ ሆዱ የተነፋ ሰው ፈውስ /ሉቃስ 14፡2/፣ በንዳድ ታማ የነበረች ሴት ነጻ መውጣት /ማቴ 8፡15 /፣ የዲዳው ፈውስ /ማቴዎስ 9፡33/፣ የአይነስውሩን አይን ማብራት /ዮሐንስ 9፡ 1-38/፣ የማይሰማ ጆሮ ፈውስ /ማቴዎስ 11፡5/፣ ለምጻሙን ማዳን /ማቴዎስ 8፡3፣ ሉቃስ 17 ፡19/፣ ኢየሱስ ቢያንስ ሌሎች አሥር የተለያዩ በሽታዎችን ፈውሷል፡፡

መ በሞት ላይ፡- አልአዛር /ዮሐንስ 11፡43–44/፣ የኢያይሮስ ልጅ /ማቴዎስ 9፡18–26/፣ በናይን የመበለት ልጅ / ሉቃስ 7 ፡ 12–15/፡፡

ሠ. በተለያዩ ነገሮች ላይ፡- ውሃን ወደ ወይን ጠጅ መቀየር /ዮሐንስ 2፡1–11/ አምስት ሺህ ሰዎችን መመገብ /ዮሐንስ 6፡1–14/፣ በባህር ላይ መሄድ /ዮሐንስ 6፡15–21/፣ አራት ሺህ ሰዎችን መመገብ /ማቴዎስ 15፡32–39/፣ የበለስ ዛፍን መርገም /ማቴዎስ 21፡18–22/፣ ከአሣ አፍ ዲናር ማውጣት /ማቴዎስ 17፡27/ እና በተዓምር አሣ ማጥመድ /ሉቃስ 5፡1–11 እና ዩሐንስ 21፡ 6/፡፡

ረ ትንሣኤው ከሁሉ የሚበልጥ ታዓምር ነው /1 ቆሮንቶስ 15፡4፣ ሮሜ 1፡4/፡፡

## ትምህርት 10፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ማጠቃለያ

1. ሶስተኛው ደረጃ አገልግሎቱ ለአንድ አመት ያህል በገሊላ ነበር፡፡ ብዙ ሰዎች ተከትለውታል፣ የተራራውን ስብከትም አድርጓል /ማቴዎስ 5፣6 እና 7/፡፡
2. በቀጣይ ኢየሱስ ክርቶስን ለመግደል ፈሪሳዊያን ይነዘንዙት ነበር፡፡ ኢየሱስም በቆጵሮንየም፣ ፍንቄ፣ ቤተሳይዳ፣ ቂሳሪያ፣ ፊሊጱስዩስ ተዘዋውሮ፣ በመጨረሻም ወደ ገሊላ እንደገና ሄዷል፡፡
3. የመጨረሻዎቹ ስድስት ወራት በማስተማር፣ በመስበክና ወደ ተለያዩ በታዎች በመዘዋወር ነበር ያሳለፈው፡፡
4. የመጨረሻው ሳምንት የሆሳዕና ቀንን፣ የጌታ እራትን፣ ጌቴሰማኒን፣ መከራውንና የመስቀል ላይ ሞቱን ያጠቃልላል፡፡
5. በትንቢት እንደተነገረ በሶስተኛ ቀን ከሞት ተነስቷል፡፡
6. ከትንሣኤው በኂላ 40 ቀናት ቆይቶ፣ በአይን እየታየ ሥጋ እንደለበሰ ወደ ላይ አርጓል /ሐዋሪያት ሥራ 1፡10 ፣11/፡፡
7. ውይይት፡- ከምድራዊ ሕይወቱ የክርስቶስን አምላክነት የሚያመለክተው የትኛው ክስተት ነው? ሰዋዊነቱንስ?

## ትምህርት 11፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ

“ትንሣኤ” የሚለው ሐሣብ በአዲስ ኪዳን 104 ጊዜ ተጠቅሷል፡ ክርስትና ሕያውና ሕይወትንም ከፈጠረ አምላክ ጋር የሚያገናኝ ብቸኛው ኃይማኖት ነው።

### 1. የትንሣኤ ማስረጃ

ሀ. ባዶ መቃብር /ማቴዎስ 28፡6፣ ሉቃስ 24፡3/።

ለ. የመላእክት ምስክርነት /ማቴዎስ 28፡ 46 እና ሉቃስ 24፡5-7/።

ሐ. ከትንሣኤ በኋላ ከሰዎች ጋር ተገናኝቶ ተናግሯል /ጴጥሮስ፣ ማሪያም፣ ፊልጶስ፣ ቶማስ/።

መ. ኢየሱስ ክርስቶስ በልቷል፣ ጠጥቶአል፣ ቁስሉንም አሳይቷቸዋል።

ሠ. 500 የሚሆኑቱ በአንድ ጊዜ አይተውታል /1ኛ ቆሮንቶስ 15፡6/።

ረ. እስጢፋኖስ በተገደለ ጊዜ ከሰማይ ሆኖ ታይቷል /ሐዋሪያት ሥራ 7፡56/።

ሰ. በደማስቆ መንገድ ለጳውሎስ ተገልጦአል /ሐዋሪያት ሥራ 9፡5/።

ሸ. በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስለ ህያውነቱ መስክረዋል፣ አረጋግጠዋል።

ቀ. ሌሎች ብዙዎች የማይለወጥ ማስረጃ አላቸው /ሐዋሪያት ሥራ 1፡3/።

### 2. የትንሣኤ አካል ምን ይመስላል

ሀ. አጥንትና ሥጋ ነበረው /ሉቃስ 24፡39/።

ለ. የከበረ አካል ነበረ /ፊልጵስዩስ 3፡21/።

ሐ. የማይበሰብስና የማይሞት አካል ነበረው /ሮሜ 6፡9/።

መ. መንፈሳዊ አካል ነበር /1ቆሮንቶስ 15፡44/።

**ማጠቃለያ**፡- ዛሬ በጣም የሚፈራ ነገር ቢኖር ሞት ነው። የትንሣኤው ኃይል ከሞት ይበልጣል፤ ምክንያቱም የሞትንና የመቃብርን ኃይል ሙሉ በሙሉ ሰብሮታልና።

# አስተምህሮተ መንፈስ ቅዱስ

## ትምህርት 12፡- የመንፈስ ቅዱስ ማንነት

መንፈስ ቅዱስ ማንነት አለው የምንለው ለምንድነው? ምክንያቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡

1. መጽሐፍ ቅዱስ መንፈስ ቅዱስን በማንነቱ ይጠቅሰዋል /ዮሐንስ 16፡7-8፣ 13-15/፡፡ በግሪኩ "እሱ" ተብሎ በመደብ ተጠርቷል /ዮሐንስ 15፡26/፡፡
2. የማንነት ባህሪ መያዙ

ሀ. ሃይል ይሰጣል /1ቆሮንቶስ 12፡1/

ለ. አዋቂነቱ /ነህምያ 9፡20 እና ሮሜ 8፡27/

ሐ. ጥበቡ /1ኛ ቆሮንቶስ 2፡10-12/

መ. ኃይሉ /ሐዋሪያት ሥራ 1፡8/

ሠ. መውደዱ /ሮሜ 15፡30/

ረ. ማዘኑ /ኤፌሶን 4፡30/

3. ማንነት ያለው አካል የሚሠራውን በመስራቱ

ሀ. የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር መመርመር /1ኛ ቆሮንቶስ 2፡10/

ለ. መናገር /ራዕይ 2፡7/፣ መጮህ /ገላትያ 4፡6/

ሐ. መቃተት /መማለድ/ /ሮሜ 8፡26/

መ. መመስከር /ዮሐንስ 15፡26/፣ ማስተማር /ዮሐንስ 14፡25፣ ዮሐንስ 16፡12-14

ሠ. መምራት /ሮሜ 8፡14/

ረ. ማዘዝ /ሐዋሪያት ሥራ 16፡6-7/፣ አገልጋዮችን ለሥራ መጥራትና ማሰማራት /ሐዋሪያት ሥራ 13፡2/

እርሱ እውነተኛ አጽናኝ ነው /ዮሐንስ 14፡16/፡፡ በግሪኩ "ጰራቅሊጦስ" የሚለው "በአጠገብ የሚቆም" ማለት ነው፡፡ መንፈስ ቅዱስ አጋር ነው፡፡

***ማጠቃለያ፡-*** መንፈስ ቅዱስ አካል ነው፤ ምክንያቱም ያስባል፣ ያቅዳል፣ ይሰማዋል፣ ያውቃል፣ ይፈቅዳል፣ ይወዳል፣ ያዝናል፣ እንዲሁም አካል የሚያደርገውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

## ትምህርት 13፡- የመንፈስ ቅዱስ አምላክነት

*መንፈስ ቅዱስ ሁሉን ቻይ፣ ከአብ እና ከወልድ ጋር እኩል አምላክ ነው፡፡*

### 1. *መንፈስ ቅዱስ የመለኮት ባህሪያት አሉት*

*ሀ* ዘላለማዊ /ዕብራውያን 9፡14/

ለ በሁሉ *ሥፍራ መገኘት* /መዝ .139፡7-10/

ሐ ሁሉን ቻይ / ሉቃስ 1፡35 እና ዘፍጥረት 1፡27/

*መ* ሁሉን አዋቂ /1ቆሮንቶስ 2፡10-11/

*ሠ*. ቅዱስ /ሉቃስ 11፡13/

*ረ* እውነት /1ዮሐንስ 5፡6/

ሰ. ቅን /ነህምያ 9፡20/

ሸ. አጋር /2ቆሮንቶስ 13፡14/

### 2. *መንፈስ ቅዱስ አምላክ የሚያደርገውን ሁሉ ያደርጋል*

*ሀ*. መፍጠር /ኢዮብ 33፡4/

ለ. ማዳን /1ቆሮንቶስ 6፡11/ ማተም /ኤፌሶሰን 1፡13/

ሐ. ሕይወት *መስጠት* /ዮሐንስ 6፡63/

*መ*. አዲስ ልደት ሰጪ / ዮሐንስ 3፡3-5/

*ሠ*. ትንቢት *መግለጥ* /2ኛ ጴጥሮስ 1፡21/

*ረ*. ሰዎችን ስለሚመጣው ድቅድቅ ጨለማና ፍርድ መውቀስ /ዮሐንስ 16፡8-11/

***የቤት ሥራ***፡- በብሉይ ኪዳን ስለመንፈስ ቀዱስ የሚናገሩ ጥቅሶችን ከላይ በተሰጡት ላይ ጨምር፡፡

## ትምህርት 14፡- የመንፈስ ቅዱስ ስምና ተምሳሌቶች

### 1. የመንፈስ ቅዱስ ስሞች

ሀ. መንፈስ ቅዱስ /ሉቃስ 11፡13/

ለ. የፀጋ መንፈስ /ዕብራውያን 10፡29/

ሐ የመቃጠል መንፈስ /ማቴዎስ 3፡11፣12 እና ኢሳይያስ 4፡4

መ የእውነት መንፈስ /ዮሐንስ 14፡17 ፣15 26፡16፡13 1ዮሐንስ 5፡6/

ሠ የህይወት መንፈስ /ሮሜ 8፡2/

ረ የእውቀትና የጥበብ መንፈስ /ኢሳይያስ 11፡2፣ 61፡1-2 ፣ሉቃስ 4፡8

ሰ. የተስፋ መንፈስ /ኤፌሶን 1፡13/

ሸ የክብር መንፈስ /1ጴጥሮስ 4፡14/

ቀ የእግዚአብሔር እና የክርስቶስ መንፈስ 1ቆሮንቶስ 3፡15፣ ሮሜ 8፡9/

ሸ. እፅናኝ /ዮሐንስ 14፡16/

### 2. የመንፈስ ቅዱስ ተምሣሌቶች

ሀ. ውሃ /ዮሐ 3፡5፣7፡38-39/፡- ውሃ ያሳድጋል፣ ያለመልማል፣ በነፃ ይሰጣል፣ የተትረፈረፈ ነው፡፡

ለ. እሳት /ማቴዎስ 3፡11 /፡- እሳት ያስወግዳል፣ ያቃጥላል፣ ያነፃል፣ ያነጥራል/

ሐ ንፋስ /ዮሐንስ 3፡8/፡- ንፋስ ሃይለኛ ነው፣ ያነቃቃል፣ ራሱን የቻለ ነው፣ የማይታይ ግን ውጤታማ ነው/

መ. ዘይት /መዝ 45፡7/፡- /ይቀድሣል፣ ያፅናናል፣ ያስወግዳል፣ ይፈውሣል/

ሠ. ዝናብና ጤዛ /መዝ. 72፡6/፡- ያድሣል፣ ያነፃል፣ የተትረፈረፈ ነው ፍሬን ይሰጣል

ረ እርግብ /ማቴዎስ 3፡16/

ሰ. ድምፅ /ኢሳይያስ 6፡8 /፡- ይመራል፣ ይናገራል፣ ያስጠነቅቃል

ሸ. ያትመናል /ራዕ 7፡2 እና ኤፌ 4፡30 /፡- ማረጋገጫና ከለላ ይሆናል

***ውይይት***፡- በእነዚህ ተምሳሌቶች የተገለጠው የመንፈስ ቅዱስ ሥራው ለአማኞች ጠቀሜታው ምንድነው /እንዴት ነው?

## ትምህርት15፦ መንፈስ ቅዱስ የማይወዳቸው ነገሮች

መንፈስ ቅዱስን የሚያበሳጩት ፈቃዱን በመጣስ በአማኞች ህይወት የሚሰሩ ነገሮች /ጥፋቶች/ ናቸው፡፡ ይህ ከአንዳንድ ምክንያቶች ጋር ሊያያዝ ይችላል፡፡ መንፈስ ቅዱስን የሚቃረን ወይም ፈቃዱን የሚጥስ ሥራ መሥራት ዋጋው እጅግ አስፈሪ /አስደንጋጭ/ ነው፡፡

1. **ባላመኑ ሰዎች የሚሰራ ጥፋት**

ሀ. መንፈስ ቅድስን መግፋት /ሐዋሪያት ሥራ 7፡51/

ለ. መንፈስ ቅዱስን መሳደብ /ዕብራውያን10፡29/

ሐ. መንፈስ ቅዱስ ላይ ማላገጥ /ማቴዎስ 12፡13-32/

2. **በአማኞች የሚሠራ ጥፋት**

ሀ. መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን /ኤፌሶን 4፡30-31/

ለ. መዋሸት /ሐዋሪያት ሥራ 5፡3-4/

ሐ. መንፈስን ማጥፋት /1ኛተሰሎንቄ 5፡19/

**ማጠቃለያ**፦ መንፈስ ቅዱስን መቋቋም ከዳግም መወለድ፤ መንፈስ ቅዱስን ማሳዘን ማደሪያው ከመሆን፤ መንፈስን ማጥፋትም ከመገኘቱ ጋር ይያያዛል፡፡

# አስተምህሮተ ሰው

## ትምህርት 16፦ የመጀመሪያው ሰው ሁኔታ

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሯል /ዘፍጥረት 1፡26 እና 9፡6/፡፡ አምሣል ማለት የአንድ ነገር ጥላ ወይ ነፀብራቅ ነው፡፡ መመሳሰል ከዋናው ነገር ጋር ያለውን መመሳሰል ያሳያል፡፡

1. የእግዚአብሔር አምሳል ማለት በአካል መመሳሰል አይደለም፤ እግዚአብሔር መንፈስ ነውና፡፡
2. የመጀመሪያው ሰው ብልህ ነበር፦ ለእንስሳት ሁሉ ስም ሰጥቷል፤ የመናገር፣ የመጠየቅ እና የማሰብ አቅምም ነበረው /ዘፍጥረት 2፡19 -20/
3. ሰው ሥነ-ምግባራዊነትንና መንፈሳዊነትን የተላበሰ ነው፡፡

**ውይይት**፦ ከውድቀት በፊት የነበረው ህይወት ከዛሬ ጋር ሲታይ እንዴት ይመስላል?

## ትምህርት 17፡- የሰው ውድቀት

የሰው ውድቀት በክርስትናም ሆነ በሌሎች ኃይማኖቶች ተጠቅሷል፡፡ ዘፍጥረት ሶስት የተዘበራረቀ የሰውን ታሪክ ሙሉ ሐሳብ ይሰጠናል፡፡ ታሪኩ ገና ኃጢአት ወደ አለም መግባቱን አይናገርም፤ ምክንያቱም ሰይጣን ቀድሞ ኃጢአት ሰርቶ ከሰማይ ወድቋልና /ሕዝቄል 28፡12-15 እና ኢሳይያስ 14፡9-14/፡፡ ታሪኩ የሚናገረው ኃጢአት እንዴት ወደ ሰው ዘር ገብቶ እኛን ኃጢአተኞች እንደዳረገን ነው፡፡

**1. የውድቀት ወኪል /ዘፍጥረት 3፡1/**

ሀ. ሰይጣን በአካል አልቀረበም ፤ ነገር ግን በእባብ ተመሰለ፡፡

ለ. በሕብረት ውስጥ ጥንካሬ እንዳለ አውቆ አዳምና ሔዋን በተለያዩ ሰዓት አጠቃቸው፡፡

ሐ. ጥቃቱንም በአመጋገብ /የምግብ ፍላጎት/ እና በእውቀት በኩል አደረገ፤ ነገር ግን አልተከላከሉም፡፡

**2. ለውድቀት የመሩ ሁኔታዎች**

ሀ. ሔዋን በዛፋ አጠገብ ነበረች /ከፈተናው ቦታ መራቅ ነበረባት/፡፡

ለ. የተከለከለውን ነገር ታደንቅ ነበር፡፡

ሐ. ከሰይጣን ጋር መነጋገሯ፡፡

መ. አትንኩ ፤ ብትነኩ ሞትን ትሞታላችሁ የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል አቃለለች፡፡

**ውይይት**፡- በዛሬው ዘመን ሰይጣን ሰዎችን የሚፈተንበት መንገድ /ዘዴው/ ምንድነው? ወዲያው ይሸነፋሉ ወይስ ባሉበት ፀንተው ይቆማሉ?

## ትምህርት 18 ፡- የውድቀት ውጤቶች

**1. ፈጣን ውጤት**

ሀ. ኃጢአተኞች ሆኑ፤ መንፈሳዊነታቸው ሞተ /ኤፌሶን 2፡1/፡፡

ለ. አይኖቻቸው ተከፈቱ ፤ እራቁታቸው እንደነበሩም አወቁ፡፡

ሐ. በእግዚአብሔር መገኘት ተሰወሩ፤ ከኃጢአት በኃላ ማፈር፣ ከእግዚአብሔርም መለየት መጣ፡፡

**2. እግዚአብሔር መርገምን ተናገረ /ዘፍጥረት 3፡14-19/**

ሀ. በእባብ ላይ፡- ከምድር አውሬ ሁሉ ይልቅ የተረገመ እንዲሆን፡፡

ለ. በሴቲቱ ላይ፡- ሕመምና ስቃይ በመውለድ ጊዜ፡፡

ሐ. በሰው ላይ፡- ምድርም እሾህማና አሜከላ እንድትሆን፤ በወዙና በጥረቱ ሕይወቱን እንዲመራ፤ በሞት ወደ ተፈጠረበት አፈር መመለስ።

### 3. የመጨረሻ ውጤት

ሀ. ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኛ መሆኑ /ሮሜ 5፡12/።

ለ. ሁሉም አለም ከፍርድ በታች መግባቱ /ሮሜ 3፡19 /።

ሐ. ዳግም ያልተወለዱ ሰዎች የዲያብሎስ ልጆች እንጂ የእግዚአብሔር ልጆች አለመሆናቸው /ዮሐንስ 8፡44/።

መ. የሰው ሁሉ አዕምሮ በሰይጣን መታወሩ /2ኛ ቆሮንቶስ 4፡4/።

ሠ. የሰው ዘር በሙሉ በአዕምሮ ግብረገብ፣ በመንፈስ እና በአካል፣ ከኃጢአት የተነሣ መመረዙን /ኤፌሶን 4፡17-18 ፤ ሮሜ 7፡18/ ።

***ውይይት፡-*** ከሰው ውድቀት በኋላ እግዚአብሔር የማዳንና የመዋጀት ተስፋ ሰንቆ ነበር /ዘፍጥረት 3፡15/። ይህንንም እግዚአብሔር ከ4000 አመታት በኃላ በመወለዱ ፈፅሟል።

# አስተምህሮተ ድነት

## ትምህርት 19፡- ንስሐ

በመጽሐፍ ቅዱስ ከ100 ጊዜ በላይ የተጠቀሰው ንስሐ እጅግ ዋና ሐሳብ ነው።

### 1. ንስሐ ምንድነው

ሀ. አሉታዊ፡- ንስሐ ስለ ኃጢአት የንስሐ ስሜት ለኛ አድርጎ ወዲያው ወደ ኃጢአት መመለስ /እብራውያን 12፡17/። አስቆሮቱ ይሁዳ እና ኤሳው ስለ ኃጢአታቸው አዝነው በቋሚነት መመለስ ያቃታቸው ናቸው።

ለ. አዎንታዊ፡- ሙሉ በሙሉ የአዕምሮና የተግባር ለውጥ ማድረግ ነው ማቴዎስ 21፡28-32/

### 2. የንስሐ አስፈላጊነት

ሀ. ንስሐ መግባት የመጥምቁ ዮሐንስ ዋና ስብከት ነው /ማቴዎስ 3፡1-2/።

ለ. ኢየሱስ ክርስቶስም ስለ ንስሐ ሰብኳል /ማቴዎስ 4፡17/።

ሐ. ኢየሱስ ክርቶስ ደቀ-መዛሙርቱን ንስሐ ስለ መግባት እንዲሰብኩ አዟቸዋል። /ማርቆስ 6፡12/።

*መ*. ከጴንጤቆስጤ በኋላ *ሐዋሪያት* ስለ ንስሐ ሰብከዋል /*ሐዋሪያት ሥራ* 2፡38 እና 20፡21/፡፡

*ሠ*. ሁሉም ንስሐ እንዲገቡ የእግዚአብሔር ፍላጎት ነው /2ኛ ጴጥሮስ 3፡9/፡፡

*ረ*. እግዚአብሔርን አለመታዘዝ፣ ከዘላለም ጉዳይ *ጋር* ይያያዛል /ሉቃስ 13፡3/፡፡

**3. የንስሐ ውጤት**

*ሀ*. በሰማይ ደስታ ይሆናል /ሉቃስ 15፡7-10/፡፡

ለ. ስለ ኃጢአት ይቅርታ መተውን ያመጣል /ኢሳይያስ 55፡7፣ *ሐዋሪያት ሥራ* 3፡19/፡፡

ሐ. መንፈስ ቅዱስ ንስሐ በገባው ሰው ላይ ይመጣል /*ሐዋሪያት ሥራ* 2፡38/፡፡

***የቤት ሥራ*፡-** ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች በመጠቀም በንስሐ ላይ አንድ የስብከት መርሐ ግብር አዘጋጅ ፡፡

## ትምህርት 20፡- እምነት

አማኞች በእምነት ስለዳኑ "እምነት" ወሳኝ ነገር ነው /ኤፌሶን 2፡8/፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰዎች *ጋር* ንግግር ካደረገ እና ከፈውሳቸው በኋላ እምነታቸውን ይጠብቅ ነበር፡፡

**1. የእምነት ምሳሌዎችን ታስታውሳለህ?**

*ሀ*. የስሮፊንቃዊት ሴት ያሳያቸው እምነት /ማርቆስ 7፡26/

ለ. መቶ አለቃው የተገኘበት የትህትና እምነት /ማቴዎስ 8፡8-10/

ሐ. አይነስውሩ ያሳየው ቅንነት የሞላበት እምነት /ማርቆስ 10፡50/

**2. የእምነት ትንታኔ /እምነት ምንድነው? /**

*ሀ*. እምነት፣ ማመን፣ መደገፍ እና ታማኝነት ነው /እብራውያን 11፡1/፡፡ እምነት የሚያድነው በክርስቶስ ኢየሱስ በመደገፍ ብቻ ነው፡፡

ለ. ስለ መዳን ሁለት አይነት እምነት አለ

○ ***የአዕምሮ እምነት፡-*** ስለ ክርስቶስ እውቀት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ተቀባይነት፡፡

○ ***የልብ እምነት፡-*** አንድ ሰው በልቡ ያመነውን እንዲያደርግ የሚረዳ እምነት ነው፡፡ በክርስቶስ የማመን እምነት እርሱን ወደ መቀበል የሚያደርስ ማለት ነው /ዮሐንስ 1፡12 እና ቆላስይስ 2፡6/ ፡፡ እውቀት ወይም ስምምነት እውነተኛ እምነት ሊሆን አይችልም፤ እውነተኛ እምነት ትክክለኛነትን ያካትታልና!

### 3. የእምነት ውጤቶች

ሀ. በእምነት ድነናል /ዘፍጥረት 15፡6፤ሮሜ 5፡1፣ ገላትያ 3፡26/

ለ. በእምነት ተቀድሰናል /ሐዋሪያት ሥራ 26፡18/

ሐ. እረፍት፣ ሰላም፣ ማረጋገጫ እና ደስታ የሚመጣው በእምነት /ኢሳይያስ 26፡3፣ ፊልሞና 4፡6፣ ዕብራውያን 4፡1-3፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡5/

መ. በእምነት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ሆነናል /ዕብራውያን 11፡33-40፣ ማቴዎስ 21፡21፣ ዮሐንስ 14፡12/

***ውይይት፡-*** የአእምሮና የልብ እምነት የምታውቀውን ምሳሌ ስጥ፡፡

## ትምህርት 21፡ ትንሣኤ ወይም አዲስ ልደት

በክርስቶስ በኩል አዲስ ከመወለድ ሌላ ክርስቲያን የሚያደርገን ሌላ መንገድ የለም፡፡

### 1. አዲስ ልደት /ዳግም ልደት/ ምንድነው

ሀ. መጠመቅ አይደለም፤ መጠመቅ አንዴ ያመነውን ሰው በቤተክርስቱያን የሚፈፅም ተግባር ነው፡፡

ለ. መለወጥ አይደለም፤ መለወጥ ማለት ከኃጢአት መንገድ የመመለስ የአማኞች ተግባር ነው፡፡ አዲስ ልደት ማለት መንፈሳዊ፣ ፈጣን፣ በመለኮታዊ ተግባር የሚከናወን ነው፡፡

ሐ. አዲስ ልደት /አዲስ ፍጥረት/ ሆኖ መወለድን የሚያመጣ መንፈሳዊ ድርጊት ነው /2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17 እና ኤፌሶን 2፡1/፡፡

### 2. የአዲስ መወለድ አስፈላጊነት

ሀ. ሁሉም ሰው ደግም መወለድ አለበት፤ ምርጫ ስለሌለ! /ዮሐንስ 3፡3–7፣ ገላትያ 6፡15/፡፡

ለ. የሰው የኃጢአተኝነት ባህሪይ ደግም እንዲወለድ ያስፈልገዋል /ዮሐንስ 3፡6 ኤርሚያስ 13፡23፣ ሮሜ 7፡18 እና 8፡8/፡፡

ሐ. የእግዚአብሔር ቅድስና ሰው ዳግም እንዲወለድ ያደርገዋል /ዕብራውያን 12፡14/፡፡

3. **የዳግም መወለድ መንገዶች**

ሀ. ዳግም መወለድ የመለኮት ሥራ ነው /ዮሐንስ 1፡13 ፣ ቲቶ 3፡5፣ ዮሐንስ 3፡5/፡፡

ለ. የሰው ምላሽ /ዮሐንስ 1፡12–13/ የመለኮትና የሰው ድርሻ የሚለውን ሐሳብ ያቀርባል፡፡ ሁለቱም በዳግም መወለድ ሚና አላቸው፡፡ የተቀበሉት ሁሉ ዳግም የተወለዱ የእግዚአብሔር ልጆች የሚባሉ ናቸው፡፡

***ማጠቃለያ፡–*** ሰው የወንጌልን መልእክት በመቀበል ዳግም መወለድ ወይም በግሉ ክርስቶስ መቀበል ይችላል /1ኛ ቆሮንቶስ 4፡15፣ ቆላስይስ 1፡18፣ 1ኛ ጴጥሮስ 1፡23፣ ዮሐንስ 1፡12–13 እና ገላ 3፡26/፡፡

## ትምህርት 22፡- መጽደቅ

1. **ትርጓሜ**

ሰው ከእግዚአሔር ጋር ያለውን ሕብረት ወይም አቋም መቀየር ነው፡፡ ዳግም ልደት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ያለውን አቋም ከመጽደቁ የተነሣ ተቀባይነት አለው፡፡ ከይቅርታ ያለፈ ፀድቀሃል ማለት ቅድስናን ማወጅ ማለት ነው፡፡

መጽደቅ ማለት አይሁዶች ከእግዚአብሔር ፊት ያላቸው ተግባር ሲሆን፣ ለአማኞች በክርስቶስ በማመን በኩል ከእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትን ማግኘት ከኃጢአተኝነትና በደለኝነት ነፃ መሆን ማለት ነው፡፡

2. **መጽደቅ ሁለት ነገሮችን ያካትታል**

ሀ· የኃጢአት ይቅርታ፣ የሁሉም በደለኝነት እና ቅጣት መወገድ /ሚኪያስ 7፡18–19፣ ሐዋሪያት ሥራ 13፡38፣ ሮሜ 8፡1፡33–34/ ፡፡

ለ· የክርስቶስን ቅድስና በማስገባት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ማደስና ተቀባይነት ማግኘት 2ኛ ዜና 20፡7፣ ያዕቆብ 2፡23 ሮሜ 5፡17–21/፡፡

3· **የመጽደቅ መንገዶች**

ሀ. አሉታዊ፡– በሕግ ሥራ አይደለም /ሮሜ 3፡20፣ 28፣ ገላ. 2፡16፣ 3፡10

ለ. አዎንታዊ፡- በአግዚአብሔር ፀጋ /ሮሜ 3፡24/

ሐ. በክርስቶስ ደም፡- የፅድቅ ፀጋ /ሮሜ 3፡24፤ 5፡9፡ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡21፣ እብራውያን 9፡22/፡፡

መ. በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን፡- የመጽደቅ ቅድመ ሁኔታ /ገላትያ 2፡16 ሮሜ 3፡26፤ ገላትያ 3፡10፣ ሐዋሪያት ሥራ 13፡39/፡፡

***ውይይት፡-*** ጽድቅ ከይቅርታ እንዴት ይለያል?

## ትምህርት 23፡- ጉዲፈቻ

### 1. የጉዲፈች ትርጓሜ

"ጉዲፈቻ" ማለት "በልጅ ቦታ" የሚተገበር የሮማውያን ሕጋዊ ቃል ነው፡፡ ይህ ማለት የሌላን ሰው ልጅ እንደ ራስ ልጅ አድርጎ መውሰድ ማለት ነው፡፡ የተወሰደው ልጀ ከተወለደው ልጅ እኩል ቅቡልነትና ድርሻ እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ /ገላትያ 4፡5፤ ሮሜ 8፡15፤23፣ ሮሜ 9፡4፣ ኤፌሶን 1፡5/፡ ዘጸአት 2፡10 እና እብራውያን 11፡24 ሁለት መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጉዲፈቻ ምሳሌዎች ምንነትን ያሳዩናል፡፡

### 2. የጉዲፈቻ በረከቶች

እኛ በእግዚአብሔር የተወደድን /ዮሐንስ 17፡23/ እና አምላካዊ ጥበቃው ያለን ነን /ሉቃስ 12፡27–33/፡፡ ቤተሰባዊ ስም /1ኛ ዮሐንስ 3፡1፤ ኤፌሶን 3፡14–15/ የቤተሰብ መልክ /ሮሜ 8፡29/፣ የቤተሰብ ፍቅር /ዮሐንስ 13፡35፤ 1ኛ ዮሐ 3፡15/፣ የአባትና ልጅ መንፈስ /ገላትያ 4፡6/ እና የቤተሰብ አገልግሎት አለን /ዮሐንስ 14፡23–24፣15፡8/፡፡

አባታዊ ተግሳጽንም እንቀበላለን /ዕብራውያን 12፡5–11/፣ አባታዊ ማጽናናት አለን /ኢሳይያስ 66፡13፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡4/፣ ወራሾችም ነን /1ኛ ጴጥ 1፡3–5፤ ሮሜ 8፡17/፡፡

### 3. የልጅነት ማስረጃ

ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ የመጡ የጉዲፈቻ ልጀች፡-

ሀ በመንፈስ ይመራሉ /ሮሜ 8፡4፤ ገላትያ 5፡18/

ለ እንደ ልጅ በእግዚአብሔር ይታመናሉ /ገላትያ 4፡5–6/

ሐ ወደ እግዚአብሔር በነፃነት ይቀርባሉ /ኤፌሶን 3፡12/

መ የወንድሞች ፍቅር አላቸው /1ዮሐንስ 2፡9–11፤5፡2/

ሠ ታዛዥች ናቸው /1ዮሐንስ 5፡1–3/

***ውይይት***፡– የእግዚአብሔር ልጅ መሆንና የእግዚአብሔር አገልጋይ መሆን ልዩነቱ ምንድ ነው?

## ትምህርት 24፡- መቀደስ

መቀደስ ከእኛ ባህሪይ ተግባር ጋር ይገናኛል። መጽደቅ ግን እግዚአብሔር ለኛ ያደረገው ተግባር ነው። ሆኖም መቀደስንም በእኛ የሚሰራ እግዚአብሔር ነው።

### 1. ትርጓሜው

በትርጓሜው ውስጥ ሁለት ሐሳብ አለ፡-

ሀ. ከክፉት መለየት፡- /2ኛ ዜና 29፡5፣ 15-18፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡3/። መቀደስ ነፍስንና ስጋን ከሚያጎድፍ ኃጢአት ሁሉ መራቅ /መለየት/ ነው።

ለ. ለእግዚአብሔር መለየት፡- /ዘኅልቁ 27፡14-16፣ ናሆም 8፡17፣ ዮሐንስ 10፡36/። ምንም ነገር ለእግዚአብሔር የተለየ ከሆነ መቀደስ ይባላል /እግዚአብሔር የተጠቀመበት/ ሕዝቅኤል 36፡23/።

### 2. የመቀደስ ጊዜ

መቀደስ ያለፈ፣ የአሁኑና የሚመጣው ወይም ወዲያው የሚሆን ሂደታዊ ፍጻሜ ነው።

- ወዲያው የሚሆን /1ኛ ቆሮንቶስ 6፡11፣ ዕብራውያን 10፡10፣14/፡- በክርስቶስ በማመን ብቻ ወዲያው ከክርስቶስ የተነሳ በጽድቅ ቦታ ሊሆን ይችላል።
- ሂደታዊ /2ኛ ጴጥሮስ 3፡18፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 3፡18፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 3፡12/፡- ዕለት ዕለት ከአንዱ ክብር ወደ ሌላው የምናድግበት ደረጃ ማለት ነው።
- የሚፈጸም የመጨረሻው መቀደስ /1ኛ ተሰሎንቄ 5፡23፣ 3፡13/

### 3. የመቀደስ መንገዶች

የመለኮትና የሰው ድርሻ ናቸው። መቀደስ እንዲከናወን ሰውም እግዚአብሔርም ይተባበራሉ።

- ከመለኮት በኩል፡- የሥላሴ ስራ ነው ፡-

- አብ አባት /1ኛ ተሰሎንቄ 5፡23-24፣ ዮሐንስ 17፡17/
- ኢየሱስ ክርስቶስ /እብራውያን 10፡10፣ኤፌሶን 5፡25፣27፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30
- መንፈስ ቅዱስ /1ኛ ጴጥሮስ 1፡2፣2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13/
- በሰው በኩል፡- በክርስቶስ የመዋጀት ሥራ ማመን፡- በዋናነት የማይረሳ ነገ ሰው በደረሰበት ደረጃ የሚያግዝ የኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና የተቀደሰ ሕይወት ይደመራሉ። እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና በቃሉም መታዘዝ /ዮሐንስ 17፡17፣ ኤፌሶን 5፡76፣ ዮሐንስ 15፡3/

***ውይይት፡-*** *በመቀደስ ሂደት ያለው የጊዜ ሁኔታ እያንዳንዱን ደረጃ ተወያዩ።*

## ትምህርት 25፡- ፀሎት

ፀሎት የክርስቲያን እስትንፋስ ስለሆነ፣ ያለፀሎት የክርስትናን ሕይወት መግፋት አይቻልም።

### 1. የፀሎት አስፈላጊነት

ሀ አለመፀለይ ጌታን ያሳዝነዋል /ኢሳይያስ 43፡21–22፣ 64፡6–7/።

ለ ብዙ ክፉ ነገሮች ወደ እኛ የሚመጡት ከፀሎት እጥረት የተነሣ ነው / ሶፎንያስ 1፡4–6 ዳንኤል 9፡13–14/።

ሐ ፀሎትን መጥላት ኃጢአት ነው /1ሳሙኤል 12፡23/።

መ ሁል ጊዜ መፀለይ ትዕዛዝ ነው /ቆላስይስ 4፡2 ፣1ኛ ተሰሎንቄ 5፡17/።

ሠ ፀሎት ከእግዚአብሔር የፀጋ ስጦታን የምንቀበልበት አምላካዊ መንገድ ነው /ዳንኤል 9፡3፣ ማቴዎስ 7፡17፣ 9፡24 –29 ሉቃስ 11፡13/።

ረ ሐዋሪያት በሁሉም አገልግሎታቸው ውስጥ ፀሎት ቦታ ነበረው /ሐዋሪያት ሥራ 6፡4 እና ሮሜ 1፡9/

### 2. እንዴት እንፀልይ

ጸሎት ቢያንስ አራት ነገሮችን የያዘ መሆን አለበት፡- “ተግባር” የሚለውን ቃል አስቡ ⁄ACTS⁄፡-

A = Adoration ⁄ማድነቅ⁄: - እግዚአብሔርን ማምለክና ማመስገን /መዝ. 95፡6/

C= Confession /ንስሐ መግባት/:- ከማናቸውም ኃጢአቶች መናዘዝ /መመለስ/ /መዝ. 32፡5/

T= Thanksgiving /ማመስገን/:- አመስጋኝ መሆን /ፊልጵስዩስ 4፡6/

S= Supplicaton /መማለድ/:- መማለድ፣ መጠየቅ፣ መለመን፣ መፈለግ/ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1/

**3.የፀሎት እንቅፋቶች**

ሀ አለማመን /ያዕቆብ 1፡6–7/

ለ ይቅርታ አለማድረግ /ማርቆስ 11፡25/

ሐ ታማኝ አለመሆን /መዝሙር 66፡18/

መ ጉድለትን መጠየቅ /ያዕቆብ 4፡3/

**4· የፀሎት ተስፋዎች**

ማርቆስ 11፡24፣ ዮሐንስ 15፡17፣ 1ኛዮሐንስ 5፡14–15፣ ኤፌሶን 3፡12፣ ፊልጵስዮስ 4፡19፣ ፊልጵስዩስ 4፡6፣ ማቴዎስ 7፡7–8፣ ሉቃስ 11፡9–13፣ እብራውያን 4፡16፡፡

***ውይይት፦*** በቅርቡ ፀልየህ የተመለሰልህ ነገር ምንድነው? አሁን ስለምን ትፀልያለህ?

# አስተምህሮተ ቤተክርስቲያን

## ትምህርት 26፡- ትርጓሜና የቤተክርስቲያን አመሠራረት

በዚህ አለም የእግዚአብሔር ትልቁ አላማ የቤተክርስቲያን አንድነት ነው፡፡

**1 የቤተክርስቲያን ትርጓሜ**

ሀ· ቤተክርስቲያን የአዲስ ኪዳን ተቋም ሆኖ በጴንጤቆስጤ ተወልዳለች፡፡ ምናልባትም የሚያበቃው በመነጠቅ ወይም በክርስቶስ ዳግሞ መመለስ ይሆናል፡፡

ለ· ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል" ኤክሊሺያ" ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ሲሆን፣ ትርጓሜውም" ስብስብ" ማለት ነው፡፡ በክርስቶስ የሆኑ አማኞች የሚሰበሰቡበት ቤተክርስቲያን ተብሏል /1ኛ ቆሮንቶስ 1፡2/፡፡

ሐ. ቤተክርስቲያን የሚለው ቃል የአንድ አካባቢ አማኞች ህብረትን ያካተተ ነው /ቆላስዩስ 4፡15/፡፡

መ. ቤተክርስቲያን አለምአቀፋዊ /በሁለም ቦታ ያሉ አማኞችን የምታጠቃልል /ናት/ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡9/፡፡

ሠ. በምድር ላይ ያለችው የምትታየው ቤተክርስቲያን ያቀፈችው የዳኑትንና ስማቸው በበጉ መጽሐፍ የተፃፉትን ብቻ ነው /ራዕይ 21፡27/፡፡

ረ. የቤተክርስቲያን ሠራዊት የቤተክርስቲያን አባልነትን ያሳያል፤ የቤተክርስቲያን አሸናፊነት በሰማያዊ ሥፍራ ያለችውን ቤተክርስቲያን አመልካች ነው፡፡

## 2 ቤተክርስቲያን አመሠራረት

ቤቤተክርስቲያን በጴጥሮስ ስብከት በክርስቶስ ላይ የተመሠረተች ናት /ማቴዎስ 16፡16–18/፡፡ "ኢየሱስ ክርስቶስ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነው" በሚለው የእምነት መሠረት ላይ ነው የተመሰረተችው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የመሠረተው በጴጥሮስ ላይ ሳይሆን፣ በጴጥሮስ በኩል በተመሠከረው እውነተኛ አዋጅ /ቃል/ ላይ ነው፡፡

በታሪክ ቤተክርስቲያን የተመሠረተችው በጴንጤቆስጤ /ሐዋሪያት ሥራ 2/ መንፈስ ቅዱስ ከመጣ በኂላ ነው /ሐዋሪያት ሥራ 2፡47፣ 1፡13፣ 5፡12፣ 2፡46፣ 12፣12/፡፡

***ውይይት***፦ የቤተክርስቲያን የተለያዩ ትርጓሜዎች ምንድናቸው?

# ትምህርት 27፡- አባልነት እና የቤተክርስቲያን ዓላማ

## 1 የቤተክርስቲያን አባል መሆን ቅድመ ሁኔታዎች

ሀ ንስሐ መግባት /ሐዋሪያት ሥራ 2፡38/

ለ ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታ፣ አዳኝና የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ማመን/ ማቴዎስ 16፡16–18/፡፡

ሐ ደኅንነት፣ መለወጥ እና ዳግም ልደት /ሐዋሪያት ሥራ 2፡47/፡፡

መ በአብ፣ በወልድ፣ በመንፈስ ቅዱስ ስም መጠመቅ /ሐዋሪያት ሥራ 2፡38/፡፡

ሠ በሐዋሪያት ትምህርት መኖር /ሐዋሪያት ሥራ 2፡42/፡፡

## 2 የቤተክርስቲያን ዓለማ

ሀ. ክርስቶስን ለማምለክና በምድር ለማክበር /ኤፌሶን 1፡46/፡፡

ለ. አለምን በወንጌል ለመድረስ /ማቴዎስ 28፡19–20፣ ማርቆስ 16፡15/፡፡

ሐ. አማኞችን ለማረምና ለማስተማር /ኤፌሶን 4፡11–15፤ 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡11፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 12፡1/፡፡

መ. በቋሚነት ለመመስከር /ሐዋሪያት ሥራ 1፡8/፡፡

***ውይይት***፡፡-ስለ ቤተክርስቲያን አባልነት እየተስተዋሉ ያሉ ችግሮች ምንድናቸው?

## ትምህርት 28፡- ምልክትና የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች

### 1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የቤተክርስቲያን ምልክት

- አአካል፡- ክርስቶስ ራስ ነው፣ እኛ የአካሉ ብልቶች ነን /ቆላስዩስ 1፡18፣ 1፡22–23፣ ቆላስዩስ 2፡19/፡፡
- መቀደስ፡- የእግዚአብሔር መንፈስ ማደሪያ /ኤፌሶን 2፡20/፤ ክርስቶስ የማዕዘኑ እራስ ነው፤ እኛ የመቅደሱ የተለያዩ ክፍሎች ነን፡፡
- የክርስቶስ ሙሽራ፡– ቤተክርስቲያን የክርሰቶስ ሙሽራ ናት /2ኛ ቆሮንቶስ 11፡2/፤ ክርስቶስ ሙሽራው ነው /ዮሐንስ 3፡29/፤ ሠርጉም በራዕ 19፡1 ላይ ተገልጿል፡፡

### 2. የቤተክርስቲያን ሥርዓቶች

**የቤተክስቲያን ስርዓቶች ሁለት ናቸው፡-**

ሀ ጥምቀት፡- ማቴዎስ 28፡19-20፣ ማርቆስ 16፡16፣ ሐዋሪያት ሥራ 2፡38-41፣ ሐዋሪያት ሥራ 8፡36-40፣ ሐዋሪያትሥ 10፡47-48

ለ) የጌታ ዕራት፡- ሐዋሪያት ሥራ 2፡42-46፣ 20፡7፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡20-34

***ውይይት***፡- ስለቤተክርስቲያን ሥርዓቶችና ምልክቶች የተጠቀሰውን መሰረት በማድረግ የቤተክርስቲያን አባል መሆን ምንነትን በትክክል አስረዳ፡፡

# አስተምህሮተ መጽሐፍ ቅድስ

## ትምህርት 29፡- የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት

### 1. የመጽሐፍ ቅዱስ አንዳንድ እውነታዎች

- መጽሐፍ ቅዱስ የ66 መጽሐፍት ጥርቅም /ስብስብ/ ነው፡፡ ይህም ብሉይ ኪዳን 39 እና አዲስ ኪዳን 27 ተብለው ይከፈላሉ፡፡
- መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈው ከ36 እስከ 40 በሚያህሉ ጸሐፊዎች፣ ከተለያየ ህዝብና አለም ከሆኑት በ1600 አመታት ጊዜ የተፃፈ ነው፡፡

- ብብሉይ ኪዳን መጀመሪያ የተፃፈው በእብራይስጥ ነው፤ በዳንኤል እና በዕዝራ ጊዜ ደግሞ በአራማይክ ተጽፏል።
- መጽሐፍ ቅዱስ በአለም ላይ የመጀመሪያ መጽሐፍ ነው። 16 ክፍለ ዘመናትን የፈጀ ነው፤ የመጀመሪያው ፀሐፊ የመጨረሻው ፀሐፊ ከመወለዱ 1450 ዓመታት ቀደም ብሎ ነው የሞተው።

2. እእስትንፋስ መለኮት /Inspiration/ ትርጓሜ

ሀ) በግሪክ" theopneustos" የእግዚአብሔር አስትንፋስ ማለት ነው።" theo" እግዚአብሔር፣" pneustos" ደግሞ እስትንፋስ ማለት ነው /2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16/።

ለ) የተቀደሱ የእግዚአብሔር ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ስር ሆነው የታዘዙትን ፅፈዋል፤ ከስህተትም ተጠብቀዋል።

3. እእስትንፋሰ መለኮት /Inspiartion /መጽሐፍ ቅዱስ ምስክርነት

- ፀሐፊዎቹ / 2ኛጴጥሮስ 1፡21/
- መጽሐፍቱ /2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16/
- ቃላቶቹ /1ኛ ቆሮንቶስ 2፡13፣ 2ኛ ጴጥሮስ/

***ውይይት፡-*** *ስለመጽሐፍ ቅዱስ በተነገረው የተለየና ልብህን የነካው የቱ ነው?*

## ትምህርት 30፡- ስለመጽሐፍ ቅዱስ ሁለት ሰባቶች

### 1. ስለመጽሐፍ ቅዱስ ሰባቱ ቁንጮ ተዓምራቶች

*ሀ* የአወቃቀሩ ተዐምር፡- አንድ መጽሐፍ አንድ ቦታ በአንድ ቋንቋ ተፃፈ፣ ሌላኛው በሌላ አገር ከክፍለ ዘመናት በኂላ በሌላ ቋንቋ መጻፉ።

ለ የልዩነቱ ተዐምር፡- የ66 መጽሐፍት ስብስብ ሆኖ አንድ ትልቅ መጽሐፍ መባሉ፤ ይህም ዋና ፀሐፊው መንፈስ ቅዱስ ሲሆን አለመቃረኑ ያስገርማል።

ሐ የዕድሜው ተዐምር፡- ከሁሉም መጽሐፍት ይልቅ ጥንታዊ /ቀዳሚ/ መሆኑ።

*መ* ተፈላጊነቱ፡- በሁሉም ዘመን በመምህራን፣ በልጆችና በሁሉም ትውልድ /የሰው ዘር/ ተፈላጊ መሆኑ

*ሠ* የሽያጭነቱ ተዓምር፡- ከመጽሐፍት ሁሉ የበለጠ የተሸጠ

ረ የቋንቋ ተዓምር፦- ባልተማሩ ሰዎች መፃፉ፣ በዚህም የሥነ-ጽሑፍ ቁንጮ መሆኑ

ሰ) የፅናቱ ተዓምር፦- ጊዜ፣ ነገሥታትና መንግሥታት አቃጥለው ከምድር ለማጥፋት ሞክረዋል። ሆኖም ግን እግዚአብሔር ለእኛ እንዲሆን በሁሉም ቤት እንዲገኝ አደረገው።

2. **በበእግዚአብሔር ቃል የተመሰሉ ሰባት ምልክቶች**

- ሰሰሚውን የሚያሳምን ሰይፍ /እብራውያን 4፡12/።
- የየሰሚውን ልብ የሚሰብር መዶሻ /ኤርሚያስ 23፡29/።
- ለለሰሚው ሕይወት የሚሰጥ ዘር /1ኛ ጴጥሮስ 1፡23/።
- ግለሰዎች የራሳቸውን ማንነት መልሶ የሚያሳይ መስተዋት /ያዕቆብ 1፡23–25/።
- በሰሚው ልብ ውስጥ ያለውን ቆሻሻ የምትበላ እሳት /ኤርሚያስ 20፡9፣ 23፡ እና 23፡29/።
- አአማኞችን በየቀኑ የሚመራ ብርሃን / መዝሙር 119፡105/።
- ነነፍስን የሚያጠግብ መንፈሳዊ ምግብ /1ኛ ጴጥሮስ 2፡2፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 3፡2፣ ሮሜ 10፡17/።

***የቤት ሥራ፡*** የእግዚአብሔር ቃል ምልክት ከሆኑት አንዱን በመጠቀም አንድ ጠቃሚ ትምህርት አዘጋጅ።

## ትምህርት 31፡- የእግዚአብሔር ቃል ለምን ይሰበካል?

- ስለ ኃጢአት ይወቅሳል፡– በእግዚአብሔር ቃል ስለሚመጣ ሐዋሪያት ሥራ 2፡14 ከጴጥሮስ ስብከት በአብዛኛው የብሉይ ኪዳን ቃል ነው።
- እምነት የሚገኘው ቃሉን በመስማት ስለሆነ /ሮሜ 10፡17/።
- መንፃት የሚገኘው በቃሉ ነው /2ኛቆሮንቶስ 7፡1/፤ ተስፋውም ቃሉ ነው።
- ማረጋገጫ የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል ነው /1ዮሐንስ 5፡13/።
- መጽናናት የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል ነው /1ኛተሰሎንቄ 4፡18/። ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፉ ቃላት ናቸው።

- እውነት የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ነው /ሐዋሪያት ሥራ 17፡11/
- ዳግም መወለድ የሚመጣው ከእግዚአብሔር ቃል ነው /1ኛ ጴጥሮስ 1፡23/
- እውነት የሚገኘው በእግዚአብሔር ቃል ነው /ሐዋሪያት ሥራ 17፡11/
- ዳግም መወለድ ከእግዚአብሔር ቃል ዘንድ ነው /1ጴጥሮስ 1፡23/

***ማጠቃለያ፡-*** ከክርስቶስ እና ከመንፈስ ቅዱስ ቀጥሎ መጽሐፍ ቅዱስ ለአለም የተሰጠ ትልቁ ስጦታ ነው፡፡

## አስተምህሮተ መላእክት

## ትምህርት 32፡- መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት ምን ይላል?

### 1. ስለመኖራቸው

*ሀ* “*መላእክት*” *የሚለው ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሰው* ዘፍጥረት 16፡7 ላይ አጋር ከሣራ ቤት ተሰዳ በወጣች ጊዜ ይረዳት በነበረት *ሥፍራ* ነው፡፡

ለ. በብሉይ ኪዳን ብዙ ማጣቀሻዎች ስለመላእክት ተጽፈዋል /*መዝሙር* 104፡4፣ *ዳንኤል* 10፡12-13፣ 2ኛ ሳሙኤል 14፡20፣ *መዝሙር* 103፡20፣ 2ኛ *ነገስት* 19፡35፣ 2ኛ ሳሙኤል 24፡15-16/፡፡

ሐ. ኢየሱስ ክርስቶስ በመኖራቸው *ያምናል* /*ማቴዎስ* 18፡10፣ ማርቆስ 13፡32 እና 8፡*ማቴዎስ* 13፡41 እና 26፡53/፡፡

*መ*. ጳውሎስና ሌሎች ሐዋሪያት በመላእክት *ያምናሉ* /2ኛ ተሰሎንቄ 1፡17 ቆላስዩስ 2፡18፣ ዮሐንስ 1፡51፣ *ራዕይ* 12፡7 ፣22፡9 ፣1ኛ ጴጥሮስ 3፡22 ፣1ኛ ጴጥሮስ 2፡11፣ *ይሁዳ* 9/፡፡

### 2. የመላእክት አፈጣጠር

- የተፈጠሩ ናቸው፣ የተጣሉቱ ግን አይደሉም /ቆላስይስ 1፡16/
- *መንፈስ* ናቸው /*መዝ*. 104፡4/፤ አንዳንድ ጊዜ ግን በአካል ታይተዋል /ዘፍጥረት 19፣ *መሳፍንት* 2፡1፣6፡11-12፣ *ማቴዎስ* 1፡20፣ ዮሐንስ 20፡12/
- ጠንካሮች ናቸው /*መዝሙር* 103፡20፣ 2ኛ *ነገስት* 19፡35፣ 2ኛ ሳሙኤል 24፡15-16/

- *ሥጋ የላቸውም* /*ሉቃስ* 20፡35-36/
- *አይቆጠሩም* /*ራዕይ* 5፡11፣ *ዕብ* 12፡22፣ *ማቴዎስ* 26፡53/

3. **የወደቁ መላእክት**

በመጀመሪያ ሁሉም መላእክት መልካም ሆነው ተፈጥረዋል፡፡ በ2ኛ ጴጥሮስ 2 ፡45 እና ይሁዳ 6 ላይ የተወሰኑት ወድቀዋል፤ የመውደቃቸው ምክንያት ባይታወቅም ምናልባት በትዕቢት፣ አለመታዘዝና የሰይጣን ውድቀት ይሆናል /ሕዝቄል 28/፡፡

***ውይይት***፡- ስለ ሰይጣን ውድቀት የተፃፈውን ምዕራፍ በማንበብ ምክንያቶቹን ተወያዩበት፡፡

## ትምህርት 33፡- የመላእክት ሥራ

1. **የወደቁ መላእክት ሥራቸው**

*ሀ*. የእግዚአብሔርን ዓላማ መቃረን /ዳንኤል 10፡101-14/፡፡

*ለ*. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ማንቃት /ሉቃስ 13፡16፣ ማቴዎስ 17፡15-18/፡፡

*ሐ*. የሰይጣንን ዓላማ ያካሂዳሉ /ማቴዎስ 25፡41፣ 12፡41፣ 12፡26-27/፡፡

*መ*. ለእግዚአብሔር ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት እንቅፋት ይሆናሉ /ኤፌሶን 6፡12/፡፡

*ሠ*. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማሳት ይጥራሉ /1ኛ ሳሙኤል 28፡7-20/፡፡ የመዳን ተስፋ የላቸውም /ይሁዳ 6፡2፣ 2ኛ ጴጥሮስ 2፡4፣ ማቴዎስ 25፡41/፣ ለዘላለም በጨለማ እሳት ይሰቃያሉ፡፡

2. **የመላእክት ሥራ**

*ሀ*. በሰማይ እግዚአብሔርን ያከብራሉ፣ ያመልካሉ፣ ያገለግላሉ /ራዕይ 5፡11-12፣ 8፡3-4/፡፡

*ለ*. በምድር ላይ የጌታን መልዕክት ያስተላልፋሉ፡፡ ለአጋር ምንጭ አሳይተዋል፣ ሠይፍ ይዘው በኢያሱ ፊት ተገልጠዋል፣ ከጴጥሮስ እጅ ሠንሠለት ፈትተዋል፣ የእሥር ቤት በር ከፍተዋል፣ መግበዋል፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ አበረታተዋል፣ ጠብቀዋልም፣ ወዘተ

*ሐ*. የእግዚአብሔርን አላማና ፍርዱን ይተገብራሉ /ናሆም 22፡22፣ ሐዋሪያት ሥራ 12፡23፣ ማቴዎስ 13፡41/፡፡

*መ*. አማኞችን ይመራሉ /ሐዋሪያት ሥራ 8፡26/፡፡

ሠ. ቅዱሣንን መርዳት፣ መጠበቅ እና ማበረታታት፤ ኤልያስን /1ኛ ነገስት 19/፣ ዳንኤል /6፡22/፣ ኢየሱስ ክርስቶስን በጌተሠማኒ /ማቴዎስ 4፡11/ አበረታተዋል።

ረ. ጌታ ኢየሱስ ዳግም ተመልሶ ሲመጣ ያጅቡታል/ ማቴዎስ 25፡31፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡7-8/።

ሰ. አማኞች በሚሞቱበት ጊዜ ወደ ሰማይ ይወስዷቸዋል /ሉቃስ 16፡22/።

***ውይይት***፡- የመላእክትን እርዳታ በሕይወትህ አይተህ ታውቃለህ?

# አስተምህሮተ ሰይጣን

## ትምህርት 34፡- የእግዚአብሔርና የሰው ትልቁ ጠላት

### 1. የሰይጣን መጀመሪያ

ሀ. በሕዝቂል 28፡12-19 ተጠቅሷል፤ በውበት የመጀመሪያ ነበር፣ ዋና የመላእክት

አለቃም ሆኖ ኃጢአትና ክፋት በውስጡ ሲገባ በትዕቢት ምክንያት ተጣለ።

ለ. በኢሳይያስ 14፡12-17 ተጠቅሷል፤ ሉሲፈር ተብሎም ተጠርቷል። የንጋቱ ልጅ፣ በትዕቢት እንደ እግዚአብሔር ለመሆን ፈለገ፣ በዚህም ወደ ምድር ተጣለ።

ሐ. ሰይጣን አካል ነው፤ ሕይወት አለው፤ ብልህ ነው፤ የፈለገውን ያደርጋል፤ ስሜትም አለው።

### 2. የሰይጣን ባህርይ

- ሌባ ነው፡- የእግዚአብሔርን ቃል ከሰው ልብ ይሰርቃል /ማቴዎስ 13፡19/።
- ጮሌ ነው /2ኛ ቆሮንቶስ 11፡3/።
- ገዳይ ነው /ዮሐንስ 8፡44/።
- ውሸታም ነው /ዮሐንስ 8፡ 44/።
- ያስታል /ራዕይ 12፡9/።

***ውይይት***፡- በዚህ አለም ላይ ሰይጣን እጅግ እያየለ እንደሆነ ታስባለህ? በአንተ አመለካከት ምን ይመስልሃል?

## ትምህርት 35፡- የተሸነፈ ጠላት

### 1. የሰይጣን ስሞች

ሀ. የብርሃን መላአክ /2ኛቆሮ 2፡13-15/፡፡
ለ. የሚያጓራ አንበሣ /1ጴጥሮስ 5፡8/፡፡
ሐ. የአየር አለቃ /ኤፌሶን 2፡2/፡፡
መ. የጨለማ ባለሥልጣን /ቆላስይስ 1፡13/፡፡
ሠ. ታላቁ አውሬ፣ እባብ፣ ዲያብሎስ፣ ሰይጣን /ራዕይ 12፡9/፡፡
ረ. የዚህ ዓለም ገዥ /ዮሐንስ 14፡30/፡፡
ሰ. የዚህ ዓለም አምላክ /2ኛቆሮንቶስ 4፡4/፡፡
ሸ. የጨለማ ንጉሥ /ራዕይ 9፡11/፡፡

2. **የሰይጣንን መጨረሻ**

- አማኞችን በተመለከተ የተሸነፈ ጠላት ነው /ዮሐንስ 12፡31፣16፣ 1ኛ ዮሐንስ 3፡8፣ ቆላስይስ 2፡15/፡፡
- በማይለወጥ መርገም ሥር ነው /ዘፍጥረት 3፡14፣ ኢሳይያስ 65፡25/፡፡
- በሕይወት እያለ ወደ እሳተ ባህር ይጣላል፤ ለዘላለምም ይሠቃያል /ማቴዎስ 25፡41 እና ራዕ 20፡10/፡፡

***ማጠቃለያ፡-*** ሰይጣን ጉልበት አለው፤ እግዚአብሔር ግን ሁሉን ቻይ ነው፡፡ ሰይጣን በተፈጥሮ የተረገመ ነው፤ በሰይጣን ላይ በክርስቶስ በኩል ድልን እናውጃለን /ራዕይ 12፡11/፡፡

# ስለ መጨረሻው ዘመን አስተምህሮ

## ትምህርት 36፡- የክርስቶስ ዳግም መምጣት

የኢየሱስ ክርስቶስ ዳግም መመለስ በአዲስ ኪዳን በ260 ምዕራፎች፣ በ25 ቁጥሮች፣ በአጠቃላይ 318 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ከ30 ቁጥሮች መካከል አንዱ ስለ ክርስቶስ መመለስ ይናገራል፡፡ ሁሉም ስለ መጀመሪያው መምጣት እና ስለ ሁለተኛው ይናገራሉ፡፡

1. **ክርስቶስ እንዴት ይመጣል?**

ሀ. በቅጽበትና በድብቅ /1ኛ ተሰሎንቄ 5፡2፣ ማቴዎስ 24፡44፣ ማቴዎስ 24፡50/፡፡
ለ. በሕዝብ ፊት በግልጽ /ራዕይ 1፡7/፡፡

2. **ክርስቶስ ወዴት ይመጣል?**

ሀ. በመነጠቅ ጊዜ በአየር ላይ እናገኘዋለን /1ኛተሰሎንቄ 4፡17/
ለ. ከእርሱም ጋር ወደ ምድር እንመለሣለን /ዘካሪያስ 14፡4/

3. የመምጫው ምልክቶች

2ኛ ጢሞ 3፡1-7 23 ምልክቶችን ይጠቁማል፤ ከነዚህም በአብዛኛው ዛሬ የሚሆኑ ናቸው። ማቴዎስ 24፡5-7፣ 12-38 አስር ምልክቶችን ይዘረዝራል። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መመለስ ስንዘጋጅ፣ በሌላ ዘመን እንደሚመጣ ሳይሆን፣ የተቀደሰ ሕይወት በመኖር፣ ዛሬ እንደሚመጣ በማሰብ መዘጋጀት ተገቢ ነው /1ኛ ተሰሎንቄ 3፡12-13/። የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው ፀሎት "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ና" የሚል ነው!

***ውይይት፡-*** ስለ ክርስቶስ ዳግም መምጣት ከተዘረዘሩት ምልክቶች ዛሬ እየተከሰቱ ያሉ የትኞቹ ናቸው።

## ትምህርት 37፡- የሙታን ትንሣኤ

1. የሙታን ትንሣኤ በመጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ተቀምጧል

*ሀ.* በብሉይ ኪዳን በግልጽ ተቀምጧል /ኢዮብ 19፡25-27፣ መዝሙር 16፡9፣17፡15፣

ዳንኤል 12፡1-3/፣ ትክክለኛ ትንሣኤ የተጻፈው 1ኛ ነገስት 17. 2ኛ ነገስት 4፡32-35 እና 13፡21/።

ለ. በአዲስ ኪዳን፡- በኢየሱስ ክርስቶስ ትምህርት /ዮሐንስ 5፡28-29፣ 6፡39 ፣49 44፣54፣ ሉቃስ 14፡13-14፣ 20፡35-36፣ ሐዋሪያት ሥራ 24፡15፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 15፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 4፡14-16፣ ፊልጵስዮስ 3፡11፣ ራዕይ 20፡4-6፣13/።

2. የትንሣኤው አካል

**ሀ. አማኞች፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 15ን ተመልከቱ**

- ሥጋና ደም የሌለው /ቁ. 50 አና 51/፣ ስጋና ደም ያለው /ዕብራውያን 2፡14፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-6 ሉቃስ 24፡39/
- የማይበረዝ /ቁ.42/፣ የማይበሰብስና የማይታመም፣ ሥቃይ የማይነካው
- የከበረ /ቁ. 43/፣ የተለወጠ /ማቴዎስ 17፤ ራዕይ 1፡13-17/
- ኃይለኛ /ቁ.43/ የማይደክም
- መንፈሳዊ አካል /ቁ 44/፣ መንፈስ ሕይወት ይሆነዋል
- ሰማያዊ /ቁ.47-49/

**ለ. ያላመኑ ሰዎች፡- መጽሐፍ ቅዱስ ዝም ብሏል።**

3. የትንሣኤው ጊዜ

*ሀ. ጻድቃን*፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 15፡23 እና 1ኛ ተሰሎንቄ፣ 4፡14-17 የአማኞች ትንሣኤ ክርስቶስ መምጣት ጋር ይያያዛል።
ለ. *ኃጢአተኞች*፡- ዮሐንስ 5፡28-29፣ *ዳንኤል* 12፡2፣ *ራዕይ* 20፡5፣ *ራዕይ* 20፡12፤ የኃጢአተኞች ትንሣኤ የሚያያዘው በመጨረሻ ቀን ከሚሆነው ፍርድ ጋር ነው። *ራዕይ* 20፡4-6 በቅዱሳንና በኃጢአተኛ ትንሣኤ መካከል ሺ አመታት ያህል ልዩነት እንዳለ ያሳያል።
***ማጠቃለያ***- የትንሣኤው አካላችን ዛሬ ካለን አካል እንዴት ይለያል?

## ትምህርት 38፡- ፍርድ

ለዚህ አለም የፍርድ ቀን ተቀጥሮለታል፤ ይህም ፃድቃን የሚሸለሙበት ኃጢአተኞች የሚፈረዱበት ነው። *ሐዋሪያት ሥራ* 17፡31፣ እብራውያን 9፡27። *ፈራጁም* የተሰቀለው፣ በዙፋኑ ላይ ያለው ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። ዮሐንስ 5፡22-23፣ 27፣ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡1፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡10፣ *ሐዋሪያት ሥራ* 10፡42 እና 17፡31።
ከአንድ በላይ ትንሣኤ እንዳለ ሁሉ ከአንድ በላይ ፍርድ ይኖራል፤ በኖህ ዘመን ፍርድ በውሃ እንደነበረ፣ በባቢሎን ግንብ ላይ በቋንቋ መደበላለቅ የተደረገ ፍርድ ምሳሌ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ስለመጨረሻው ሰባት ፍርዶች ይናገራል፡-
1. *በመስቀል ላይ መፍረድ*፡- በአማኞች ላይ የነበረው የሰይጣን ጉልበት ተሰብሯል፤ የአማኞች ኃጢአት ተፈርዶበታል፣ ከእነርሱም ተወግዷል /1ኛ ዮሐንስ 5፡24፣ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24/።
*2. የአማኞች የራሳቸው ፍርድ፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 11፡33ና 33- የሚቀጥል ነው።*
*3. በአማኞች ላይ ፍርድ፡- በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት /2ኛ ቆሮንቶስ 5፡10/፤ ክርስቶስ ሲመጣ ለእያንዳንዱ እንደስራው ይከፍላል። ከእሳት ተፈትኖ ያለፈ ሥራ ሁሉ ሽልማት ይኖረዋል /1ኛ ቆሮ 3፡13/።*
*4. የአይሁድ ፍርድ፡- በታላቁ መከራ ጊዜ /ሕዝቄል 20፡34-38፣ ኤርሚያስ 33፡7. ሉቃስ 23፡18፣ ሐዋሪያት ሥራ 7፡51/።*
*5. የአህዛብ ፍርድ፡- በክርስቶስ ዳግም መመለስ ጊዜ በኢዮሳፍጥ ሸለቆ ውስጥ /ኢዮብ 3፡2፣ ማቴዎስ 25፡32፣34፣41/።*

6. *የወደቁ መላዕክት ፍርድ* /1ኛ ቆሮንቶስ 6፡3፣ ይሁዳ 6፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 2፡4/፡፡ *የሞቱ ኃጢአተኞች ፍርድ*፡- በክርስቶስ ያላመኑና ዳግም ያልተወለዱ በመጀመሪያው ትንሣኤ አይነሡም፤ አይነጠቁምም፡፡ ይህ የሚሆነው በነጩ ዙፋን ፊት ነው፡፡ ከሺህ ዓመት ጊዜ በኃላ ያላመኑ ሁሉ ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ /ራዕይ 20፡15/፡፡

***ውይይት***፡- ስለ ፍርዶች የሚያሳስብህ ምንድነው?

## ትምህርት 39፡- የኃጢአተኞች ዕጣ ፈንታ

በብሉይ ኪዳን 162 ጥቅሶች ኃጢአተኞች ስለሚጠብቃቸው ጨለማ ይናገራሉ፡፡ ከነዚህ ጥቅሶች 70ዎቹ በኢየሱስ ክርስቶስ የተነገሩ ናቸው፡፡ ክርስቶስን ያላመኑ ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይጣላሉ /መዝሙር 9፡17/፡፡

1. ሲኦል ምንድነው?

*ሀ*. ከእግዚአብሔር መገኘት መወገድ /2ኛ ተሰሎንቄ 1፡9/

*ለ*. የስቃይና የቅጣት ቤት ነው /ሉቃስ 16፡23/

ስለ ሲኦል ማብራሪያ

*ሀ*. ሲኦል የተዘጋጀው ለሠይጣንና ለክፉ መላእክት ነው /ማቴዎስ 25፡41፤ በክርስቶስ ያላመኑና ሰማይን የጠሉ ሁሉ በሲኦል ሰይጣንን ያጅባሉ፡፡

*ለ*. የቅጣት ቦታ ነው /ማቴዎስ 25፡46/፡፡

*ሐ*. የስቃይ ቦታ ነው /ሉቃስ 16፡23/፡፡

*መ*. የእሳት ባህር ነው /ማቴዎስ 13፡42፣50፣ ራዕይ 20፡15፣ 14፡10፣ ማቴዎስ 3፡12፣ ኢሳይያስ 33፡14/፡፡

*ሠ*. የቃጠሎ ቦታ ነው /ማርቆስ 9፡44፣ 46 እና 48/

*ረ*. በሉቃስ 16 አንድ ሃብታም ሠው ነበር፡፡ ቁ. 23 በፀሎት ነገር ግን ፀሎቱ መልስ የለውም፤ ቁ 27 ውሃ ፈልጎ ነበር፣ ወንድሞቼን አስጠንቅቅ ብሎም ነበር /ቁ. 24-27/፡፡

*ሰ*. ሲኦል የማያቋርጥ ዘላለማዊ ነው /ማቴዎስ 25፡41፡46፣ ራዕይ 20፡10ና 15/

***ውይይት***፡- የዘላለም ቅጣት ስናስብ ላላመኑት ወንጌልን እንድንናገር ያነሳሳናል፡፡

## ትምህርት 40፡- የጻደቃን የመጨረሻ ሽልማት

ሞት ለአማኞች እንደ እንቅልፍ ነው /1ኛ ተሰሎንቄ 4፡14/፤ ይኸውም ሰው በክርስቶስ መገኘት ወዲያው ይነቃል /ፊልጵስዩስ 1፡23/፡፡

### 1. የወደፊት የአማኞች ክብር

ሀ. ከክርስቶስ ጋር መሆን /ዮሐንስ 14፡3/

ለ. በፊቱ ይቆማሉ /መዝሙር 17፡15፤ 2ኛ ቆሮንቶስ 416፤ ራዕይ 22፡24/

ሐ. የክርስቶስን ክብር ያያሉ /ዮሐንስ 8፡17-18/

መ. ከክርስቶስ ጋር ይከብራሉ /ሮሜ 8፡17-18/

ሠ. ከክርስቶስ ጋር ይነግሣሉ /2ኛጢሞቴዎስ 2፡12/

ረ. የሁሉ ነገር ወራሾች ናቸው /ራዕይ 21፡7/

ሰ. እንደ ከዋክብት ያበራሉ /ዳንኤል 12፡3/

### 2. አማኞች የሚቀበሉት ዘውድ

ሀ. የማይወገድ ዘውድ 1ኛ ቆሮንቶስ 9፡24-25 የሯጮች ዘውድ እብራውያን 12፡1

ለ. የደስታ ዘውድ 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡19 ለወንጌል ሰባኪዎች

ሐ. የጽድቅ ዘውድ 2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡8 በክርቶስ በማመን የሚገኝ ዘውድ

መ. የሕይወት አክሊል ያዕቆብ 1፡12 ለታማኞች /ለታመኑት/

ሠ. የክብር አኪሊል 1ኛ ጴጥሮስ 5፡4 ለእረኞች፣ ለመጋቢያን፣ ለወንጌል መልእክተኞች እና ለአስተማሪዎች

### 3. ሰማይ ምንድ ነው?

- የጌታ አምላክ ቤት ነው /ማቴዎስ 6፡9፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 12፡2/፡፡ የመጀመሪያው ሰማይ ወፎች የሚበሩበት ነው፤ ሁለተኛው ተመራማሪዎች የሚሄዱበት ሲሆን፣ ሶስተኛው የእግዚአብሔር መገኘት ቤት ነው፡፡
- በአምላክ የተሠራ የሰው እጅ ያልነካው ሕንፃ ነው /2ኛ ቆሮንቶስ 5፡1/፡፡
- የእግዚአብሔርንና የክርስቶስ መንግሥት ያለበት ነው /ኤፌሶን 5፡5/፡፡
- የአብ ቤት ነው /ዮሐንስ 14፡2/፡፡
- ሞት፣ እንባ፣ ሐዘን፣ ስቃይ፣ የሌለበት ነው /ራዕይ 21፡4/፤ ጨለማም ሌሊትም በዚያ የለም /ራዕይ 22፡3-5/፡፡

- በአዲስ ፍጥረት የተሞላ ቦታ፣ የሕይወት ወንዝ፣ የሕይወት ዛፍ፣ አዲስ አገልግሎት፣ አዲስ ሕብረት እና አዲስ ብርሃን ያለበት ነው /ራዕይ 22፡4/፡፡

***ማጠቃለያ፡-*** **ሰማይ ለተዘጋጁ ሰዎች የተዘጋጀ ቦታ ነው፡፡ የኛ ግብ እዚያ ለመድረስ ነው፤ ከእኛ ጋር በክርስቶስ የተዋጁ ለእርሱ መከራን የተቀበሉ ሁሉ የሚያጅቡን ቦታ ነው፡፡**

## ሥነ-ስብከት
## መግቢያ

ሥነ-ስብከት መዝገብ ቃላት እንደሚያስቀምጠው የስብከት -ጥበብን ያመለክታል፡፡ ዓላማውም በተማሪዎች ውስጥ ያለውን የስብከት ጥበብ ማሳደግ ነው፡፡ ነገር ግን አንድ መረዳት ያለብን ነገር ስብከት ማለት በተሰበሰቡ ሰዎች ፊት ቆሞ በድፍረት በመናገር ከሚደረገው በላይ መሆኑ ነው፡፡ ስብከት ማለት የእግዚአብሔርን መልእክት ለሰው ልብ ማስታላለፍ ነው፡፡ ጳውሎስ ስለዚህ እውነት በግልጽ ጽፏል፡፡ “የመስቀሉ ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለኛ ለምንድን ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው” /1ኛ ቆሮንቶስ 1፡18/፡፡ ይህ ትምህርት የሚጠይቀው የስብከት ጥበባችንን ለማሳደግ መትጋት እና ጥረት ማድረግ እንዳለብን በመሆኑ ብዙዎችን የማዳን ብሎም የማነጽ ዕድል ያስገኛል፡፡

ይህ አጭር ገጾች ስላሉት ስለ ስብከት አቀራረብ ብዙ መናገር አንችልም፡፡ ስለድምጽና አለባበስ በተመለከተ በአስተማሪው በኩል የሚታረሙ ይሆናል፤ በዚህ ትምህርት ስለ ስብከት ይዘትና የተሻለ አቀራረብ ማስተማር የሚችሉ ነገሮች ተካትተዋል፡፡
የትምህርት አቀራረቡ ወይም ዝግጅቱ በተለያዩ ትምህርት ቤቶች በቀንና በክፍል የተከፋፈለ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም፡፡ ነገር ግን እነዚህ በሳምንታዊ ይዘት የተዘጋጁ ትምህርቶች ናቸው፡፡ ይህም ለተግባር ሥራ ዝግጅትና ስብከት የሚሆን ጊዜ ለመስጠት የሚያስገድዱና ምቹ ሆኖ የቀረበ ነው፡፡

ይህ ትምህርት የመጣው በብዛት ከHow to Prepare Sermons, William Evans Moody Press Pub/ ላይ ነው፡፡

# ክፍል ሦስት
# ሥነ-ስብከት

## 1ኛ ሳምንት

### ቀን አንድ፡- ስብከት ምንድነው?

ስብከት ማለት የመዳንን መልካም ዜና ከሰዎች ወደ ሰዎች ማወጅ ነው። ሁለት ክፍሎች አሉት፡- ተናጋሪው እና መልእክቱ ወይም እውነት እና ሰው። ሰባኪ ወንጌልን ለመስበክ የሚጠራው በእግዚአብሔር ነው። ስለ እግዚአብሔር ከሰው ጋር ያውራል፤ ስለ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ይነጋገራል። የተቀደሰ፣ መንፈስ ቅዱስ እና እምነት ያለበት ሊሆን ይገባል። ይህ ሲሆን ብዙዎች ሕይወታቸው ይለወጣል፤ የእግዚአብሔርም መንግሥት ይሠፋል /ሐዋሪያት ሥራ፡ 11፡24/። ስብከት የሰባኪውን ማንነት ስለሚያካትት የሰባኪው ልምድም ሕይወትም ወሳኝ ነው። የሚሰበከው እውነት ለሌሎች ከመናገር አስቀድሞ በሰባኪው ሕይወትና ልብ የተቀመጡ መሆኑን አለባቸው።

***ውይይት***፡- በወንጌል ስብከት በተመለከተ የሰባኪው የሕይወት ይዘት ምን መሆን አለበት? የሰባኪን አገልግሎት የሚያደናቅፉ ባህሪያት ምንድ ናቸው?

### ቀን ሁለት፡- የስብከት ጥቅስ /ምንባብ ክፍል

1. በተገቢው ሁኔታ የሚመረጡ ጥቅሶች አሉት፡-

ሀ. የሰሚዎችን ፍላጎት ያነሣሣል፤ ስለዚያ ምን ይላል?

ለ. የሰሚዎችን ልበ ሙሉነት ያገኛል፤ የእግዚአብሔር ቃል ምንድነው?

ሐ. ለሰባኪ ሥልጣንና ድፍረት ይሰጣል፡- “እግዚአብሔር እንዲህ ይላል የሚለው ሰማያዊ ሥልጣን ነው!”

መ. የሰባኪው አእምሮ ወዲያ እና ወዲህ እንዳይል ይጠብቃል።

ሠ. ሰባኪው የመጽሐፍ ቅዱስን ሐሳብ ብቻ እንዲናገር ያደርጋል።

2. የሚመረጠውን ክፍል የሚገዙ አጠቃላይ መመሪያዎች፡-

ሀ. ሰባኪው የሰሚዎችን መንፈሳዊ ፍላጎት ማወቅ አለበት።

ለ. የሰባኪውን እውነት ሂደቱን /ኡደቱን/ ማወቅ አለበት። የቀረ እውነት አለ ወይ? በአመቱ ውስጥ የሚሰበኩ ርዕሶችን /ሐሳቦችን/ ማቀድ ጠቃሚ ነው።

ሐ. የሚነገረውን ነገር ማስተላለፍ እንደሚቻል እርግጠኛ መሆን አለበት፤ እንዳንድ ወጣት ሰባኪዎች ስለሚቸገሩ ነው!

3. የሚከተሉት መመሪያዎች ርዕስ ወይም ጥቅስ በሚመረጥበት ጊዜ አጋዥ ናቸው፡-

ሀ. የእግዚአብሔርን ቃል በቋሚነት ማንበብ ጠቃሚ ነው።

ለ. ማስታወሻ መጠቀም በጣም ያግዛል።

ሐ. ጥሩ ማብራሪያ ማንበብ አዳዲስ ሐሳቦችን ለማግኘት ይጠቅማል።

መ. የመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወሳኝ ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር የሚኖር ሰባኪ መቼም ቢሆን የሚሰብከውን ነገር አጥቶት አያውቅም። የቤት ሥራ፡- በሚቀጥለው ወር እሰብካለሁ ብለህ ያሰብክበትን 10 ጥቅሶች ዘርዝር።

## ቀን ሶስት፡- የስብከት ርዕስ

ጥበብ የተሞላ አመራረጥ እንዲሁ ትክክለኛ ቃላት መጠቀም መልእክቱን ለማስተላለፍ ወሳኝ ነው፣ የሚከተሉትን ሐሳቦች ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡-

1. ስለሚናገረው ዋና ሐሳብ ሰባኪው በሚገባ ማወቅ አለበት።
2. ዋና መልእክቱ አንድ መሆን አለበት፤ ለአድማጮች በቀላሉ እንዲረዱት ከማስቻሉ ባሻገር በሰሚዎች አዕምሮ እንዲቀመጥ ያደርጋል።
3. ዋና ሐሳቡ አላስፈላጊ ትንታኔ የሌለውና ክብደት ያለው ሊሆን ያስፈልጋል።
4. ሰባኪው እንዴት ዋና ሐሳቡን መናገር እንዳለበት ማቀድ ይኖርበታል።
5. ለለውጥና ለውሳኔ መስበክ ጥሩ ነው።
6. ዋና ሐሳብ በሰአት፣ በቦታና በሁኔታ የተመቻቸ መሆን አለበት።

ለምሳሌ፡- በፋሲካ ስለትንሣኤ ማስተማር፣ ወዘተ።

## ቀን አራት፡- የስብከት ዝግጅት መረጃ መሰብሰብ

ጥሩ መጽሐፍቶችን ማንበብ የሰባኪውን ሰብከት ያበለጽጋል፤ ለወቅታዊ ጉዳዮችም እንዲሁ የነቃ መሆን አለበት። አስብ፣ ፀልይ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አዛምድ። ክርስቶስ ሁልጊዜ የሚያይ፣ ስብከቶቹ ካያቸው ከሰማቸው ነገሮች ምሳሌ የታጀቡ ናቸው።

ሰባኪው ማስታወሻ መያዝ አለበት፣ ምክንያቱም ያየውንና የሰማውን በአጭሩ ፅፎ ስለ እርሱ ማሰላሰልና ማሰብ እንዲችል ይረዳዋል፡፡ በቋሚነትም መረጃ መሰብሰብና ማጥናት ይኖርበታል፡፡

***ውይይት***፡- ለስብከት ጠቃሚ የሆኑ፣ ባለፈው ወር የተከሰቱ ነገሮች ምንድን ናቸው?

**ቀን አምስት፡- የስብከት ይዘትን ማቀናጀት**

በስብከት ዙሪያ የተዘጋጁ ሐሳቦችን በሙሉ ማቀናጀት በጣም ጠቃሚ ነው፡ ሐሳቦችን ማቀናጀትና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፣ ሁሉም ጠቃሚ ሐሳቦች መካተታቸውን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡ የስብከት ሓሳቦች ማቀናጀት ጥቅሙ፡-

1. *ለሰባኪው*፡- በግልጽ በተገቢ ሁኔታ የተቀመጡ ሐሳቦች ለማስቀመጥ ቀልል ይላሉ፡፡

2. *ለስብከት*፡- የስብከት ውጤታማነት የሚለካው በግልጽ እና ተገቢ ሁኔታ የተዋቀረ አንደሆነ ነው፡፡

3. *ለሰሚዎች*፡- አድማጮች የሚያስታውሱትንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ይዘው እንዲሄዱ የሚያደርገው የአቀራረብ ብሎም የቅንጅት ጥረት ነው፡፡ ጥሩ ዝግጅት ለሰባኪው ሲያቀርብ ይጠቅመዋል፤ ለሰሚዎችም የሰሙትን ለመከተል ይረዳቸዋል፡፡

***ውይይት***፡- አንዳንድ ደካማ ዝግጅቶች ምንድናቸው? ለምን?

**2ኛ ሳምንት**

**ቀን አንድ፡- የጥሩ ስብከት ዝግጅት ይዘቶች**

1. *ወጥ ሐሳብ፡-* ሰባኪው ወጥ ኣሳብ ሊኖረው ይገባል፡፡ ማስረጃዎችን፣ ማረጋገጫዎችን፣ ምስክርነቶችን እና ምሳሌዎችን ዋና ሐሳቡን በሚደግፍ መልኩ ማሰናዳት አለበት፡፡

2. *ተገቢ አስተሳሰብ /አመክንዮ/፡-* በስብከት ክፍሎች መካከል ማስረጃዎቹ በብልህነት የተቀናጁ፣ ወደ ስሜት የሚሄዱና ፈቃደኛ የሚያደርጉ መሆን አለባቸው፡፡

3. *የስብከት ቅደም ተከተል*፡- ስብከት ግልጽ ቅድመ ተከተል ሊኖረው ይገባል፤ የሰው አካል አፅም እንደሚፈልግ ሁሉ እውነት ለመናገር የስብከት ቅደም ተከተል ለመከታተል ግልጽና በቀላሉ ለመረዳት የሚያስችል መሆን አለበት፡፡ አንዳንድ ሰባኪዎች በእያንዳንዱ ቅድመ ተከተል የመጀመሪያው

ቃል ተመሳሳይ በማድረግ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ ሌሎች በማወዳደር ተቃራኒውን ይጠቀማሉ፡፡ በተመሳሳይ ቃል የተቀመጠውን ቅድመ ተከተል ምሳሌ ተመልከቱ፡-

ዋና ሐሳብ፡- መለወጥ

1. Place /ቦታ/
2. Purpose /ዓላማ/
3. Persons /ሰዎች/
4. Power /ኃይል/

ሌሎች ደግሞ የሚከተለውን መንገድ ይጠቀማሉ፡-

5. Admit /መቀበል/
6. Commit /መሰጠት/
7. Submit /መቅረብ/
8. Transmit /ማስተላለፍ/

***የቤት ሥራ፡-*** በተመሳሳይና ቀለል ባሉ ቃላት በመጠቀም የስብከት ቅደም ተከተል

አዘጋጅ፡፡

**ቀን ሁለት፡- የስብከት መግቢያ**

ሁሉም ጥሩ ስብከት በ3 ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡- መግቢያ፣ ዋና ሐሳብ፣ መደምደሚያ፡፡

***የስብከት መግቢያ፡-*** በምግብ እንደሚደረገው ቅመም ነው፤ ለብዙ ስጋ ወጥ ጥሩ መዓዛ እንደሚሰጥ ቅመም ስብከቱን ያሳምራል፡፡ በዋና ሐሳብ የራሱ ጊዜና አቀራረብ ቢኖረውም አስቀድሞ ማስተዋወቅ ጠቃሚ ነው፡፡

***የመግቢያ ዓላማ፡-***

1. የሰሚዎችን ፍላጎት ለዋና ሐሳብ ማዘጋጀት ሰሚዎች ለመስማትም ሆነ ለመረዳት እንዳይቸገሩና እንዲዘጋጁ የማድረግ ኃላፊነት የተናጋሪው ነው፡፡
2. ለሚቀጥለው ሐሳብ ሰሚዎችን ማነሣሣት

*የመግቢያ ምንጮች*

1. አጠቃላይ ከሐሳብ ወይም ከጥቅሱ ጋር ያለው ቁርኝት መዝሙር 23፡4-6ን ለማስተዋወቅ ሰባኪው እንዲህ ብሎ ሊጀምር ይችላል፡- “ይህ ጥቅስ ታሞ በሞት አልጋ ላይ ያለውንና ሰው የሞተበትን ሐጢአተኛ እንዴት ያፅናናል?”
2. ታሪካዊ ዳራው /በክፍሉ ያለው/
3. የመጽሐፍ ቅዱስ መልከአ ምድር
4. ልምዶችና መሣሪያዎች በዚያን ዘመን
5. ለፀሐፊው ዋና የሆኑ የታቀደባቸው ሁኔታዎች
6. ክስተቶቹ /ገና ወይስ ፋሲካ/

***የቤት ሥራ፡-*** ለፋሲካ ስብከት መግቢያ አዘጋጅ፡፡

**ቀን ሶስት፡- የጥሩ መግቢያ ይዘቶች**

- *በስሜት ወይም በሚያነሣሣ መልክ አትጩሁ-* መግቢያ ላይ ከሆንክ ትደርስበታለህ፡፡ ቀስና ዝግ ባለ ድምፅ መጀመር፣ በሂደት ከፍ እያደረግህ መሄድና ወደ ጡዘቱ መድረስ ተገቢ ነው፡፡
- *በጣም አይርዘም፡- ረዥም መግቢያ አድማጮችን ያደክማል፡፡*
- *በጥንቃቄ የተዘጋጀ መሆን፡- መፃፍ ጥሩ ነው፤ መግቢያህ መጨረሻህን ስለሚያሳይ* በጥንቃቄ ተዘጋጅ፣ በጥንቃቄ ጀምር፡፡

***የቤት ሥራ*-** ለሮሜ 1፡16-17 ስብከት ጥሩ መግቢያ አዘጋጅተህ ለክፍል ተማሪዎችህ አካፍል፡፡

**ቀን አራት፡- የስብከት ዋና አካል**

ዋና ሐሳብህ በሐሳቡ ውስጥ ባሉ ክፍፍሎች ሊወሰን ይችላል፡፡ ክፍፍሎች ምናልባት ሶስት ወይም ሰባትም ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ክፍፍሎቹ የሚከተሉትን ጥቄዎች መመለስ አለባቸው፡-

1. ***ምን?*** የመጀመሪያው ክፍል የሐሳቡን ማብራሪያ የያዘ መሆን አለበት፡፡ ከክፍሎች በኋላ ግራ መጋባት እንዳይኖር መጠበቅ አለብህ፣ ምክንያቱም የሚደርሰው ወደ አእምሮ እንጂ ወደ ስሜትና ፈቃድ አይደለም፡፡
2. ***ለምን?*** ይህ ክፍል የሐሳቡን አስፈላጊነት በግልጽ ማስረዳት አለበት፤ ለምንድነው እውነትነቱ? ለምን ማመን አለብኝ? እንዴት ይረጋገጣል? ምክንያታዊ ነውን?

3. ***እንዴት?*** ይህ ክፍል ስብከቱ የሚቀርብበትን ዘዴና የአቀራረብ አተገባበርን ከግምት ያስገባ መሆን አለበት፡፡ እንዴት የሚለውን ሐሳብ ለማብራራት የሚጠቀሙ መሠረታዊ ሶስት ሐሳቦች አሉ፡፡ የእግዚአብሔር ድርሻ፣ የሰው ድርሻ እና ጥያቄ ናቸው፡፡

4. ***ከዚያስ?*** ይህ ወደ ተግባር የሚመራ ጠቃሚ ክፍል ነው፡፡ የግል ጉዳዮችን ያካተተ ነው፡፡ ይህ ክፍል ሰው ክርስቶስን እንዲቀበልና ክርስቲያናዊ ሕይወት እንዲኖር ያሳምናል፡፡

***የቤት ሥራ***፡- በሮሜ 1፡16-17 ስብከት ዋና ሐሳብ ቅደም ተከተልን አዘጋጅ፡፡

### ቀን አምስት፡- የስብከት ማጠቃለያ

የመጨረሻዎቹ አምስት ደቂቃዎች የስብከቱ ወሳኝ ደቂቃዎች ናቸው፡፡ ችግሮቻችን በማጠቃለያ ላይ የጠለቀ ዝግጅት አናደርግም፡፡ አንዳንድ ጊዜ የማጠቃለያ ጥሩ ነገሩ የዋና ሐሣብ አጣሪ ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የሚያስረዳ፣ የተመረጠ፣ ነፍስን የሚመራ፣ የተለየ ምሳሌ ይሆናል፡፡ ሌላ ጊዜም ግጥም ወይ የታወቀ መዝሙር ይሆናል፤ ወይም ደግሞ ስብከቱ ከወቀሳ መሰል ንግግር ሊያልቅ ይችላል፡፡ ማጠቃለያው ከመግቢያው መብለጥ የለበትም፤ ከ3-5 ደቂቃዎችም አያልፍም፡፡

የቤት *ሥራ*፡- ለሮሜ 1፡16-17 ስብከት የሚያነቃቃ ማጠቃለያ አዘጋጅ፡፡

### ምሳሌዎችና አጠቃቀማቸው

የኢየሱስ ክርስቶስ መልዕክቶች በተረቶች፣ በምሳሌዎችና ተምሳሌቶች የተሞላ ነው፡፡ ከማንም በላይ ኢየሱስ ክርስቶስ ምሳሌ በመጠቀም መስበክ እንደሚቻል ጥሩ ምሳሌ ሆኖአል፡፡ ጥሩ ምሳሌን መጠቀም አድማጮች ዋና ሐሳቡን ወደ ቤታቸው ይዘው እንዲሄዱ ትልቅ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

### የምሳሌ አላማ

1. በመስኮት ብርሃን እንደሚገባ ሁሉ በዋና ሐሳብ ላይ ብርሃን ይጭራሉ፡፡
2. ያብራራሉ
3. ያረጋግጣሉ
4. አድናቆትን ይጭራሉ
5. ወቀሳን ይፈጥራሉ፡፡

**የምሳሌ ምንጮች**

1. ሰባኪው ሁሉንም አቅጣጫ ማየት አለበት። ኢየሱስ ክርስቶስ በአበባ፣ በአሞራ፣ በጨው፣ በሻማ፣ በመስፈሪያ፣ የግብዞችን ፊት፣ ትንኞችን፣ ትልቅ በርና ትንሽ በሮች፣ የመርፌ ቀዳዳ፣ የዳቦ እርሾ፣ የዘሩ ምሳሌ፣ የአሣ መረብ፣ አበዳሪና ተበዳሪ፣ ወዘተ...።

2. ሌሎች ምንጮች የሚያካትቱ ጋዜጣዎችን፣ ታሪኮችን፣ እንስሳትን፣ አትክልትን፣ ሕፃናትንና የተለያዩ ነገሮችን ያካትታሉ።

***ውይይት፡-*** በዮሐንስ 3 ላይ ስላለው ዳግም መወለድ ጥሩ ምሳሌ ምንድነው?

***ማስታወሻ፡-*** በሚቀጥሉት ትምህርት ተማሪዎች ለእያንዳንዱ ስብከት ቅደም ተከተል ያዘጋጃሉ፣ ይሰብካሉ። በስብከት ዝግጅት ላይ መግቢያ፣ ምሳሌ፣ ማጠቃለያ እንደተረሳ።

**3ኛ ሳምንት፡- የግል ታሪክ ስብከት**

የመጽሐፍ ቅዱስ ሕይወት የግል ታሪክ አይነት ስብከቶችን ያካተተ ነው።

ለምሳሌ፡- አራቱ አብርሃም የተዋቸው ነገሮች፡-

1. አገሩንና አካባቢውን መልቀቅ /ዘፍጥረት 12፡1/
2. ከሎጥ መለየት /ዘፍጥረት 13፡9/
3. አጋርንና ኢስማኤልን ማባረር /ዘፍጥረት 21፡10/
4. ይስሐቅን መሰዋት /ዘፍጥረት 22/

**4ኛ ሳምንት፡- የትረካ ስብከቶች**

በእንደዚህ አይነት ስብከት መጽሐፍ ቅዱስ የነገሮችን ክስተት ያሳያል።

የትረካ ስብከት ቅደም ተከተል ምሳሌ፡-

ዳንኤል በአንበሶች ጉድጓድ

ዋና ሐሳብ፡- እግዚአብሔር ልጆቹን ይጠብቃል

መግቢያ፡- በምርኮ አገር የወጣት ሰው ታሪክ

ጥቅሱ፡- ዳን 6፡19-23

ቅደም ተከተል፡-

1. ሠይጣናዊ ሴራ /ዳንኤል 6፡1-9/
2. የየቀኑ ተግባር /ቁ.10. /
3. መለኮታዊ አቅርቦት /ቁ.21-24/

***ማጠቃለያ፡-*** ዳንኤል በልበ ሙሉነት መከራን ተጋፍጦአል፤ ምክንያቱም ከአምላኩ ጋር የጠበቀ ህብረት ነበረው፡፡ ሕይወት በአንተ ላይ የምታመጣውን ሁሉ ለመጋፈጥ እንዲያስችል ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ሁኔታ አለህን?

**5ኛ ሳምንት፡- ገላጭ /አውዳዊ/ ስብከት**

ገላጭ ስብክት በጥቅስ ላይ የተመሠረተ ስብከት ሆኖ በጥቂት ወይም በተወሰነ ቁጥሮች የተያዘ ነው፤ በጥንቃቄም መተንተን አለበት፡፡ ምሳሌ፡-

ያለ ገደብ የተሰጠ ስጦታ

ዋና ሐሳብ፡- መቀደስ

ጥቅስ፡- ሮሜ 12

***መግቢያ፡-*** መቀደስ ማለት መነቃቃት፣ መለየት፣ መሰጠት ወይም ለእግዚአሔር ክብር መለየት ነው፡፡ መቀደስ ማለት በንጉሥ ክርስቶስ ሥር ሕግ ለመታዘዝ መለየት ማለት ነው፡፡ በሕይወትህ አለቃ ማን ነው?

1. ማን ሊቀደስ ይችላል? በክርስቶስ ደም የነፃችሁ የእግዚአብሔር ቤተሰብ የሆናቸው ወንድሞች ሆይ! ታላላቆች ብቻ ሳይሆኑ አዋቂዎችም፣ ጠቢባንም ብቻ ሳይሆኑ ለሰው ሁሉ፣ መቀደስ የተሰጠ እንደሆነ እንድታውቁ እለምናችኋለሁ፡፡

2. የፅድቅ ምክንያት፡- በእግዚአብሔር ምህረት በስልጣንና በግፊት አይደለም፤ በእርሱ ምህረት እንጂ በማስፈራራትም ያልሆነ፤ ነገር ግን በፍቅርና በምህረት የተደረገ ነው፡፡ አንዳንድ የእግዚአብሔር ተዓምራቶች፡- ማዳን፣ መቀደስ፣ የመንፈስ ቅዱስ አብሮነት፣ በየቀኑ ማገዙ ጤንነቱ፣ ብንሞት እንኳ ሰማይ መሄድ ወዳጆችና ቤተክርስያን፡፡

3. የጽድቅ እርምጃ፡- "ራስን መስጠት"

ሀ. በፈቃደኝነት እራስን መስጠት

ለ. የግል ነው፡- አካላችን፣ ሕይወታችን፣ ያለንን ሁሉ

ሐ. ዋጋ የሚጠይቅ ነው፡- ሕያው መስዋዕት፣ ራሳችንን በመሰዊያው ላይ ማኖር /አብርሃም ይሳቅን እንዳኖረ/

4. ክርክሮች ስለመቅደስ፡- /ምክንያታዊ አልግሎትን/ በእውነት የዳንንና የተዋጀን ከሆነ የእኛን ትንሽ አገልግሎት መስጠት ተገቢና ምክንያታዊ ነው፡፡

5. ምን መቀደስ አለብኝ? “አካልህን” አካላችን የራሳችን አይደለም፣ በክርስቶስ ደም የተዋጀ አካል ነው።

ሀ. አካላዊ ጥንካሬ፡- ስለ ጤንነትህ እግዚብሔርን አመስግን፣ ለራሱ ጥቅም አድርገው

ለ. እግራችን በሩጫ መልእክቱን ለማድረስ የተለየ ነው

ሐ. እጃችን ለበጎ ሥራና የወደቁትን ለመደገፍ

መ. አይናችን የሚጠፉትንና የተጎዱትን ለማየት

ሠ. ጆሮአችን በመከራ ሆነው ወደ ሚያለቅሱት እንዲደርስና እንድንፈልግ

ረ. ልባችን የትክክለኛ ማንነት ምልክትና ውስጣዊ ማንነት ተምሳሌት ነው። ይህም ከሁሉ በላይ እግዚአብሔር የሚፈልገው ነገር ነው /2ኛ ቆሮንቶስ 5፡8/።

***ማጠቃለያ***- መቀደስ ሂደት ነው፤ በየቀኑ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለጌታ የመስጠት ያህል ነው። አሁን እንኳን ሁለንተናህን ለእግዘአብሔር ቀድስ።

***ማስታወሻ***- ስጦታው ለበኃላ ሳይሆን፣ ለአሁን ነው፤ ምክንያቱም ተመልሶ አይመጣምና።

**6ኛ ሳምንት፡- ርዕሳዊ ስብከት**

ርዕስ ብዙ ጊዜ የስብከት ትኩረት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ማብራሪያ /Concordance/ ጥቅሱን በተለያዩ ቃላት ስለሚያሳይ በዝግጅት ወቅት ይጠቅምሃል። የርዕሳዊ ስብከት ምሳሌ፡-

ናና ጠጣ

ዋና ሐሳብ፡- የሕይወት ውሃ

ጥቅሱ፡- ኢየሱስ ክርስቶስ ቆሞ በታላቅ ድምፅ “ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ” /ዮሐንስ 7፡37/።

***መግቢያ፡-*** የውሃ ጥም አጋጥሞህ ያውቃል? ከሁሉ ነገር በላይ ውሃን መፈለግ ምን እንደ ሆነ ታውቃለህ? ስለ ውሃ ጠቃሚ የምትለውን ሐሳብ ቀጥልበት።

ቅደም ተከተል፡-

1. የሕይወት ውሃ ባህሪያት፡-

ሀ. ሕያው /ዮሐንስ 4፡10/

ለ. ንፁህ /ራዕይ 22፡1/

ሐ. ግልፅ /ራዕይ 22፡1/

መ. የተትረፈረፈ /ሕዝቄል 47፡1-9/

2. የተሰጠው ለማን ነው?

ሀ. ለተጠሙ /ራዕይ 21፡66/

ለ. ለሁሉም /ራዕይ 22፡17/

3. የሚገኝበት መንገድ

ሀ. በመምጣት /ራዕይ 22፡17/

ለ. በመወሰድ /ራዕይ 22፡17/

***ማጠቃለያ*፡-** ማጠቃለያውን ተማሪዎች ያዘጋጁ፡፡

**7ኛ እና 8ኛ ሳምንት፡- ገላጭ ስብከት**

ገላጭ ስብከት እስከ አሁን ካየናቸው በጣም ይለያል፡፡ የጽሑፍና የርዕስ ስብከቶች አንድ ሐሳብ ላይ የተመሠረቱ ሲሆን፣ ገላጭ ስብት የሚያተኩረው የመጽሐፍ ቅዱስን ክፍል በጥልቀት በማብራራት ነው፡፡ ገላጭ ስብከት ከሁሉ የበለጠ እንደሆነ ይታሰባል፡፡

**ገላጭ ስብከትን የመጠቀም ጥቅሞች**

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሰባኪዎችንና ሰሚዎችን ያፈራል፡፡ ሰባኪውንም አድማጩንም መጽሐፍ ቅዱሳዊያን ያደርጋቸዋል፡፡

2. የመጽሐፍ ቅዱሣዊ ሐሣብ /መልእክት/ እንዲሰበክ ያደርጋል፤ ይህም የኢየሱስ ክርስቶስ ዘዴ ነበር /ሉቃስ 41፣ ኢስጢፋኖስ፡- ሐዋሪያት ሥራ 7 እና 8፣ ጳውሎስ፡- ሐዋሪያት ሥራ 28፣ ጴጥሮስ፣ ሐዋሪያት ሥራ 2ና3/፡፡

3. በይዘቱ የሰፋ ነው፤ በሰሚዎችም ሕይወትን በመተግበርና እውነትን በመግለጥ ትልቅ ዕድል አለው፡፡

**የገላጭ ስብከት ውስንነቶች**

1. ለሰሚዎች አሰልቺ ይሆናል

2. ሰባኪው ሰነፍ ሊሆን ይችላል፡- እውነትን ወይም ዋና ሐሳቡን ከመናገር ይልቅ ቁጥር በቁጥር እያነበበ እያንዳንዱ ላይ ጊዜ እንዲያጠፋ ያደርጋል፡፡

3. ክፍሉ በጣም ረዥም ከሆነ አድማጭን ግራ ሊያጋባ ይችላል፡፡

አንዳንዴ ስብከቱን በመወሰን፣ ሰባኪው ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ እንዳይነካ /እንዳይናገር/ በማድረግ ሊወስነው ይችላል። ገላጭ ስብከት አንድ ወጥ የሆነ ዋና ሐሳብ ሊኖረው ይገባል፤ ይህም የሐሳብ እንድነት እንዲኖር ያግዛል። አሰልችነትን ለመቀነስ ጥቅሱ ከማንኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የተወሰደ መሆን አለበት። ስብከቱም የንግግር ብቻ ሳይሆን፣ ተግባር ጭምር መሆን አለበት።

**የገላጭ ስብከት ምሳሌ**

ከሞት ወደ ሕይወት

ዋና ሐሳብ፡- የኢየሱስ ክርስቶስ ሞት

ጥቅስ፡ ሮሜ፡ 6-11 “ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለ ኃጢአተኞች ሞቷልና”

መግቢያ፡- በጳውሎስ ስብከት ያለው ተዛምዶ

ቅደም ተከተል

1. አንድ ሰው ሞተ

ሀ. ሁሉም አንደሚሞት የታወቀ እውነት ነው

ለ. ይህ ያልተለመደ እውነት የሚሆነው

- የሟች ባህሪያት
- ሞትን እምቢ ማለት ይቻላል
- በሞቱ የተሠራው ሥራ ስናስብ

2. ክርስቶስ የሞተለት ሕዝብ

ሀ. ኃጢአተኛ፣ አምላካዊ የልሆነ፣ ደካማ፣ ጠላት የሆነ

ለ. ሞተላቸው የሚል የቃሉ ትርጉም

3. የክርስቶስ ሞት አላማ

ሀ. አሉታዊነቱ፡- ለማጥፋት ሳይሆን እግዚአብሔር ለሰው ያለው ፍቅር ነው።

ለ. አዎንታዊነቱ፡- ሰው ምናልባት፡-

- ሊፀድቅ
- ሊታረቅ
- ከቁጣ ሊድንና
- በሕይወቱ ለማዳን ይችላል።

ማጠቃለያ: -

1. የመስቀሉን አስፈላጊነት አናውቃለን ወይ?
2. ለኛ ከንቱ ነው?  ወይስ በጣም ጠቃሚ ነው?
3. ከሞት የተነሣ ለሱ ያለን ፍቅር ምን ያክል ሊሆን ይገባል?

# መንጋውን መጠበቅ
## መግቢያ

ጴጥሮስ ሲፅፍ "በመካከላችሁ ያሉትን የእግዚአብሔርን መንጋ መግቡ" ይላል /1ኛ ጴጥሮስ 5፡2/፡፡ ያለጥርጥር ጴጥሮስ የማይረሳው ነገር ጌታ ኢየሱስ ትወደኛለህን ብሎ በጠየቀው ሰዓት ያለውን ነው /ዮሐንስ 21፡15-17/፡፡ በእያንዳንዱ ጥያቄ እየተከተለው በጎቼን ጠብቅ፣ ግልገሎቼን አሰማራ ይለው ነበር፡፡ ዛሬም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተመሣሣይ ትዕዛዝ ለተጠሩና ለሚያገለግሉ ተከታዮች ሁሉ በከተማ በገጠር ላሉ ይህንን ይነግራቸዋል፡፡

ሌላው ጴጥሮስ በመመገብ ላሉ ወጣቶች ሲመክር፣ መመገብ ብቻ ሳይሆን ምሳሌነት ያላቸው ጭምር እንዲሆኑ ያበክራል፡፡ ይኸውም ስለ መንጋው ችግር፣ ጥያቄ፣ ሸክም፣ ግድ የሚሰኙ፣ በሕይወት ምሳሌነት ይህን ዘወትር የሚተገብሩ ሊሆን እንደሚገባ ያስገነዝባል፡፡ ይህ ትምህርት የተለያዩ ሐሳቦችን ያነሣል፡- መስበክን፣ መምከርን፣ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር አምባሳደር መሆን! የጴጥሮስ ቃላት የትምህርቱን ግብ ያመለክታሉ፡፡ "የእግዚአብሔር መንጋ እረኛ ሁን፤ ዋና እረኛ በመጣ ጊዜ የማይቀየረውን የክብርን አክሊል ትቀዳጃለህ "/1ኛ ጴጥሮስ 5፡4/፡፡ በR. Stanley ተፅፎ በBlesing Books in Vellore; India የታተመው "Preachers and People መጽሐፍ በዚህ ትምህርት ያሉ እውነታዎችን ለመገንዘብ እጅጉን ያግዛል፡፡

# ክፍል አራት
# መንጋውን መጠበቅ

## ትምህርት አንድ፡- ቃሉን ስበክ

ስብከት በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረተና ፍሬ የሚያፈራ ሊሆን ይገባል፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት በብሉይ ኪዳን የመነቃቃት ተግባር ትልቅ ሚና አለው፡፡ በተለይም በንጉሥ ኢዮሲያስ ዘመን /2ኛ ነገስት 22፡-11/፣ ዕዝራ /ዕዝራ 7፡10/፣ አሞጽ የእግዚአብሔር ቃል የሆነውን የረሃብ ዘመን እንደሚመጣ ተነበየ /አሞጽ 8፡12/፡፡ ይህም ቀን በኛ ላይ ይሆናል፡፡ በብዙ መድረኮች ታሪኮች ይነበባሉ፣ ልምዶች ይነገራሉ፣ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር ቃል የሚነገረው ጥቂት ነው፡፡

ወተት ጥሩ ነው ግን እስከ መቼ? አጥንት መጋጥ የሚባል ነገር ከሌለ ማደግ ከቶውን አይታሰብም፡፡ ጳውሎስ ቃሉን ስበክ ብሏልና /2ኛ ጢሞቴዎስ 4፡2-4/፡፡

***ውይይት፡-*** ከላይ የተጠቀሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በማጥናት ጥርት ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ከመስበክ አንፃር ምን እንደሆነ ተወያዩ፡፡

## ትምህርት ሁለት፡- መነቃቃት ስለምን ያስፈልገናል?

መነቃቃት የሕይወት መጨረሻ አይደለም፤ ወደ መጨረሻ የሚያደረስ የወንጌል ሥርጭት እንጂ! መነቃቃት የወንጌል ሥርጭትን ያፈራል፡፡ ዳዊት ሲፀልይ" የማዳንህን ደስታ ፍጠርልኝ … በዚህም ያልዳኑ ይቀየራሉ /መዝሙር 51፡12-13/፤ የዌልስ መነቃቃት ፈር ቀዳጅ ኢቫን ሮበርትስ "ጌታ ሆይ ቤተክርስቲያንን በመቁረስ አለምን ባርክ" ብሏል፡፡

ባለፋት ዘመናት ከተደረጉት መነቃቃቶች አብዛኛዎቹ የታላቁን ተልዕኮ መተግበርንና የወንጌል ሥርጭትን ወልዷል፡፡ አንዳንዶቹ ግን ወዲያው ከስመዋል፤ ይህም የጠበቀ የወንጌል ሥርጭትና ነፍሳትን የመማረክ ሥራ እንዳይሠሩ መሪዎችን ያደክማል፡፡

እግዚአብሔር ሰውን ለማስደሰት ወይ ለማዝናናት ብሎ መንፈሱን በሰው ላይ አያወርድም፡፡ መንፈሱን በሰው ሲያፈስ ትኩረቱ ለአለም ነው፡፡ ከብዙ ምክንያቶች አንዱ መነቃቃትን ለምን ለምን እንደምንፈልግ አለማወቃችን ነው፡፡

***ውይይት፡-*** አንተ ያለህበት ጉባኤ መነቃቃትን እንደፈለገ የሚያሳይ ሁኔታ አለ?
በዚህ ጉዳይ በአንድ ላይ ፀልዩ፡፡

## ትምህርት ሶስት፡- ስለ መነቃቃት መስበክ

ሕዝብህ ቀዝቅዟል? በጌታ ጉዳዮች ፍላጎት የላቸውም? ይጣላሉ? ይቀናናሉ? በመንጋው መካከል ክፉ ንግግር አለ? ኃጢአት እየሠሩ ናቸው? ይሰርቃሉ? ይዋሻሉ? ወደ ክፉ ልምምድ እየሄዱ ናቸው? መነቃቃት ያስፈልጋቸዋል፡፡
መነቃቃት ማለት ወደ ሕይወት መመለስ ማለት ነው፡፡ በመነቃቃትና በወንጌል ሥርጭት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ፡፡ ኃጢአተኛው ወደ ኢየሱስ እንዲመጣ ወንጌል ሥርጭት ያስፈልጋል፡፡ ያመነ ሰው በኃጢአት ቢወድቅና በመንፈስ ቢቀዘቅዝ መነቃቃት ያስፈልገዋል፡፡

1. ***እንዴት መነቃቃት ይቻላል***? 2ኛ ዜና 7፡14 አራት አጭር ደረጃዎች ይሰቀምጣል፡-

ሀ. የዋህ መሆን

ለ. መፀለይ

ሐ. ፊቱን መፈለግ

መ. ከክፉ መንገዳቸው መመለስ

***2. የመነቃቃት ውጤቶች***

ሀ. እግዚአብሔር ፀሎትህን ይሰማል

ለ. ኃጢአትህን ይቅር ይላል

ሐ. ይፈውስሃል፤ ሕይወትህን ያበረታል፡፡ ለመነቃቃት ተጠምተሃል ወይ? በደንብ ስበክ፡፡

***ውይይት፡-*** ለመነቃቃት መጠማት እንዳለባቸው ለመንጋህ እንዴት ትናገራለህ? ማድረግ የምትችለውን እቅድ ፃፍ፡፡

## ትምህርት አራት፡- ለመነቃቃት መፀለይ

ለመነቃቃት ከልክ በላይ ጸሎትን መፈለግ አይገባም፡፡ ጸሎት ከሁሉ በላይ ቀላል ተግባር ነው፤ ይህም ራስን ማየትና ከኃጢአት ንስሐ መግባትን ያጠቃልላል /ራዕይ 2፡23/፡፡ ይህም ከጌታ ጋር ያለንን መሐላ ቃል መስበራችንን የምናይበት ነው /መኃልየ መኃልይ ዘሰለሞን 5፡1-6/ እና ሌሎችን የበደልንበትን ሁሉ የምንጥል ነው /ማቴዎስ 5፡23-24/፡፡

ፀሎት ወደ ትህትና ይመራል፤ ምክንያቱም በእግዚአብሔር ፊት ስንሆን ባዶነታችንን እናውቃለን፡፡ የእርሱን ፅድቅ እናያለን /ኢሳይያስ 6፡1-5/፡፡ ይህም የኛን አለመብቃትና ለእርዳታ ወደ እግዚአብሔር መጮህን ያመለክታል /ማቴዎስ 26፡41)፡፡ እንደዚህ አይነት መስዋዕትነት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኛል፣ እሳቱንም ይልካል /መዝሙር 51፡17-19/፡፡ ኤልያስ መሰዊያውን ባዘጋጀ ጊዜ እሳቱ ወርዷል፤ ኢየሱስ ሲፀልይ ሰማይ ተከፍቷል፤ የቀድሞዋ ቤተክርስቲያን ስትፀልይ ምድር ተናውጣለች፡፡ ፀሎት የመንፈስ ቅዱስ ጉልበት በምድር ላይ እንዲበዛ ያደርጋል፡፡ እግዚአብሔር ሕዝቡ በጉልበቱ እንዲንበረከክ ያደርጋል፡፡

ውይይት፡ ደጋግመህ ከላይ የተጠቀሱትን ጥቅሶች አንብብ፤ በአያንዳንዳቸው ላይ ፀልይበት፣ ራስህንም ስጥ፡፡

## ትምህርት 5፡- ፍቅር የአዋቂ አገልግሎት

ከዕርገቱ ቀደም ብሎ ጌታ ኢየሱስ ጴጥሮስን አንድ ጥያቄ ጠየቀው፡- ትወደኛለህን? /ዮሐንስ 21፡15-17/፡፡ ፍቅር ለአማኞች አገልግሎት መሠረታዊ ድጋፍ ነው፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ ሲጠራው መጀመሪያ አሣ አጥማጅ ነበር /ማቴዎስ 4፡19/፣ አሁን ደግሞ ሰው አጥማጅ እንዲሆን እያደረገው ነው /ዮሐንስ 21፡15-17/፡፡ ነፍሳትን ለመማረክም ሆነ ለመጠበቅ ፍቅር ወሰኝ ነው፡፡ አንደኛው ፍቅር ለጠፉት፤ ሁለተኛው ፍቅር ለተገኙት! ነፍሳት ወደ ቤቱ ሊገቡ ይገባል፤ ወደ ላይም ሊነሡ ይገባል፡፡

***ውይይት***፡- ለጠፉት ያሳየው ፍቅር የተግባር ምሳሌ አለ? ለዳኑትስ?

## ትምህርት 6፡- የሕዝብ አገልግሎት

የእረኞች ትልቁ ዕድል በአደባባይ ቆመው ወንጌልን መስበክ ነው፤ ይህም ጥናትን ልምድ ማድረግ፣ ያልዳኑትን ወደ መዳን መቀየር፣ አማኞችን ማጠናከርን ያካትታል፡፡ ወንጌል ሥርጭትንና መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን ማቃናት፣ ማመስገንና ማስጠንቀቅን በእግዚአብሔር ምክር አድርጎ ማካተት አለበት /ሐዋሪያት ሥራ 20፡27/፡፡

በሕዝብ ፊት መፀለይና በድብቅ መፀለይን መማር አለበት፡፡ በመጋቢነት ፀሎት ሕዝቡን በአምልኮ ወደ አግዚአብሔር መገኘት ከፍ ማድረግ አለበት፡፡

መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል ማንበብ፣ በመስጠትና በመለየት ማንበብ እንዲሁም መማር አለበት፡፡ ስለዚህ ሁሉም ሊረዳ ይችላል /ነህምያ 8፡8/፤ የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ለመመገብ የተሰጠ /ሐዋሪያት ሥራ 20፡28/ በመስበክና ከግለሰብ ሕይወት ጋር የሚዛመዱ ጥቅሶችን በማጥናት መንጋውን ከሐሰት ትምህርትና አስተማሪዎች የሚጠብቅ /ሐዋሪያት ሥራ 20፡29-30/፣ በመንጋው መካከል ላሉ ድሆች የማሰብ ኃላፊነት ያለው /ሐዋሪያት ሥራ 11፡29-30/ መሆን አለበት፡፡

ሰዎች ሁሉ እንዲሁም ስለጠፉት የሚያስብ፣ ቤተክርስቲያን ወደ ሌሎች ቦታ የመድረስን ትምህርት ለሕዝቡ የሚያስተምር፤ በስብከቱ መጨረሻ በእግዚአብሔር ስም ሕዝቡን የመባረክ ኃላፊነት ያለው ሊሆን ይገባል /ዘኁልቁ 6፡23-26፤ ራዕይ 1፡4-5፡፡ በ2ኛ ቆሮንቶስ 2፡16 የጠበቀ ጥያቄ ለዚህ ሁሉ ማን ሊበቃ ይችላል? አስደናቂ መልሱ በ2ኛ ቆሮንቶስ 3፡5 "እግዚአብሔር ብቃታችን ነው" የሚል ነው!

ውይይት፡- ከላይ ከተጠቀሱት ኃላፊነቶች ለማሟላት ከባድ የሚሆነው የቱ ነው? ወሳኝ የምትለውስ?

## ትምህርት 7፡- የአገልግሎት ሚዛን መጠበቅ

ከመስመር የወጣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ባህሪይ ከአገልግሎታችን ማስወገድ አለብን፡፡ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር መስበክ፣ ኃጢአትን መታገስ ስለማይቻለው ቅድስና መናገር፣ ስለ ሲኦል እንዲሁም ገነት፣ ከጌታ ጋር ስላለው ሕብረትና መሰጠት፣ እርሱን ስለማገልገልና ስለ ወንጌል ስርጭት፣ ስለ መነቃቃት ወዘተ… ጳውሎስ "የእግዚአብሔርን ምክር ለእናንተ ከመናገር ዝም አልልም ብሏል፡፡"

የስብከትን ርዕሶች በሙሉ መዝግቦ ማስቀመጥ ተገቢ ነው፤ ይህም ለብዙ ቀን የሚሆን ስብከት ታዘጋጃለህ፣ ቀድመህም ትሠብካለህ፡፡ በዚህ ሂደት አእምሮህም ልብህም ስለዝግጅትህ ብዙ መረጃ ሊያገኝ ይችላል፤ ይጠነክራል፤ ከእግዚአብሔር ምክር እውነታን እንዳትቀንስ ይጠቅምሃል፡፡

***የቤት ሥራ፡-*** ለ3 ወራት የሚሆን የስብከት ርዕሶችን በመፃፍ ማስታወሻ ያዝ፡፡

## ትምህርት 8፡- ወቅታዊ ግምገማ

ራስን ለመገምገም ወርሃዊና ዕለታዊ፣ ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ በአመት ቀናትን አቅዶ ማስቀመጥ ጥሩ ነው፡፡ ግብህን ታውቃለህ? ፍሬ አይተህበታል? ስኬቶችንና በረከቶችን ለሚቀጥለው ደረጃ አይናችንን

እንድናነሣ ማድረግ ችለዋል፤ ወይም ድንገት አንድ ችግር ቢመጣ የተማርነውን ሁሉ የማያስረሳ ይሆናል፡፡ በአገልግሎታችን ግልጽ የሆነ አመለካከትና ቆራጥነት ያለው ከሆነ ጠቃሚ ግምገማ ለማድረግ ያግዛል፡፡ ስህተቶች መታረም አለባቸው፡፡ ሐዋሪያው ዮሐንስ ሁለት ጊዜ መላእክትን እንደ ማምለክ አድርጎት ነበር /ራዕይ 19፡10 22፡8-9/፣ ሆኖም መመለስን ተምሯል፡፡ ኢየሱስ "ኑ ተለዩ" ብሎአል፡፡

***ውይይት***፡- ከግብ ልታደርሳቸው የምትፈልጋቸው የአገልግሎትህ ግቦች ምንድናቸው?

## ትምህርት 9፡- የምክር አገልግሎት

እረኛ ስለ በጎች ደህንነት ስለ ችግራቸው በግል ሊያናግራቸው ይገባል፡፡ ሚስጥራቸውን በሚናገሩ ጊዜ ልዩነቶችን ማስወገድ መቻል አለበት /ማቴዎስ 18፡15-17/፡፡ አንድ መገንዘብ ያለበት ነገር ሁልጊዜ በሁሉ ቦታ በዚህ ምድር ላይ ጌታ ኢየሱስን ወክሎ ስለሆነ ያለው መተግበር አለበት፡፡

ውይይት፡- ለክርስቲያናዊ ምክር ዕድል የሚፈጥሩ ክስተቶች በመንደርህ ላይ አሉ?

## ትምህርት 10፡- ሕብረትን ማነሣሣት

ሕብረት ከክርስቶስና ከቤተሰቡ ጋር ባለ ቁርኝነት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ አማኞች በአንድነት መሆን፣ ማውራት፣ መፀለይ፣ መዘመር፣ መሳቅና ማልቀስ አለባቸው /1ኛ ዮሐንስ 1፡7 እና 1፡3/፡፡

### 1. የሕብረት አላማ

ሀ. አንዱ አንዱን ለማበረታታት፣ በአገልግሎትና በደስታ ጊዜ አብሮ ማዕድ ለመቁረስ፣ ወንዶች ማዕድ ለመቁረስ፣ ሴቶች ሐሳብ ለማካፈል ወጣቶች ለመጫወት፣ ይህ ሁሉ በአግዚአብሔር አለም ላይ አለ፡፡ አማኞች ጠንካሮችና በውጪ ያሉትን የሚማርኩ መሆን አለባቸው፡፡

ለ. በሕይወት ውስጥ ከባድ ከሆኑ ጉዳዮች ሁሉ መተናነጽና መደጋገፍ ልብ የሚያደክምና ሸክም የሚሆኑ ነገሮችን መነጋገር፡፡

ሐ. ለጋራ ጥቅም ልምዶችን ለማካፈል፤ የኛ ምስክርነት ወዳጆቻችን ተመሣሣይ ስህተት እንዳይሰሩ ይረዳቸዋል፡፡

መ. ፀልየን የተመለሰልንን ጥልቅ ስሜታችንን ለማካፈል /መዝሙር 50፡15/ ይህ

ሌሎች እንዲፀልዩ ያበረታታል፡፡

ሠ. ከሚያለቅሱ ጋር ማልቀስ /ሮሜ 12፡15/፤ በሐዘን ውስጥ ያሉትን እምባቸውንና ለቅሶአቸውን ስንካፈል ደስ ይላቸዋል፡፡
ረ. የደከሙ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ያደርጋል፡፡

2. **የአማኞች ህብረት ውጤት**

- በብርሃን መመላለስን ያስተምራል /1ኛ ዮሐ 1፡7/
- አብሮ ማዘንን አንማራለን /ፊልጵስዩስ 3፡10/
- አብሮ ማገልገልን እንማራለን /ቆላስይስ 4፡1-7/
- አንዱ ሌላውን ማጽናናት እንማራለን /1ኛ ተሰሎንቄ 4፡18/
- አንዱ ለሌላው መፀለይን እንማራለን /1ኛ ተሰሎንቄ 5፡25/
- አንዱ የሌላውን ሸክም መጋራት እንማራለን /ገላትያ 6፡2/
- ከሚደሰቱ ጋር መደሰትን እንለምዳለን /ሮሜ 12፡15/፤ ደስታ ይተላለፋል፡፡
- ለጌታ እናድጋለን፤ ጎልተንም እንታያለን /2ኛ ጴጥሮስ 3፡18/፡፡

***ውይይት*** ፡- በቤተክርስቲያንህ የምታደርገው ጠቃሚ ህብረት ምን አይነት ነው?

## ትምህርት 11 የወንጌል ሥርጭት ስብከት

የእግዚአብሔር አገልጋዮች ባላቸው ስብከት ገደብ የሌለው ርዕስ አላቸው፡፡ ነገር ግን ርዕሱ ሁሉ ሚዛናዊ መሆን አለበት፡፡ የደህንነት ስብከት መሰበክ አስፈላጊ አይደለም ማለት በራሱ አደጋ አለው፣ ምክንያቱም ሁሉም በአማኝ ላይ ይበረታል እንጂ አዲስ ለማምጣት ደካማ ነው፡፡
ብዙ ሰዎች የቤተክርስቲያን አባል ሊሆኑ ቢችሉም የክርስቶስ አካል የሆነቸው እውነተኛ ቤተክርስቲያን አባል ግን ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ደህንነት እርግጥ ነው፤ ለዘላለም ግለሰቡ ካልጠፋ በስተቀር ባልዳኑ ግለሰቦች የተገነባች ቤተክርስቲያን ሕይወት የላትም፤ መልእክትም የሚለውጥም ኃይል ሊኖራት ከቶውን አይችልም፡፡
የቤተክርስቲያን መሪዎች መገንዘብ ያለባቸው በሕዝቅኤል 33፡6 ላይ የተናገረው መሳጭ ቃል ነው፡፡

***የቤት ሥራ***፡- ለወንጌል ሥርጭት ስብከት የሚረዱህ ጥቅሶች ዘርዝር፡፡

## ትምህርት 12፡- የደህንነት ማረጋገጫ

ከመንጋዎችህ መካከል አንዱ በትክክል ስለመዳኑ እርግጠኛ ባይሆንና ቢጠይቅህ አንድ ሰው ሌላውን በመንፈሳዊ ነገር ከመረዳቱ በፊት እርሱ እርግጠኛ መሆን አለበት። እንደዳንን ድንገት ብንሞት ወደ ሰማይ ወዲያው እንደምንሄድ ማረጋጋጫ ማግኘት ልበ ሙሉነት ይፈጥራል (ዮሐንስ 10፡28-29)።

### 1. የደህንንት ማረጋገጫ መሰረት

ሀ. የመንፈስ ቅዱስ ምስክርነት (ሮሜ 8፡16፣ ገላትያ 4፡6)

ለ. የእግዚአብሔር ቃል (1ኛ ዮሐንስ 5፡10፣ 13፣ ዮሐንስ 5፡24፣ ሮሜ 10፡13) ለሰይጣን እንደዚህ በለው፡- “በክርስቶስ የሚያምን የዘላላም ሕይወት አለው” ብሎ መጽሐፍ ቅዱስ ነግሮኛል። በ ----------------- ቀን (ቀኑን አስፍሩ) በክርስቶስ አምኛለሁ፤ ስለዚህ የዘላላም ሕይወት አለኝ። ድኛለሁ፣ ኃጢአቴም ተወግዶልኛል፣ ወደ ሰማይም እሄዳለሁ።

ሐ. የተለወጠ ሕይወት (1ኛ ዮሐንስ 3፡14፣ 2ኛ ቆሮንቶስ 5፡17)

### 2. የደህንነታችን ማረጋገጫ የሚያደናቅፉ ነገሮች

- የእግዚአብሔርን ቃል አለማመን
- አለማዊነት
- መንፈስ ቅዱስ አለመሞላት (ዮሐንስ 7፡37-39)
- ኃጢአትና ማፈግፍግ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)

***ጥንቃቄ፡-*** *እኔ ድኛለሁ በማለት ሰውን ለማሳመን ጥረት አታድርግ። መንፈስ ቅዱስ ብቻ በሰሙት ቃል ሰዎችን የሚያሳምንና የዳኑትንም እንዲመሰክሩ የሚያደረገው።*

***የቤት ሥራ፡-*** ተማሪዎች በሁለት ሁለት ሆነው ይነጋገሩ። አንዱ አማኝ አንዱ ደግሞ አዲስ ሰው /አማኝ/ ሆኖ የእግዚአብሔር ቃል እውነት ማረጋገጫ እርስ በእርስ በመስጠት ያስረዱ።

## ትምህርት 13፡- አዲስ አማኝ ማስተማር

የአዲስ አማኝ የመጀመሪያ ሳምንታት ወሳኝ ናቸው፤ ምክንያቱም ይህ ወቅት ሰይጣን መጠራጠርን ጨምሮ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ ለማደናቀፋ የሚተጋበት ነው። በየቀኑ አግኘው፤ አብረህ መጽሐፍ ቅዱስን አንብብ፣

ፀልይም፡፡ ስለ አዲሱ እምነት የተሰማውን ሁሉ እንዲነግርህ ጠይቀው፤ ይህም እራሱን ያጠነክረዋል፤ ለሌሎችም መዳን ምስክርነት እንዲተጋ ያስችለዋል፡፡

የአንተ ቤተክርስቲያን በእርግጠኝነት እስከ ጥምቀት ድረስ ተገቢ የሆነ ትምህርት ማስተማር አለባት፤ አንድ ሰው ከተለወጠ በኂላ ወዲያው ትምህርት መከታተል አለበት፡፡ አዲስ አማኝ በጥልቀት ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ቁርኝት መፍጠር አለበት፤ በሕይወት እድገት ጠቃሚና ወደር የሌለው ወተት ስለሆነ፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አባል መሆኑን ማረጋገጥህን አትዘንጋ (1ኛ ጴጥሮስ 2፡2)፡፡

ትልቅና ጥሩ እድል፡- አዲስ አማኝን ከነባሩ ጋር ማቆራኘት፣ ወንድምን እህትን፣ ትልቁ ትንሹን እንደ የደረጃቸው ማጣመር እግዚአብሔር መውደድንና ፀሎትን እንዲለማመዱ ያደርጋል፡፡

***ውይይት፡-*** አዲስ አማኞች እንዴት ነው በቤተክርስቲያንህ ውስጥ የምታበረታታው? ትልቁንና ትንሹን ወንድም እንዴት ታጣምራቸዋለህ?

## ትምህርት 14፡- ምስክርነት ለምን?

*የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፡- ማቴዎስ 10፡32-33፣ ሮሜ 10፡9*

**1. ክርስቶስን መቀበልና ማመን ስለሚያስፈልግ**

ሀ. ክርስቶስ አዟል /ማቴዎስ 10፡32-33/

ለ. የእርዳታ ምንጭና ሕይወታችን የሚያጠናክር ነው፤ የሚመስክር አማኝ ወደ ኂላ አያፈገፍግም፡፡

ሐ. ብዙ ችግሮችን ይፈታል፤ ሌሎች ስለ አቋምህ ያውቃሉ፣ ያከብሩሃልም፡፡

መ. ምክንያቱም ክርስቶስ ለእናንተ ብዙ አድርጎልሃልና፡፡

**2. ክርስቶስን የማመን ዘዴ**

ሀ. በአደባባይ፣ በቤተክርስቲያን፣ አምልኮ ጊዜ፣ በፀሎት ኘሮግራም፣ በምስክርነት ኘሮግራሞች ወዘተ……

ለ. በየቀኑ ከጓደኞች ዘመዶችና ጐረቤቶች ጋር መነጋገር፡፡ በተለያዩ ጊዜ የሚቻል ዘዴ ነው፤ ብሎም ተገቢ ነው፡፡

ሐ. በአደባባይ መጠመቅና ቤተክርስቲያን መቀላቀል

መ. በየጊዜው የቤተክርስቲያን አምልኮና ሥርዓቶችን መሳተፍ

ሠ. የአደባባይ ንስሐ ሁልጊዜ የተለመደ መሆን አለበት /ኤርሚያስ 20፡9/፡፡

***ማስታወሻ***- ክርስቲያን ነኝ የሚል፣ ነገር ግን ያልመሰከረ ሰው ይታሠራል፣ ይሞታልም፡፡

***ውይይት*** - ወዳጅነት ለምስክርነት የጠቀመህ ሁኔታ አለ? በወዳጅነት ምስክርነትን እንዴት መጀመር ይቻላል?

## ትምህርት 15፡- የሚማርኩ ሰዎችን ማስጀመር

"ማንን እልካለሁ? ማንስ ይሄድልናል?" የሚለው ጥሪ እግዚአብሔር በማድረግ ላይ ነው /ኢሳይያስ 6፡8/፡፡ ይህ ልመና ዛሬም እውነት ነው፡፡ ሠራተኞች ግን ጥቂት ናቸው /ሉቃስ 10፡2/፡፡ ቤተክርስቲያን ግን የሚልኩና የሚላኩትን ሰዎች ቁጥር እየጨመረ ያለ ይመስላል፤ ነገር ግን ይህ በአሳዛኝ ሁኔታ ተገላቢጦሹ ይሳላል፡፡

ስለዚህ ምን ታርደርጋለህ? አሁን ያለውን ሁኔታ ለመቀየር የተቻለህን አድርግ አራት ነገሮችን ማድረግ ትችላለህ፡-

1. በምሳሌነት መምራት
2. ነፍሳትን በመማረክ ሂደት ያተኮረ ስብከትና ሥልጠና መስጠት
3. የስልጠና ጊዜና ሁኔታዎች ማመቻቸት
4. ነፍሳትን በመማረክ የሚረዳ መጽሐፍ በሳምንት የማጥናት ልምድ አሳድግ፤ ለሁሉም ሰው ይሁን! ነፍሳትን የሚያሸንፉ የሚማርኩ፣ የሚመሰክሩ ሰዎችን ኃጢአት ወይም ያላመኑ ሰዎች ወዳሉበት የመላክን ጥሪ ከዘነጋህ ፍሬያማ አትሆንም፡፡

***የቤት ሥራ***፡- ምክር እንዲሆኑ ለቤተክርስቲያን አባላት እንዴት ምሳሌ መሆን ይቻላል? ሶስት ሓሳቦችን አዘጋጅ፡፡

## ትምህርት 16፡- ነፍሳትን የመማረክ ምክንያት

አንዳንዶች ሰባኪዎች ሊሆኑ ተጠርቷዋል፤ ሁሉም አማኝ ግን ነፍሳትን እንዲማርኩ ተጠርተዋል፡፡ ነፍሳትን በመማረክ የሚገኘውን ደስታ ለሕዝብህ አስተምር፡፡ "ነፍሳትን መማረክ በትክክለኛ ጉልበት፣ ሰውና ጊዜ ከትክክለኛው አዳኝ ጋር እንዲገናኝ ያደርጋል" (ቢል ሰንዴይ) ፡፡

**1. ነፍሳትን የመማረክ አብይ ምክንያቶች**

ሀ. የነፍሣት ፍላጎት /ማርቆስ 8፡35-38/

ለ. የሲኦል መኖር

ሐ. ለሁሉም ኃጢአተኛ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መከራን መቀበሉ

መ. የአለም ከንቱነትና ሞኝነት

ሠ. የቤተሰባዊነት በሰማያዊ አካል የመዋሃድ ፍላጎት

ረ. የሰማያዊ ክብር

ሰ. ታማኝ ነፍሳትን ለሚማርኩ የተዘጋጀ ሽልማት

**2. የሠራተኞች አስፈላጊነት**

ሀ. አምኖ የዳነና እርግጠኛ የሆነ

ለ. ንፁህ ሕይወት መኖር የሚችል

ሐ. በፍቅር መንፈስ የሚሠራ

መ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውቀት ያለውና እንዴት እንደሚጠቀም የሚያውቅ፡፡

ሠ. የፀሎት ሠው

ረ. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ

ሰ. ለነፍሳት ፍቅር ያለው፡፡

***ውይይት፡-*** ለነፍሳት ማራኪ ሰው ከላይ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ለምን አስፈላጊ ሆነ?

## ትምህርት 17፡- እንዴት መመስከር ያስፈልጋል?

**1. እንዴት መመስከር ይቻላል**

ሀ. ስለ ክርስቶስ መመስከር፣ መጀመሪያ ራሱ የዳንበት መሆን አለበት

ለ. የተለወጥክበትን የሕይወት ምስክርነት ተናገር

ሐ. ፀልየህ የተመለሰልህን ፀሎቶችን ተናገር /መዝሙር 50፡15/

መ. ክርስቶስ እንዴት የሚያረካ እንደሆነ ተናገር

ሠ. በኃጢአትና በፈተና ላይ ያለህን የድል ተሞክሮ አካፍል

ረ. ከመጽሐፍ ቅዱስ የምትወደውን ጥቅስ ተናገር፤ ከዚህ በፊት እግዚአብሔር እንዴት በቃሉ በኩል እንደተናገረህ አካፍል፡፡

ሰ. ለጓደኛህ የክርስቶስን ወንጌልን ስጥ፣ ስለ ጌታም ንገረው፡፡

**2. ክርስቶስን ማመን የሚከለክሉ እንቅፋቶች**

ሀ. ሰውን መፍራት (2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡7፣1ኛ ዮሐንስ 4፡18፣ ፊልጵስዮስ 4፡13)

ለ. ማፈር (2ኛ ጢሞቴዎስ1፡8

ሐ. ያልነፃ ሕይወት (1ኛ ዮሐንስ 1፡9

***ማስታወሻ፡-*** ሕዝቄል 33፡8 አንብብ፤ የምስክርነት እንቅፋቶች ምንድናቸው፡፡

***የቤት ሥራ፡-*** አንተ የተለወጥክበትን ምስክርነት አዘጋጅ፤ በሕይወትህ የመጣውን ለውጥ አካፍል።

## ትምህርት 18፡- የምስክር እቅድ

1. ***አራት መንፈሳዊ ሕጎች፡-*** ምናልባትም ለምስክርነት የሚጠቀሙ ይሆናሉ።

2. ***ቃል የሌለው መጽሐፍ፡-*** ከጥቁር፣ ቀይ፣ ነጭ፣ ወርቅና አረንዴ ገጾች የወጣለት አገልግሎት አላቸው፤ በተለይም ለልጆች!

3. ሌላው ለልጆች የመዳንን መንገድ የምናሳይበት ዘዴ ***ጣቶቻችንን በመጠቀም***፤ ሌላ መሳሪያም ሆነ መጽሐፍ አያስፈልግም፡

*የመጀመሪያ ጣት፡- እግዚአብሔር ይወድሃል /ዮሐንስ 3፡16/*

*ሁለተኛ ጣት፡- ሁሉም ኃጢአት ሠርቷል /ሮሜ 3፡23/*

*ሶስተኛ ጣት፡- ክርስቶስ ስለኃጢአትህ ሞቶልሃል /1ኛ ቆሮንቶስ 15፡3/*

*አራተኛ ጣት፡- ክርስቶስ ለኃጢአትህ እንደ ሞተልህ እመን /ዮሐንስ 1፡12/*

*አምስተኛ ጣት፡ ስታምን የዘላለም ሕይወት ታገኛለህ /ሮሜ 6፡23/*

4. አንዳንዶች የሮማውያንን መንገድ ይጠቀማሉ፤ ስትጠቀም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማጣቀስ ተጠቀም፡-

*የሰው ፋላጎት /ሮሜ 3፡23/*

*የኃጢአት ቅጣት /ሮሜ 6፡23/*

*የእግዚአብሔር አቅርቦት /ሮሜ 5፡8/*

*የሰው ምላሽ ሮሜ /10፡9/*

በአዲስ ኪዳን የተመለከቱ አንድ ሰው አብሮህ የሚያነባቸው በደህንነት ላይ ያተኮሩ ጥቅሶች ይኑሩህ። በመጽሐፍ ቅዱስ ዝግጅት ወቅት ያጋጠመህን ተግዳሮቶች ያሳለፍክበትን ጨምሮ አካፍል። በገጽ አናት ላይ አንድ ቁጥር ምልክት አኑርበት /ሮሜ 3፡23/። የምታሰምርበትን ማርከር ተጠቀም፣ በቀላሉ ለማግኘት ይረዳሃል። ከሥር ለገጽ ሁለት ቦታ ስጥ /ሮሜ 6፡23/ ምልክት አድርግ። በዚህ መንገድ ቀጥሎ ላሉት ጥቅሶች ምልክት አድርግ /ዮሐንስ 1፡12 ፣1ኛ ዮሐንስ 1፡9፣ *ራዕይ* 3፡20፣ 1ኛ ዮሐንስ 5፡10-13/።

**የቤት ሥራ፡-** ከእነዚህ የትኛውን እንደምታስተምር ወስን፤ በቁጥሮቹ መሠረት ክፍሉን ደልድል፤ የሰሚና የነፍስ ማራኪ ተግባር አሰራ። ሲጨርሱ

ሚናቸውን ቀይረው እንዲሰሩ አድርግ፤ ሁሉም ንግግር በግልጽ ጥያቄ እንዲያልቅ አድርግ፣ ከዚያም ለይቅርታ ለፀሎት ጠይቅ።

## ትምህር 19፡- ስለመስጠት ማስተማር

መስጠት የሚባል ነገር፣ ለሕዝብህ ከባድ ነገር ሊሆን ይችላል። ሐሳቡ በልባቸው መተከል አለበት፤ ምክንያቱም ደስታን ይሰጣቸዋል።

ለጌታ እንዴት እንሰጣለን?

1. በዘዴ፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2 ከመጀመሪያ ቀን ጀምሮ አመቱን ሙሉ መሰጠትን ጉዳያችን እናድርግ፤ ስለታማኝነታችን እግዚአብሔር ይሸልመናል።

2. በግል፡- 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2 "ሁላችሁም /እያንዳንዳችሁ/" የሚለው የቤተሰብ ራስን ብቻ ሳይሆን፣ ልጆችንም እናቶችንም፣ ድሆችንም፣ ሐብታሞችንም ያሳትፋል።

3. እንደ አቅማችን፡- "እግዚአብሔር እንደ ባረከህ መጠን" አሥራትንና ስጦታዎችን እንድንሰጥ ያስፈልጋል። ለሚሰጡት አግዚአብሔር አብዝቶ ይሰጣል።

4. በደስታ፡- /2ኛቆሮንቶስ 9፡7/ በማጉረምረም አይደለም

5. በመስዋዕትነት፡- /2ኛ ቆሮንቶስ 8፡2/ ከድህነታቸው ሰጡ፤ መበለቷ ሁለት ዲናር ሰጠች፣ እሱም ትዳሯ ነበር። እግዚአብሔር ስጦታችንን የሚመዝነው ካስቀረነው ጋር ነው፤ ከሰጠነው ጋር አይደለም!

6. በረከቶች ለአግዚአብሔር ከመስጠት የሚከተሉ ናቸው /ሐዋሪያት ስራ 20፡35፣ ማቴዎስ 6፡20፣ ሚልኪያስ 3፡10/።

*አንድ ተጨማሪ ቃል*፡- በደስታ የማትሰጥ ከሆንክ የአንተ ሕዝብ ላይሰጥ ይችላል!

***ውይይት***፡- ስጦታዎችን በመቀበል ረገድ የአንተ ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መንገድ ትከተላለች? ምን ማስተካከያ ለማድረግ አስበሃል።

## ትምህርት 20፡- እንዴት ማነሣሣት ይችላል?

እግዚአብሔር በፀጋው በኩል ለኃጢአት ይቅርታ አዘጋጅቷል። ንስሐ ስንገባ ያነፃናል /1ኛ ዮሐንስ 1፡9/ ኃጢአት ንስሐን ካላገኘ የልብ ጥንካሬ አደገኛነት አለው። በእብራውያን 3፡13 እንደተገለጸው ቀን ሣለ ሥራውን ለመሥራት እርስ በእርስ መነሣሣትና መቀስቀስ ይኖርብናል እንጂ በኃጢአት በመታለል

ልባችንን እልከኛ ማድረግ የለብንም። ኃጢአትን በማስወገድ ሕብረትን ማጠናከር ይቻላል።

አንደ መሪ በድካም ወይም ማፈግፈግ ላይ ያለውን ሰው በወንድማዊነት መንፈስ ለመምከርና ለማበረታታት መትጋት ግድ ይላል። ይህ እንዴት ይተገበራል፡-

1. ከመካከላቸውም ለስላሳና ጤናማ ግንኙነት ሊኖር ይገባል /ሉቃስ 9፡54-56፣ 1ኛ ተሰሎንቄ 2፡11፣ ማቴዎስ 12፡20/
2. በሙሉ ትህትና መናገር /ሮሜ 12፡10፣ ኤፌሶን 4፡2/
3. ቃሉን መጠቀም አለብን /2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16-4፡2፣ ቆላስይስ 3፡15/
4. በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሆን አለበት /ኤፌሶን 5፡18-19/
5. መንፈሳዊ መተራረም በግል ማድረግ /ማቴዎስ 18፡15/

ጳውሎስ ለሶስት ዓመታት ማንንም ሳለመገሰጽ በቀንም በሌሊትም ያነባ ነበር ሐዋሪያት ሥራ 20፡31/።

***ውይይት***፡- በማሳ መንገድ ለማረም መሞከር ምን ውጤት አለው? በሕዝብ ፊትስ? እንዴት ትከላከላለህ?

## ትምህርት 21፡- በመንጋው መካከል ኃጢአትን እንዴት እናስወግዳለን?

**1. *መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርህ* /ማቴዎስ 18፡15-17/**

ሀ. ለብቻ መታረም ያለበትን ማናገር

ለ. የማይሰማህ ከሆነ ሁለት ወይም ሶስት ምስክር ፊት አናግር

ሐ. በዚህም ልቡ ባይመለስ ለቤተክርስቲያን አሳውቅ

መ. አሁንም የማይመለስ ከሆነ ኃጢአተኛ ስለሆነ ተወው።

**2. የእርማት መንስኤዎች**

ሀ. የሐሰት ትምህርቶች /ቲቶ 1፡13/፣ የሐሰት ትምህርት አማኞች ሊያስት ይቻላል። ይህም መቆም አለበት።

ለ. የተገለጡ ኃጢአቶች /1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡20/

ሐ. የሥነ ምግባር ችግር /1ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-5/

**3. በኃጢአት ያለ ወንድምን እንዴት ማረም ይችላል**

ሀ. በትዕግሥት /1ኛ ቆሮንቶስ 10፡12/

ለ. በወዳጅነት /ማቴዎስ 7፡3-5/

ሐ. በፍቅር /1ኛ ቆሮንቶስ 13፡4/

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ

ሠ. በምስክርነትና በልምድ

***የቤት ሥራ፡-*** በጉባኤህ መካከል በኃጢአት ያለ ሰው አለ? እንዴት ልታደርግ አስበሃል?

## ትምህርት 22፡- ማፈግፈግ

ብዙ ጊዜ በጥንካሬውና በመንፈሳዊነቱ የምናውቀው ሰው ዛሬ ወደ ኃላ ቢያፈገፍግ፣ በ1ኛ ቆሮንቶስ 10፡12፣ ምሳሌ 16፡18 ላይ ያለውን ማስጠንቀቂያ አስታውስ። ወዲያው እንዲሁ አያፈገፍግም፤ ጥቂት ነገሮች እየተደመሩ ሕይወትን ይሸረሽራሉና!

***1. ወደኋላ ለማፈግፈግ እውነተኛ ምክንያቶች***

ሀ. አለመፀለይ

ለ. ቃሉን አለማንበብ /2ኛ ጢሞቴዎስ 2፡15/

ሐ. ቤተክርስቲያን አለመካፈል / እብራውያን 10፡25/

መ. መንፈስ ቅዱስን አለመታዘዝ /ኤፌሶን 4፡30/

ሠ. ክርስቶስን ከልብ አለማመን /ማቴዎስ 10፡33/

ረ. በብርሃን አለመመላለስ /1ኛ ዮሐንስ 1፡7/

**2. ወደኋላ የማፈግፈግ ውጤቶች**

ሀ. አቅምን፣ ሠላምን፣ ደስታንና እረፍትን ማጣት

ለ. ማጉረምረምና የቀን ሕይወትህ በጨለማ መከበብ

ሐ. ሽልማት ማጣት፣ በማጣቱም መሰቃየት

መ. አንዳንዶች እንደሚሉት ነፍሳትን ወደ ማጣት ይመራል

**3. የእግዚአብሔር ጥሪ ለመመለስ**

ኤር 3፡22 ፣ሆሴዕ 14፡4

እውነተኛ አማኝ ወደ ኃላ ማፈግፈግ አይኖርበትም /መዝሙር 101፡3/ "በፊቴ ኃጢአትን አላኖረም" ፤ አትኩረን መመልከት ያለብን ጳውሎስ ግቡ ክርስቶስ ነው! ይላል /እብራውያን 12፡2 ፣ ፊልጵስዩስ 3፡14/።

***የቤት ሥራ፡-*** በመንደርህ ውስጥ ወደ ኋላ ያፈገፈገ ካለ ራስህን ጠይቅ፤ እንዴት ወደ ክርስቶስ ህብረት እንደምትመልሳቸው አቅድ፣ ከጉባኤውም ጋር ፀልይላቸውም!

## ትምህርት 23፡- ፍቺ

ቤተክርስቲያንህ በፍቺ ባንዲራ የተሞላች ብትሆን ምን ታስባለህ? ፍቺ በአለም ላይ አንድ የቤተሰብን ችግር ያመለክታል፡፡ የቤተሰብን ዋጋ ስለሚሸረሽር የተወዛገበና የተዘበራረቀ ነው፡፡ ማህበረሰብን፣ የቤተክርስቲያንን አንድነት እና የክርስቶስ ቤተሰብነትን የሚያዛባ አደጋኛ ነቀርሳ ነው፡፡ ብዙዎች ሰይጣን በጋብቻ ላይ ባለው ጥቃት ማለትም ለብዙ ህይወት መዘበራረቅ፣ ቤተሰብ መፍረስ፣ የልብ መሰበር፣ ቤተሰብ የሌላቸው ልጆች፣ ዱርዬ ወጣቶች፣ ብቸኝነት እና ለመሳሰሉ እክሎች ያጋልጣል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ የፍቺ ምክንያት ዝሙት መሆኑን በማቴዎስ 19፡9 ያስቀምጣል፡፡ ከሌላ ወገን ጋር የግበረ ሥጋ ግንኙነት መፍጠር ማለት ነው፡፡ ካልተለመደውና አላአስፈላጊ ምክንያቶች ውጪ የተፈቀደ አይደለም፡፡ በጣም የተቸገሩ የትዳር አጋሮችን አስማምታችሁ ታውቃላችሁ? አንዳንድ አስተያየቶችን እንመልከት፡-

- የጋብቻ ውል የሕይወት ዘመን እንደሆነ በግልጽ ማስተማር “ሞት እስኪለየው ድረስ” /ማቴዎስ 19፡6/፡፡ ሁለት ግለሰቦች በጋብቻ ሲጣመሩ እግዚአብሔር ተአምራቶችን ያደርጋል፡፡ አንዱን አጋር በሞት በመውሰድ ብቻ ነው እግዚአብሔር ትዳርን የሚያፈርሰው፡፡
- ልጆች ካሉ ደህንነታቸው መታሰብ አለበት
- ፍቺ ሲከሰት ለሰው ፍፁም ውድቀት እንደሆነ መታወቅ ይኖርበታል
- ከጌታም ጋር እንዲሁም እርስ በርሳቸው እንዲስማሙ ጥረት ማድረግ፣ በጋራ ንስሐ መግባትና መመለስ ለማስታረቅ እጅጉን ይጠቅማል፡፡

ስምምነቱ ከተፈፀመ በኋላ ባልም ሚስትም እስከ ሞት ድረስ ባለመለያየት መሃላቸውን ማድረግ አለባቸው፡፡ በተደጋጋሚ እንዲፈላለጉ ማበረታታት ተገቢ ነው፤ ፍቅርን ይፈልጋሉና! የተቀደሰ ሕይወት እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን እንዲለምኑ መናገር ጥሩ ነው፡፡

***ውይይት***፡- በክርስቲያናዊ ቤተሰብ በጣም ወሳኝ የሆነ ነገር ምንድ ነው? የሚጐዱ ነገሮችስ ምንድናቸው?

## ትምህርት 24፡- ዝሙት

*መንፈሳዊ መሪ በዝሙት ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ማውራትና ማስተማር አለበት፡፡* ሰባተኛው ትዕዛዝ በፍፁም አልተሻረም /ዘፀአት 20፡14 እና 17/፡፡

በማየት ሳይቀር የሚደረገውን እግዚአብሔር እንዴት እንደሚጠላው ማየት ይቻላል፡፡ ዝሙት የሰሩትን ሁለቱም በድንጋይ ተወግረው እንዲሞቱ እግዚአብሔር እንዳዘዘ ታስታውሳለህ? ዘፍጥረት 20፡10 *መሪ የፆታዊ ስህተቶችን ለማስወገድ ፍፁም ጠንካራና አስተማሪ መሆን አለበት፡፡ ዝሙትና መዳራት ወደ ሲኦል እንደሚመራ ምንም ጥያቄ የለውም* /ምሳሌ 7፡9-17 ፣1ኛ ቆሮንቶስ 6፡9-10/ ፡፡

***ውይይት***፡- በአካባቢ ያሉ በዝሙት ኃጢአት ውስጥ ያሉ ሰዎች አሉ? ውጤቱስ?

## ትምህርት 25፡- ጥንቆላ

*የተለመደው ክስተት፡-* ወላጆች ልጆቻቸውን ለጥምቀት ወይም ለፀሎት ወደ ጉባኤ ያቀርቧቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የወገብ ልብሳቸው ቢገለጥ የታሰረ ክር ይታያል፤ ይህ ይፈቀዳልን? በፍፁም! *መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር* በጥንቆላና በአስማት ተግባር *መገኘት* የክፋት *ሥራ* እንደ ሆነ ይገልፃል /ዘፀአት 22፡18፣ ሐዋሪያት *ሥራ* 19፡18-19 *ገላትያ* 5፡20 እና *ራዕይ* 22፡15ን ተመልከት፡፡

የወንጌል ብርሃን እስኪደርስ ጥንቆላ እና የብርጭቆ *መርዝ* ምድርን በጨለማ *ያኖራታል*፡፡ ዛሬም ሰይጣን ሰዎች ወደ ቀድሞ ጨለማ እንዲመለሱ እያደረገ ነው፤ ክርስቶስ ግን ከጨለማ ጋር አይተባበርም፡፡ ጥንቆላንና አስማትን የሚለማመዱ ሁሉ መጨረሻቸው የእሳት ባህር ይሆናል (ራዕይ 21፡8)፡፡ እያንዳንዱ ሰው ማንን ማገልገል እንዳለበት መምረጥ አለበት፡፡ ነገር ግን ሁለት ጌቶችን ማገልገል አይችልም፤ ክርስቶስን በተቀበሉ ጊዜ ጥንቆላ መቃጠል አለበት፡፡

***ውይይት***፡- በአገርህ ውስጥ የትኛውን የጥንቆላ አይነት ነው ሰው የሚለማመደው? ይህን ለማስወገድ ምን ማድረግ ትችላለህ?

## ትምህርት 26 ፦ ስካርን እየተቃወሙ መስበክ ለምን አስፈለገ

ሁሉም ሰው መጠጥ መርገም እንደሆነ ይናገራል፤ ጠጪውን፣ ማህበረሰቡን እንዲሁም ቤተሰቡን ጭምር ያበላሻል። የአልኮል መጠጦችን በመቃወም የሚናገር የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አለ፤ እንደ ኃጢአት የማይወገድ ወደ ተጣበቀ ሱስ፣ ጎጂነት፣ ስርቆት፣ መግደል እና ጥፋት የሚመራ ነው። “የወይን ጠጅ አትጠጡ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ይሙላባችሁ /ኤፌሶን 5፡18/። ወይን የሚቆጣጠር ነገር ሲሆን፣ እግዚአሔር የፈጠረውን ሰውነት ሌላ እንዲሆን ያደርጋል። ከወይን ይልቅ በእግዚአብሔር መንፈስ የተሞላህ ሁን፤ እርሱም በደስታ በፍቅር፣ በሠላም፣ በፅናት፣ በትህትና፣ በመልካምነት፣ በየዋህነት እና ራስን በመግዛት ይሞላብሃል /ገላትያ 5፡22-23/።

ስለ መጥምቁ ዮሐንስ የተነገረውን ተመልከቱ፦ በእግዚአብሔር ፊት ታላቅ ይሆናል ወይንም ሆነ ሌላ መጠጥ አይጠጣም /ሉቃስ 1፡15/። የግሪክ ቃል ስለ ወይን የሚጠቀመው /oinos/ አይኖስን ነው፤ ይኸውም የፈላ እርሾ ያለበት መጠጥ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲናገር ወይንን በአሮጌ ዕቃ አታስቀምጥ ይሰብረዋል ይላል። በመጀመሪያ በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሰው በዘፍጥረት 9፡21 ኖህ ጠጥቶ ራቁቱን በመወደቀ ጊዜ ነው፦

1. ወይን ሞኞች እንድንሆን ያደርጋል፣ ያስታልም /ምሳሌ 20፡1፣ ሆሴ 4፡11/።
2. የቤተክርስቲያን መሪዎች ለወይን የተገዙ መሆን የለባቸውም /ቲቶ 1፡7/፤ የግሪኩ ቃል /paroinos=para +oinos “አትቅረብ” የሚለውን አሳብ ያስቀምጣል።
3. ወይን ሱስ ይሆናል፣ ያጠፋልም /ምሳሌ 23፡29-35/።
4. ጥበብን በማበላሸት ምክንያት አልባ ያደርጋል፣ አገልግሎትንም ይጎዳል /ኢሳይያስ 28፡7/።
5. መጠጥ ወይም ሰካር ከሌሎች ኃጢአቶች ጋር በተገናኘ አብሮ ተነስቷል።

**አማኝ መጠጣት የሌለበት ምክንያት**

1. አካሉ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ስለሆነ መርከስ የለበትም።
2. አማኙ የክርስቶስ መስካሪ ስለሆነ፣ ትንሽ ሲጠጣ ቢገኝ ደካማ ወንድሙ ከእርሱ በባሰ ሁኔታ ብዙ በመጣጠት ይጎዳል።
3. የወንድሙ ጠባቂ ስለሆነ /ዘፍጥረት 4፡9/፣ ወንድሙ ጤናማ ሕይወት እንዲኖር የመርዳት ኃላፊነት አለበት፤ በተጨማሪም አማኝ ሆነ ያላመነ ከመጠጥ መለየት ያለበት ብዙ ምክያቶች አሉ፡-

- ገንዘብ ማባከን ነው /ዘዳግም 21፡18-21፣ ምሳ 23፡20/
- ስለሌሎች ደህንነት
- ቤተሰብን ስለሚያፈርስ

ጠንካራ መጠጥ ከጦርነትና ከረሐብ በላይ ጥፋት የማድረስ አቅም አለው፤ ከአንዱ ብርጭቆም ወደሌላው ይመራል /ዊሊያም ግለስቶን/። መጽሐፍ ቅዱስ መፍተሔው ፈጽሞ መራቅ እንደሆነ ያበክራል።

<u>ውይይት</u>፡- አማኞች መጠጣት የሌለባቸው ሌሎች ምክንያቶች አሉን? ግለጻቸው!

**ትምህርት 27፡- የሚቸገሩትን አማኞች መርዳት**

ብዙ አማኞች የእግዚአብሔር ነን ተብለው ይጠራሉ። ለምን? እንደዚህ የምንቸገረው ለምንድ ነው ይላሉ? አንዳንድ ጓደኞች እንደ ኢዮብ ወዳጆች ከኃጢአት የተነሳ ነው ብለን ለመፍረድ እንፈጥናለን። ምናልባት ጠንቋይ እንዲቸገሩ ረግሚቸው ይሆናል። ነገር ግን ለእውነተኛ አማኝ ሕይወት እቅድ አላት፤ እግዚአብሔርም ለእያንዳንዷ ነፍስ ዕቅድ አለው /ሮሜ 8፡28/።

1. **መከራ ለምን ይመጣል**

ሀ. አንዳንዴ የኃጢአት ውጤት ይሆናል /ዮሐንስ 5፡14፣ ማርያም በዘሌዋውያን 12፡10፣ ንጉሥ ኦዚያ በ2ኛ ዜና 16፡12/።

ለ. የእግዚአብሔር ሥራ እንዲገለጥ /ዮሐንስ 9፡2-3/።

ሐ. ለእግዚአብሔር ክብር /ዮሐንስ 11፡4፣ ፊልጵስዮስ 1፡29/።

መ. የጠላት ሥራ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሥር /ኢዮብ፣ ማርቆስ 5፡1-5፣ ሉቃስ 13፡16፣ ሐዋሪያት ሥራ 10፡38/፤ እግዚአብሔር አቅማችንን ያውቃል፡፡

ሠ. ቁጣ ወይም ቅጣት፡- የልጅ ሥልጠና /እብራውያን 12፡5-13/፡፡

## 2. ለመከራ ያለን ምላሽ

ሀ. በመቀበል ፈንታ እንገፋለን፣ እንቃወማለን፡- ይህ አመለካከት ወደ ጥንካሬ ያመራል፡፡

ለ. 892ኛ ቆሮንቶስ 12፡9/

ሐ. ተቀብለን ታግሰን ይሆናል፤ ነገር ግን አናጉረመርማለን፡፡

መ. ለእግዚአብሔር ፈቃድ በደስታ እየተገዛን ይሆናል፤ ይህ ደግሞ የድል ትልቁ መንገድ ነው፡፡

***የቤት ሥራ***፡- ከመንጋህ መካከል ከ3 እስከ 7 የሚሆኑ የሚቸገሩ ሰዎችን ዘርዝር፡፡ ልታገለግላቸው አቅድ፡፡ ሌሎችም ከመንጋዎች አብረው እንዲያገለግሉ አድርጋቸው፡፡

# ትምህርት 28፡- የታመሙትን ማገልገል

አማኞች ሊታመሙ ይችላሉ፤ ነገር ግን የቤተክርስቲያን አገልጋይ የእግዚአብሔርን ፍቅር በማሳየትና በመርዳት እግዚአብሔር እንደሚወዳቸው ማሳየት አለባቸው፡፡ ከበሽታ ጋር ተገናኝቶ ያለውን የአመለካከት ችግር እንመልከት፡-

## 1. እግዚአብሔር በፈውስ ታዓምር ሊሠራ ይችላል?

መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ተዓምራቶችን ሥራ ይነግረናል፡፡ ከተዓምራቶች ሁሉ በላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ሲሆን፣ ብዙዎቹ ተፈጽመዋል፡፡ የእኛ አምላክ ተዓምር አድራጊ አምላክ ነው፡፡ በዘፀአት 15፡26 "ጅሆቫ ራፋይ" የሚለው ቃል ከእግዚአብሔር ስሞች አንዱ ነው፡- "እኔ የምፈውሳችሁ አምላክ ነኝ" ማለት ነው /መዝሙረ ዳዊት 103፡3፣ ማቴዎስ 19፡26፣ ሉቃስ 18፡27/፤ ይህ አምላክ ዛሬም የሚያክም አምላክ ነው፡፡

## 2. የታመሙትን ስለመቀባት /ያዕቆብ 5፡14-20/

ሀ. የታመመ ሠው መሪዎች ይጠራል፡፡

ለ. መሪዎችም የእምነት ፀሎት ፀልየው ዘይት ይቀባሉ፡፡
ሐ. ያዕቆብ ሲናገር አንዱ በአንዱ የሰራውን በደል ይናዘዝ ይላል፡፡

### 3. የማይፈውሱ በሽታዎች አሉ

ሀ. በሐዋሪያት ሥራ 28 ጳውሎስ ሁለት ተዓምራቶችን አድርጓል፤ ነገር ግን ሶስት ጊዜ ለተዓምራቶች ቢጸልይም አልተመለሰለትም /2ኛ ቆሮንቶስ 12፡7-10/፡፡ ጳውሎስ የመታመሙ አላማ በትህትናው ለመጠበቅ ነው፡፡
ለ. ሁል ጊዜ የምንፈውስ ከሆነ መሞት የለም ማለት ነው፡፡ አማኞች የታመመውን ሰው በእግዚአብሔር ቃል ማበረታታት አለባቸው፡፡ የታመመን ሰው አለመርዳት ምን ያህል የነፍስንና የሥጋን ህመም እንደሚጨምርበት ማሰብ ተገቢ ነው፡፡ እስከ ሞት ድረስ ታሞ እንኳን እግዚአብሔር የበረከት ተስፋ ለቅዱሳን እንዳለው ማሰብ ተገቢ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ በሕመም እንኳን ፀጋህ ይበቃሃል ብሎ ተስፋ ሰጥቷል፡፡

***ውይይት፡-*** *የታመሙትን ለማፅናናት የሚጠቅሙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶች የትኞች ናቸው?*

## ትምህርት 29፡- በሞት ጊዜ ማገልገል

ሕይወት የማይጨበጥ እና አላፊ ነው፤ ዛሬ ታይቶ ነገ የሚጠፋ! በምድር ላይ ከተወለዱ ሰዎች ሁሉ ኤልያስና ሄኖክ ብቻ ናቸው ሞትን ያላዩት፡፡ ሞትን ያላዩት አሁን ካለው ትውልድ ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ በመነጠቅ ከሚያገኙት ውጪ ሁሉም ይሞታሉ /እብራውያን 9፡27/፡፡
አማኝ የሆኑ አገልጋዮች የሕዝቡ ጌታ በሚመጣበት ጊዜ ትልቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ቤተሰብና ጓደኞች ሰው ሲለያቸው የሚሰማቸው በኃዘን ያሉትን በመመገብ በመጠየቅ ማጽናናትና ከጎናቸው መሆን አለባቸው፡፡ ከሚያዝኑ ጋር ማዘን የአማኞች የፍቅር መገለጫ ነው፡፡
ከማያምን ሰው ይልቅ ያመነን ሰው ማፅናናት ይቀላል፤ ምክንያቱም ነፍሱ በጌታው ዘንድ የሠላምንና የደስታን ቦታ ስላገኘች በእውነት ይህ አለም ከሚሰጠው ሁሉ ይልቅ በጌታ ጋር መሆን ይሻላል፡፡ የለቅሶ ስነ-ስርአት በሐዘን ፈንታ ስለተለየው ሰው በጌታ ስለሆነ የደስታ ይሆናል፡፡

በሞት ጊዜ አማኝ የሆነ መሪ የፀና አቋሙን ላላመኑት ቤተሰቦች በሚገባ የማሳየት ኃላፊነት አለበት። በአማኞች ቀብር ጊዜ የሐብት፣ የመጠጥ፣ የጣኦት አምልኮ በአማኞች ሕይወት ቦታ እንደሌላቸው መገለፅ አለበት፤ ነገር ግን ያላመኑ ቤተሰቦችና ጓደኞች ስለሞት ያላቸው አመለካከትን አስከትለው ተስፋ ቢስነትንና ከንቱነት ያወራሉ። ለእንደዚህ አይነት አመለካከት ተቃራኒ ሆኖ መቆምና አውነትን ማሳየት ተገቢ ነው። ስለዚህ አማኞች በደስታና በመዝሙር የሞተውን አካል ለምድር ማስረከብ አለባቸው። እዚህ ላይ መሰበክ ያለበት ይህ ምድር ጊዜያዊ እንደሆነና የዘላለም ቦታ ከሞት በኋላ እንዳለ ማሳየት አለበት። ጠቢብ ሰው ተከታዮች ከመሞታቸው በፊት ለሞት የተዘጋጁ እንደሆኑ ይነግራቸዋል፤ ነገር ግን እነርሱ አልተቀበሉትም። ነገ ልንሞት ስለምንችል ዛሬን መዘጋጀት አለብን።

***ውይይት***፡- የቤተክርስቲያን አባል የሆነ ሰው ቢሞት ሌላ ማድረግ ያለብህ ነገር ምንድነው?

## ትምህርት 30፡- እጮኛዎችን ማማከር

መተጫጨት ማለት ሁለቱም ወንድና ሴት ለመጋባት መወሰናቸውን ለማህበሩ የሚያሳዩበት ነው፤ ምናልባትም በአመት ጊዜ ውስጥ ሊሆን ይችላል። ሁለቱም ጥንዶች በመተጫጨት ወቅት በግልጽ እንዳቸው ለአንዳቸው እንደሚያስፈልጉ በሚገባ ማወቅ ተገቢ ነው። ነገር ግን ስላልተጋቡ ምንም ነገር ለማድረግ ነፃነት ሊኖራቸው አይገባም። በጋብቻ ወቅት በድንግልናቸው ቢጋቡ የወደፊት ደስታቸው ታላቅ ይሆናል። በጋብቻ የሚገኝ ደስታ ለጋብቻ ጊዜ መጠበቅ ካልቻለ፣ መተማመንም ሆነ የጋራ ጥቅም ሁሉ ሊበላሽ ይችላል /2ኛ ሳሙኤል 13፡15/።

ጊዜው የንቃት ስለሆነ፣ የቤተክርስቲያን መሪዎች በዚህ ጉዳይ ጥንዶችን በማስተማር፣ አቅጣጫ በማሳየት፣ ክርስቲያናዊ ቤተሰብ እንዲመሠርቱ በማድረግ ሊያስተምሯቸው ይገባል /ኤፌሶን 5፣ቲቶ 2/። ሁለቱም በችግሮቻቸውና ግራ ባጋባቸው ላይ አብረው እንዲፀልዩ ማድረግ ተገቢ ነው። አንዱ ለአንዱ ፍቅራቸውን በቃልም በተግባርም በዘመናቸው ሁሉ ማሳየት አለባቸው።

ጋብቻ የመጀመሪያው የሰው ተቋም ነው። ከደህንነት ቀጥሎ የትዳር አጋርን መምረጥ ትልቁ ውሳኔ ነው። በዚህ ወሳኝ ሰዓት መንፈሳዊ መሪ ጠንካራ ድጋፍና ምክር ለጥንዶች መስጠት አለበት።

**የጥሩ ጋብቻ መመሪያዎች**

1. አማኞች ማግባበት ያለባቸው አማኞችን ብቻ ነው /2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14-17/።
2. ብዙ መፀለይ የእግዚአብሔርንም ፈቃድ መፈለግ
3. ሌላኛው ሰው ደካማና ጠንካራ ነገሮችን እስኪሚያውቅ ድረስ ታገሥ፤ ቸኩሎ መጋባት ችግር ያመጣል።
4. ትክክለኛውን ፍቃድ ጠብቅ ጊዜያዊ የሆነ ፍቅር በቂ አይሆንም፤ ምክንያቱም ጋብቻ ለዘላለምና ለቤተሰብ ደስታ መሆን አለበት።
5. ለማግባት ዝግጁ እስከምንሆን ጠብቅ ጋብቻ ለአዋቂ ሰዎች እንጂ፣ ለልጆች አይደለምና፤ ምክንያቱም ታላቅ ኃላፊነት የያዘ በመሆኑ ነው።
6. የሥነ-ምግባር ችግሮች እስኪስተካከሉ ድረስ አታግባ፤ አስተካከላለሁ ብሎ ማግባት ጥሩ አይደለም።
7. የሴቷ ቤተሰቦች እስኪፈቅዱ ጠብቅ ጠቃሚ ነውና።
8. የገንዘብ አቅም እስክታዳብር ድረስ ጠብቅ፤ ይህ ማለት ሀብት ማከማቸት ማለት አይደለም ነገር ግን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።
9. በህዝብ ፊት የሚደረግ ክርስቲያናዊ ሥርግ ለማድረግ ጥረት አድርግ።
10. ድብቅ ጋብቻን ለማድረግ መቼም አታስብ፤ ጋብቻ የተቀደሰ ስለሆነ በዚህ ተግባር ላይ መውደቅ የለበትም።

***የቤት ሥራ***፡- የወጣቶች የሚሆን ጤናማ ጋብቻ ለመመስረት የሚጠቀሙ ትምህርቶችን አዘጋጅ።

## ትምህርት 31፡- ልጅ ያልወለዱ ጥንዶችን እንዴት እንመክራለን

ሁለት ጥንዶች ከተጋቡ በኋላ ልጅ ይጠብቃሉ፤ ካልወለዱ አመታት ካለፋባቸው ግን ማጉረምረምና መቆጣት ያድግና ክርስትናን የሚፈታትን ይሆናል። ጓደኞቻቸው ልጅ አስከትለውና፣ ሌሎች አዝለው ወደ ቤተክርስቲያን ሲመጡ በሚያዩ ጊዜ እግዚአብሔር የእኛን ፀሎት ለምን አይመልስም ብለው ይጠይቃሉ።

አንዳንዶች በማማረር ቤተክርስቲያንን ይለቃሉ፣ እንዳንዶች ወደ ጠንቋይ ቤት በመሄድ ያላቸውን ንብረት ያባክናሉ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውንም ሕብረት ይጎዳሉ። መካን የሆኑ ጥንዶች የአንተን ፀሎት ምክርና ድጋፍ ይፈልጋሉ። ብዙ ጊዜ እንደ ራሔል ልጅ ስጠኝ ካልሆነ እሞታለሁ ይላሉ /ዘፍጥረት 30፡1/።

ሐና ለአመታት ያነባችው ዕንባ ባሏ ያደረገላት ድጋፍ ልጅ ለሌላቸው ጥንዶች ጠቃሚ ምክር ሊሆን ይችላል። ሐና ልጆች አልነበራትም፣ የባሏ እልቃና የጎላ ታማኝነት በ1ኛ ሳሙኤል 1፡5 ተገልጿል፡- “ሐናን ይወዳታል፣ ጌታም ማህፀኗን ዘግቶት ነበር።” መካን የሆነችን ሴት ባል ወደ ቤተሰቦቿ ሊያባርሯት አይገባም፣ እሱም እንደ ሕልቃና መሆኑ ተገቢ ነው። በአንተ ቤተክርስቲያን ላሉ ለእኛ ሐናዎች የሚከተለውን እውነት ንገራቸው፡-

1. ሐና እንደ ፀለየች እነርሱም በፀሎት መቀጠል አለባቸው። ማህፀኗን የዘጋው እግዚአብሔር ነበር፣ ጊዜውም ሲደርስ የከፈተው እርሱ ነው። አብረሃምና ሣራ ልጅ ለመውለድ በማይቻሉና ባረጁ ጊዜ እግዚአብሔር ልጅን ሰጣቸው /ዘፍጥረት 21፡2፣ መዝሙር 113፡9/ ጥሩ ጥቅስ ነው።
2. በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፣ አትጨነቅ፣ እንደ ራሔል ባልሽን አትጨቅጭቂው፣ ስለተሰጠሽ በረከት ደስ ይበልሽ፤ ፊትሽም ደስተኛ ይሁን። ጨለምተኝነት የባልሽን ፍቅር ሊገድለው ይችላል፣ ከዚያም ግራ የተጋባች ያደርግሻል።
3. እግዚአብሔር ልጆችን የማይሰጥ ከሆነ የእናትነት ልብ አሁንም ሊኖርሽ ስለሚችል ፍቅርን ለሌሎች ልጆች መስጠት ትችያለሽ። ምክንያቱም ብዙ ወላጅ ያጡና የተገፋ ልጆች አሉና! የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና ህብረት መካፈል ምናልባት ልጆች ለማግኘት እድል ሊፈጥርልሽ ይችላል። በእስራኤል ዲቦራ እናት ለመሆን በቅታለች /መሳፍንት 5፡7/።

***ውይይት***፡- በቤተክርስቲያን ውስጥ ልጅ የሌላቸውን ስለማገልገል ተወያይ። እንዴት ልታበረታታቸው ትችላለህ?

## ትምህርት 32፡- መበለቶችን ማልገል

በቤተክርስቲያንህ ምናልባት ያረጁ መበለቶች ጌታን የሚወዱና በአገልግሎታቸው ታማኞች የሆኑ ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ምናልባት የማይፈለጉና ብቸኞች የሆኑ ይመስላቸዋል፡፡ እነርሱም በፀጋቸው ጌታን እንዲያገለግሉ ያስፈልጋል /1ኛ ጴጥሮስ 4፡10/፡፡ ለእነርሱ መበለቶች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡-

1. ኑሐሚን የልጅ ልጅዋን በመንከባከብ ጎበዝ ነበረች /ሩት 4፡16/፡፡ እምነቷንም ለቀጣይ ትውልድ ማሻገር የቻለች ሴት ነበረች፡፡ ሴት አያቶች ለልጅ ልጆቻቸውና ወላጆቻቸውን ላጡ ብዙ እርዳታ ማድረግ ይችላሉ፡፡
2. በሰራኝታ የነበረች መበለት የእግኢብሔርን ሰው ተቀብላለች /1ኛ ነገስት 17/፡፡ ትልልቅ ሴቶች ከምንም በላይ የእንግዳ ተቀባይነትን አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡
3. ሐና መበለት ነበረች፣ ዕድሜዋ ሰማንያ አራት ሆኖም እግዚአብሔርን ታገለግላለች ትፀለያለች፤ ትፆማለች፣ ስለ እግዚአብሔር ለሌሎች ትናገር ነበር /ሉቃስ 2፡36-38/፡፡
4. ያላትን እያነሳትም ቢሆን ሁሉን ለጌታ ትሰጥ ነበር /ሉቃስ 21፡4/፡፡
5. ዶርቃ የምትባል ደግ ብዙዎችን አፅናንታለች፤ ለታረዙት አልብሳለች፣ ለመበለቶችም ድጋፍ አድርጋለች /ሐዋሪያት ሥራ 9፡39/፤ በችግር ውስጥ ያሉትንም ደግፋለች፡፡
6. ጢሞቴዎስን ለአገልግሎት በማዘጋጀት ረገድ አያቱ ትልቅ ሚና ተጫውታለች /2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡15/፡፡ ይህ ዕድሜ ፍሬያማና ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ ዝም ብሎ ሞትን ከመጠበቅ ይሻላል፡፡

***ውይይት***፡- ስለ መበለቶች አገልግሎት የተጠቀሱት ጥቅሶችን ከልሳቸው፣ ሌሎችን መጨመር ይቻላል?

## ትምህርት 33፡- አማኞች ካላመኑ የትዳር አጋሮች ጋር

አማኝ ሆኖ ያገባ ሰው ብቻውን ካለ መንፈሳዊ ምክርና ማበረታታት ያስፈልገዋል፡፡ እነርሱን ስትመክር የሚከተለውን ንገራቸው፡-

1. በአንተና በትዳር አጋርህ መካከል ክፍተት እንዲኖር አትፍቀድ፡፡
2. የትዳር አጋርህ የበታችነት ስሜት እንዲሰማው /ማት/ አታድርግ /ጊ/፡፡

3. በትዳር አጋርህ ላይ ብዙ ፍቅርን አሳይ፤ የእግዘአብሔርን ፍቅር በአንተ/በአንቺ/ ላይ እንደሆነ እንዲሁ ፍቅርን አብዛ/አብዢ/።

4. ችግርህን ለውጪ ሰዎች አትናገር።

5. አምላካዊ መንፈስ በቤትህ ይብዛ።

6. ደስተኛ ሁን፣ መንፈስ ቅዱስም በአንተ /በአንቺ/ ላይ ይሁን።

***ውይይት***፦ የዳነ ሰው ያልዳነውን ሊያገባ /ልታገባ/ ስትዘጋጅ የቤተክርስቲያን መሪዎች ምን ማድረግ አለባቸው? ጥንዶችን ወደ ቤተክርስቲያን ወደ ክርስቶስ የሚያቀርብ ምን ቢያደረግ ጥሩ ነው ትላለህ?

## ትምህርት 34፦ የእግዚአብሔርን ቀን ስለመጠበቅ

የእግዚአብሔርን ቀን "እሁድ" በአዲስ ኪዳን የበሉይ ኪዳን መሠረት አለው፦

1. በሰንበትና በጌታ ቀን የሚለውን አመዛዝን

ሀ. ሰንበት ሰባተኛው ቀን ሲሆን፣ የጌታን ቀን ከሳምንቱ የመጀመሪያው ቀን ነው።

ለ. ሰንበት የእግዚአብሔርና ፍጥረት ማረፍን ያመላክታል፤ የጌታ ቀን የክርስቶስን ትንሣኤ ያስታውሳል።

ሐ. ሰንበት ለአይሁድ፣ የጌታ ቀን ደግሞ ለቤተክርቲያን ነው።

2. የሐዋሪያት ቤተክርስቲያን የሚያከብሩት የሳምንቱን መጀመሪያ ቀን ነው።

ሀ. ማቴዎስ 28፡1 ኢየሱስ የአይሁድን ሰንበት ለማክበር ሙሉ ቀን በመቃብር ዋለ፤ የተነሣው በፋሲካ በመጀመሪያው ቀን ነው።

ለ. ሐዋሪያት ሥራ 20፡7 መደበኛ የቤተክርስቲያን አምልኮ በዚህ ተጠቅሷል።

ሐ 1ኛ ቆሮንቶስ 16፡2 ለእሁድ አምልኮ አንድነት መመሪያ ተሰጥቷል።

መ. ራዕይ 1፡10፣ ዮሐንስ የጌታ ቀን በማለት ተናግሯል።

3. የጌታ ቀን ለማክበር ትክክለኛ መንገድ

ሀ. በጌታ መደሰት የአምልኮ፣ የፀሎትና የምስጋና ቀን አድርገህ ያዘው።

ለ. ከግል ደስታዎች መለየትና ጌታን የምታስደስትበት ቀን መሆኑን ተረዳ። የታመሙትን ጠይቅ ሌሎችንም ጌታንም የሚያስደስት ተግባራት ፈፅም።

ሐ. እግዚአብሔርን የሚያከብር ቀን ለማድረግ ትጋ። ስድስት ቀን ሥርተን የሚያስልገንን ማግኘት ብንችልም፣ ሰባተኛው ቀን የጌታ መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

***ውይይት***፡- በእሁድ የምንሠራቸው የጌታ ቀን መሆኑን የሚያሳዩ ሥራዎችን ምንድናቸው፡፡

## ትምህርት 35፡- የአባቶች ቀን

በዘፍጥረት 18፡19 እና ኤፌሶን 5፡23 እግዚአብሔር ባሎችን የቤተሰብ ራስ እንደሆኑ አድርጎ አስቀምጧል፡፡ ክርስቲያን ባሎች እንደ ቤተሰብ ሆነው ሥራቸው ለመቀጠል ድጋፍ ይፈልጋሉ፡፡ በቤተክርስቲያናችን ያሉ አባትን የምናከብርበት ቀን ለምን አይኖረንም? አንድ ቀን አስቀድሞ ማስታወቂያ በመናገር ልጆች ከወላጆቻቸው ጋር እንዲቀመጡ አሳስብ፡፡ ከአባት ጋር ሆነውም ከልጆቻቸው ጋር እንዲቀመጡ አሳስብ፡፡ ከአባት ጋር ሆነው መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና መፀለይ፣ በጉባኤው ውስጥ ያሉትን ታላላቅ አባቶች መካከለኛ ዕድሜ ያላቸውን ልጆችን እውቅና ስጥ፡፡ የቀኑ ስብከት የክርስቲያን አባቶች ክብር ቀን የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡ ሚስቱን መውደድ አለበት /ኤፌሶን 5፡25/፡፡ መወደዱም በረሐብ፣ በጥጋብ፣ በማግኘት፣ በማጣት፣ በበሽታና በፈውስ ጊዜ ሁሉ ለሚስቱ ታማኝ፣ በሐዘኗም ጊዜ አፅናኝ መሆን አለበት /1ኛ ሳሙኤል 1፡8፡፡
አባት በአጋርነት፤ በአስተማሪና በግሳፄ ልጆችን ለጌታ ለማሳደግ መትጋት ምሳሌ 22፡6፡፡ እንዲሁም የቤተሰብ የየቀኑን የምልኮ መሠዊያ ማዘጋጀት አለበት፡፡ የምግብ ዝግጅት ሃላፊነት አለበት፡፡ ከአንድነት ወላጆችን ወደ ጌታ ለማቅረብ ትጉ መሆን አለባቸው /ማቴ 19፡13/ ቤተሰቡንና ሚስቱን ቢወድም ክርስቶስን ይልቅ አብዝቶ መውደድ አለበት፡፡ ክርስቲያናዊ ባል ሁልጊዜ በሕይወቱ የሚያስቀድመው ክርስቶስን ብቻ ነው /ሉቃስ 14፡26/፡፡

***የቤት ሥራ***፡- ለአባቶች ቀን የሚሆን የአምልኮ ጊዜ የሚሆን ስብከት አዘጋጅ፡፡

## ትምህርት 36፡- የእናቶች ቀን

ጥሩ ሚስቶችና እናቶች ለቤተክርስቲያንና ለጌታ ትልቅ ስጦታ ናቸው /ምሳሌ 31፡10/፡፡ ሚስቶች ምስጋና እና ማነሣሣትን ይፈልጋሉ፤ ቤተክርስቲያን አገልግሎታቸውንም ምስክርነታቸውንም ልታከብር ይገባል፡፡ ለእናቶች የክብር ቀን ልጆች ሊዘምሩና ለጌታ የመስጠት ቀን ሊያዘጋጁ

ይችላል። ሁሉም ልጅ ለእናቱ አበባ ይዞ ሊመጣ ይችላል፤ የዕለቱም ስብከት መፅሐፍ ቅዱሳዊ ሚስት በሚለው ሐሳብ ላይ ሊሆን ይችላል።

***የቤት ሥራ፦*** በቤተክርስቲያንህ የእናቶች ቀን በማለት ኘሮግራም እቅድ በቀኑ የሚሣተፉትን ስም ዝርዝር ፃፍ፣ ኃላፊነታቸውን አሳይ።

## ትምህርት 37፡- የቤተሰብን መሠዊያ መሥራት

የውጤታማ ክርስቲያን ቤት መሠዊያ ራስ የሆነው ክርስቶስ በሚገኝበት፣ በሚመለክበት በሚመራበት መሆን አለበት።

የቤተሰብ፣ የፀሎትና የህብረት ጊዜ ብታደርግና ብታስተምር እንዳንዶች ሊከተሉህ ይችላሉ፤ ነገር ግን አንዳንዶች ምን እየተደረገ እንደሆነ አያስቡ ይሆናል። ታዲያ ለምን በአምልኮ ጊዜ አናስተዋውቀውም? አንድ ቤተሰብ ምረጥ፣ በቤተሰብ አምልኮ ጊዜ ተገኝተው እንዲያካፍሉ አግኝተህ አዘጋጃቸው፤ ምናልባት በቤተሰብ መዝሙር ወይም በጥቅስ ሊጀምሩ ይችላሉ። ሁሉም ልጆች ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ እንዲያነቡ አዘጋጅ፣ ከዚያም በፀሎት እንዲዘጋ አድርግ። ካቀረቡ በኋላ የቤተሰብ አምልኮ ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ የሚያሳይ መልእክት አቅርብ።

ቤተሰብ የሰጠው ተሞክሮ ሌሎችን የጠናክራል፤ ሌሎችን በቤታቸው ከዚህ የተነሣ ይጀምሩ ይሆናል። ሁሉም ቤተሰብ እያንዳንዱ አባል ማወቅ ያለበት ምን እንደሆነ ማየት አለበት።

*የቤት ሥራ*፡- የቤተሰብ ተማሪዎች የቤተሰብ አምልኮ በተግባር ያሳዩ።

## ትምህርት 38፡- ሁሉንም ቤተሰብ መድረስ

አንድ ትልቅ ሐላፊነት ማለት ሁሉንም የቤተሰብ አባል ወደ ሰማይ መምራት ነው። ይህም ወላጆች በመታዘዝ የእግዚአብሔርን እውነት ለልጆች እንዲያሻግሩ ማድረግ ነው። የሚከተሉትን ሐሳቦች ተመልከት፡-

1. ወላጆች በቤተሰብ ከልጆች ጋር በጋራ ሆነው የእግዚአብሔርን ቃል እንዲማሩ በአደባባይ ስበክ፣ በግልህም ምከር /ዘዳግም 6፡6-9 እና ምሳሌ 6፡20-23 ፣መዝሙር 119፡11/።

2. ወላጆች ለልጆቻቸው ጓደኞች ቤታቸውን ክፍት ማድረግና መፍቀድ አለባቸው። ስለ ልጆቻቸው ሲሉ ወላጆች የተነሣሡ፣ ታማኞች፣ ሙሉ

ልባቸውን የሰጡ፣ ከቤተክርስቲያን አላማ ጋር የሚቆሙ ሊሆን ይገባል። ለጠንካራ ቤተሰብ የእግዚአብሔር ቃል ወሳኝ ነው።

3. ቤተሰብን በቤተክርስቲያን ማበረታታት፡- ወላጆች አማኞች ከዚህ እንዲፀልዩና ልጆቻቸውን እንዲደግፉ ማበረታት ተገቢ ነው። ለትልቅ ሰው፣ ለወጣቶችና ለልጆች የሚያስረዳ ተግባር ምረጥ ወይም ይኑርህ። የእግዚአስሔር ሰዎች የትውልድን ክፍተት ማጥበብ አለባቸው።

4. የደረሱ ልጆች ያሏቸው ወላጆች ስለ ጥሎሽ አስጠንቅቃቸው፤ ብዙ ወጣቶች ለብዙ ዓመት የሚሆናቸውን ገንዘብ አንሰጥም በማለት ብዙ አደጋ ውስጥ ገብተዋል፣ አንዳንዶቹም ለመስጠት ተጨንቀዋል። ልጆች ከእግዚአብሔር ድንቅ ስጦታ ናቸው። በአንተ ጉባኤ ደግሞ ለወላጆች ልጆችን ወደ ክርስቶስ መንገድ መምራት ታላቅ ደስታ ይሆናል። ልጆቻቸውን ወደ ዘላለም ህይወት ይመራቸዋል።

***ውይይት***፡- ከላይ የተሰጡትን አራቱንም ነጥቦች አሰላስል፤ በቤተክርስቲያን ያሉ አባላት ሊተገብሩ የሚችል ይመስልሃል? ሌላ ተጨማሪ ሐሳብ ካለ ጨምር።

## ትምህርት 39፡- ተራ ሰውን ለአገልግሎት ማስተባበር

ተራ ሰውን ለአገልግሎት ማስተባበር በመሪነትህ ረገድ በቤተክርስቲያን ትልቅ ሚና እንዳለው አትዘንጋ። የቤተክርስቲያን ሥራ ሁሉ በአንተ ትከሻ ብቻ ሊከናወን አይችልም፤ ይህም ከባድ ስህተት ይሆናል ለምን?

በመጀመሪያ 1ኛ ጴጥሮስ 4፡10 አንብብ፣ ትዕዛዙ በጣም ግልጽ ነው። ሌሎችን ለማገልገል ያላቸውን ስጦታ መጠቀም እንዳለባቸው መረዳት ያስፈልጋል። አባቶች መንፈሳዊ ስጦታቸውን በጌታ ለማድረግግ መለማመድ አለባቸው፡- አሰልጥናቸው፤ አበረታታቸው። መፍሰሻ የሌለው ውኃ በአንድ ቦታ ታጉሮ ይቀመጣል፤ የሕይወት ውኃ ምንጭ በተራ አማኞች በኩል መፍሰስ አለበት።

የወንጌል ቡድን አቋቁም፤ አንዱ የመዝሙር መሪ፣ ሌሎች በግል የሚዘምር፣ ሌላው ጊታር የሚጫወት፣ አንዱ የሕይወት ታሪክ የሚያቀርብ፣ ለሁሉም በአምልኮ ጊዜ ቦታ ስጣቸው። አንዱ የፀሎት ቡድን እንዲመራ አድርግ፤ ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ይምራ! ሌሎች ደግሞ የሰንበት

ትምህርት ያስተምሩ፤ አሁንም ሌሎች የወጣቶችን ክበብ መቀላቀልና መምራት ይለማመዱ። በዚህ አይነት ሁኔታ የጋራ አገልግሎትን አናሳድግ። በዚህ ሁሉ ሌሎችን /አንድ ሰውን/ ወደ ክርስቶስ ማሳየት እንዲችሉ አድርግ።

***ውይይት፡-*** ተራ ሰዎች በአገልግሎት በኩል ለክርስቶስ ያላቸውን ፍቅር እንዲያሳዩ ማድረግ ትችላለህ።

## ትምህርት 40፡- የሴቶችን ስጦታ መጠቀም

በቤተክርስቲያንህ ያሉ ሴቶች በጌታ ሥራ ተመልካች ሆነው እንዲቀሩ አትፍቀድ። ምክንያቱም ለምዕመኑ በረከት፣ ለጌታ ክብር ለራሳቸው ጥንካሬ የሚሆን ስጦታ በውስጣቸው አለ።
በመንጋህ ውስጥ ያሉትን ሴቶች ተመልከት፤ ከተለያዩ አገልግሎቶች በአንዱ እንዲያገለግሉ አበረታታቸው፡-

**1. በሴቶች መካከል**

ሀ. እንደ ዲያቆናት ያዘኑትን ወይም የታመሙትን መጠየቅ
ለ. የፀሎት ቡድንን መምራት ወይም ማስተናገድ
ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትን መምራት
መ አዲስ አማኞች ማስተማርና ደቀ መዝሙር ማድረግ

**2. በልጆች መካከል**

ሀ. የሰንበት ትምህርት ማስተማር
ለ. የጎረቤት ስብሰባዎችን መምራት
ሐ. የቤት ውስጥ ፕሮግራሞችን ማስተናበር

**3. በቤት ውስጥ**

ሀ. ልጆቻቸው ጌታን እንዲከተሉ ማስተማር
ለ. አማኞችንና ያላመኑትን ሁሉንም የመጠየቅ ባህርይ መከተል
ሐ. ባህልን ማበረታታትና መርዳት፣ ያላመነ ከሆነ ወደ ክርስቶስ እንዲደርስ በሮችን ማመቻቸት።

***ውይይት፡-*** በመንጎችህ መካከል ላሉት ሴቶች ሌላ አገልግሎት ያሰብከው /የምትጨምረው/ አለ?

# ቅዱስ አኗኗር
# ለተቀደሰ አገልግሎት መዘጋጀት
## መግቢያ

ይህ ትምህርት ከሁሉ ይልቅ በጣም ጠቃሚና ወሳኝ ትምህርት ነው፡፡" በልብ ውስጥ የምለውን አፍ ይናገራል "/ማቴ 12፡34/፡፡ የተቀደሰ ሕይወት ብቻ መንፈሳዊ ፍሬን ያፈራል፡፡ ስለዚህ አንድ አማኝ ቅድስናውን የሚያስተጓጉሉ፣ ከልቡ የሚያጠፉ፣ ምስክርነቱን የሚያበላሹ ነገሮችን በአጽንኦት ማስወገድ አለበት፡፡

ብዙ ሐሳቦች የተወሰዱት "100 Bible Lessons, by Douglas Alban, and from Preacher and People, by Rev. R. Stanley, and The Ideal Wowman, by Dr. Lilian Stanley መጻሕፍት ነው፡፡

**ይዘት**

1. እግዚአብሔርን መፍራት
2. መንፈስ ቅዱስን የተሞላ ሕይወት
3. ዲያብሎስን መቃወም
4. የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ
5. የፀጥታ ጉዞ
6. መለየት
7. የግል ሕይወት
8. የውስጥ ስሜት
9. የመሪ መስፈርቶች
10. ዝሙት
11. የቤተሰብ መሪ
12. እውነት ብቻ
13. ስለ ገንዘብ
14. ሥርዓት ያለው ጥናት
15. የአካል ብቃት ጠብቅ
16. ስንፍና
17. ምስጋና
18. ፈተና መቼ ይመጣል
19. ተከታዮች
20. ድል ማድረግ የተረጋጠ ነው

# ክፍል አምስት
# የተቀደሰ አኗኗር

## ትምህርት 1፡- እግዚአብሔርን መፍራት

ፍርሃት ትክክለኛና ትክክለኛ ያልሆነ ሁለት መልክ አለው፡፡ “አትፍራ” የሚል መልእክት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልእክት ነው፡፡ 50 /ሃምሣ/ ጊዜ ተጠቅሷል፣ በተለያዩ መልእክቶች 366 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ የጌታን ቃላት አስተውሉ “እኔ ነኝ አትፍሩ” አላቸው፡፡ ሆኖም ግን እግዚአብሔርን መፍራት ልንከተለው የሚገባ ነገር ነው፡፡ ይህን ጥቅስ ተመልከት /ኢዮብ 28፡28፣ መዝሙር 19፡9 2 ሳሙኤል 23፡3፣ ዘዳግም 6፡13/፡-

1. **መፍራት የሌለብን ነገሮች የሚከተሉት ናቸው**

ሀ ጣኦታትንና ሌሎች አማልክትን /2ኛ ነገስት17፡38/

ለ. ሰው /1ኛ ሳሙኤል 15፡24/ የሳኦልን ስህተት ተመልከት፤ በምሳሌ 29፡25 ላይ አተኩር

ሐ. የወደፊት ቅጣትን /ዕብራውያን 10፡27/

መ. ምድራዊ ክንውኖችን /ክስተቶች የጌታን መምጣት ስለሚሳይ /ሉቃስ 21፡25-28/

ሠ. ፍርሃትን መፍራት የለብንም፣ አማኞች ፍርሃታቸውን በጌታ ላይ ስለሚጥሉ /1ኛ ጴጥሮስ 5፡7/

2. **እግዚአብሔርን መፍራት ምንድ ነው?**

ሀ. ክፉውን መጥላት /ምሳሌ 8፡13/

ለ. ጥበብ ነው /መዝሙር 111፡10/

ሐ. ጥጋብ ነው /ምሳሌ 15፡16 እና ኢሳይያስ 33፡6/

መ. የሕይወት ምንጭ ነው /መዝሙር 14፡27/

ሠ. ንፁህ ስለ ሆነ /መዝሙር 19፡9/

ረ. ለዘላለም የፀና ነው /መዝ 19፡9/

ሰ. አምላካዊ ስለሆነ /ዕብራውያን 12፡28/

**3. እግዚአብሔር የመፍራት ውጤቶች ምንድናቸው? መዝ 147፡11።**

*ሀ እግዚአብሔርን ያስደስታል /መዝሙር* 147፡11/

*ለ በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት አለው /ሐዋሪያት ሥራ* 10፡35/

*ሐ እግዚአብሔር ልጆችን እንዲያፅናና ያደርጋል /መዝሙር* 103፡13/

*መ በረከት ያመጣል /መዝሙር* 112፡1/

*ሠ ከክፉ መለየትን ያመጣል /መዝሙር* 16፡6/

*ረ የፀሎትን ሕብረት ያመጣል /ሚልኪያስ* 3፡16/

*ሰ ለፀሎት መልስ ያመጣል /መዝሙር* 145፡19/

*ሸ ረዥም ዕድሜ ይሰጣል /ምሳሌ* 10፡27/

***ውይይት፦*** ፍርሃትን የተሞላ ልብ ድካሙ ምን እንደ ሆነና እንዴት እንደምናሸንፍ ተነጋገሩ። ከዚያም እግዚአብሔርን ስለመፍራት ጥበብ ተወያዩ።

## ትምህርት 2፡- መንፈስ ቅዱስን የተሞላ ሕይወት/ ኤፌሶን 5፡18/

*ሁሉም አማኝ መንፈስ ቅዱስ አለው፣ የተሞላም ነው /ሮሜ* 8፡16/፤ *ነገር ግን በአንድ ቦታ የተወሰነ አይደለም፤ እሱ ኗሪ ነው። ልንከተለው በፈለግን ቁጥር እርሱ በኛ ሕይወት ይበዛል /ሉቃስ* 11፡13/።

*መሞላት ሰው ባመነ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ መቀበል ማለት ነው፤ ከዚያ ሙሉ በሙሉ በእርሱ ቁጥጥር ሥር እንዲንሆን ማድረግና ሁለንተናችንን ለርሱ ማስገዛት ነው።*

*የመጀመሪያው የግሪክ ቃል ትእዛዛዊ ሲሆን፣* ***"በቀጣይነት መሞላትን"*** *ያመለክታል፤ መሞላት ቋሚና ቀጣይ ነው። ሐዋሪያው ጳውሎስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቷል /ሐዋሪያት ሥራ* 2፡4 *ደግሞ* 4፡8፣4፡34/። *ሁሉም ቀን በየራሱ መሞላትን ይፈልጋል።*

**1. በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ሁኔታዎች**

*ሀ. የኃጢአት ይቅርታ /ሐዋሪያት ሥራ* 2፡38/

*ለ. ልጅነት /ገላትያ* 4፡6/

*ሐ ለመሞላት ፍላጐት መጨመር /*1*ኛ ዮሐንስ* 7፡37-39/

*መ. እምነት /ዮሐንስ* 7፡39/

ሠ. መታዘዝ /ሐዋሪያት ሥራ 5፡32/

ረ. መጠበቅን /ሉቃስ 24፡49/ እና ሐዋሪያት ሥራ 1፡4፣ አለመቸኮል!

ሰ. ፀሎት /ሉቃስ 11፡13/

ሸ. እውነትን ማድረግ /ዮሐንስ 1፡12/

**2. በመንፈስ ቅዱስ የመሞላት ውጤቶች**

ሀ. ለምስክርነት አቅም ማግኘት /ሐዋሪያት ሥራ 1፡8/

ለ. የክርስትናን ድል ሕይወት ለመኖር /ሐዋሪያት ሥራ 20፡22-24/

ሐ. ክብር ለእግዚአብሔር ይሆናል /ዮሐንስ 17፡6-14/

***ማጠቃለያ*-** እኛ በራሳችን የምንጠበቅ ሳንሆን አስተላለፊዎች ነን፤ ማፍሰስ አለብን፤ በረከት ይፈሳል፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ የሠራውን አስታውስ፡-

1. ምንጭ ይሆናል /ዮሐንስ 4፡14/፡፡
2. የሕይወት ውሃ ነው /ዮሐንስ 7፡37-39/፡፡
3. በዛፍ ውስጥ ውሃ የሚያስተላልፍ በረከት /ሮሜ 8፡11/፡፡
4. ውሃን ያፈሳል /ኤፌሶን 5፡18/፡፡

***ውይይት*፡-** ምናልባት አንዳንድ የክፍል ተማሪዎች በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን አልተለማመዱ ይሆናል፡፡ የንስሐና የፀሎት ጊዜ ለበረከቱ መንገድ ሊሆን ይችላል፡፡

**ትምህርት 3፡- ዲያብሎስን መቋቋም /1ኛ ጴጥሮስ 5፡8-9/**

ሰይጣን እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆችን እንደሚያጠቃ መረሣት የለብንም፡፡ ይህ ትምህርት ይህን ጥቃት እንዴት እንደምንከላከል ይረዳናል፡፡

**1. ሰይጣን ክርስቲያኖችን የሚያጠቃበት መንገድ /2ኛ ቆሮንቶስ 2፡11/**

ሀ. ሰነፎች ያደርግል

ለ. በተለያዩ ጉዳዮች እንድንጠመድ ያደርጋል

ሐ. በቅዥት፣ በመጨናነቅና በተለያዩ መንገዶች ይጫጫነናል

መ. የተጎዳንና ስሜታዊ እንድንሆን ያጠቃናል

ሠ ትችት፣ ተስፋ ያስቆርጠናል፣ ልንታረም እንዳንዘጋጅም ያደርጋል፡፡

ረ. ተስፋ ቢስነት

ሰ. በመንፈሳዊ ነገሮች ትዕቢት መኖር

2. **እንዴት መቋቋም ይቻላል፡፡**

*ሀ*. ችግሮች የሰይጣን መሣሪያ እንደሆኑ ማወቅ /ያዕቆብ 4፡7/

ለ. መጋፈጥ፣ መታገል፣ ሰይፍን ማንሣት /ኤፌሶን 6፡1-11/

ሐ የአንድ ወታደር መሣሪያ የሆኑትን መልበስ /ኤፌሶን 6፡10-18/

መ. በክርስቶስ ላይ መጣል /ሮሜ 13፡14/

ሠ. ቃሉን መጠቀም /ማቴዎስ 4፡4፤7፡10/

ረ. "ኃጢአት አላደርግም፣ በእኔ በሚኖረው በክርስቶስ ኃይል ኃጢአትን ድል እነሳለሁ"

ሰ. ፀሎት /ኤፌሶን 6፡18/

ሸ. የክርስቶስ ደም እንዲሸፍንህ መጠየቅና በበጉ ደም መከለል /ራዕይ 12፡11/

***ውይይት***፡- ከሰይጣን በኩል የሆነ ጥቃት ደርሶብህ ያውቃል? ልታሸንፈው የጠቀመህ ነገር ምንድ ነው?

## ትምህርት 4፡- የጌታን ፈቃድ እንዴት ማወቅ ይቻላል?

ብዙ አማኞች የሚቸገሩበት ጉዳይ አማኞች የጌታን ፈቃድ እንዴት እንደሚያውቁ ነው፡፡ ለእያንዳንዱ አማኝ ከጌታ ዘንድ ስለ ማንነቱ፣ ስለ ብቃቱ፣ ፍላጎቱ እና አካባቢው የተወሰነለት ነገር አለ /ኤፌሶን 2፡10/፡፡

- የእግዚአብሔር እቅድ ለአንተ የግልህ ነው /መዝሙር 32፡8/
- ዝርዝር የሆነ ነው /መዝሙር 37፡23/
- የተገለጠና ውስን ነው /ኢሳይያስ 30፡21/
- ስለ እቅዱ እንድንጠይቀው ይፈልጋል /መዝሙር 143፡8/፤ ይህም በየቀኑ በምናደርገው ፀሎት መሆን አለበት
- እቅዱ ሁልጊዜ መልካም፣ ተቀባይነት ያለው፣ ለእያንዳንዱ አማኝ ፍፁም የሆነ ነው /ሮሜ 12፡2/

1. **የእግዚአብሔር ዕቅድ የሚከተሉትን ሁኔታዎች ያካትታል፡-**

ሀ. ከኃጢአት መለየት በቅድስና መኖር /1ኛ ተሰሎንቄ 4፡3/

ለ. ፀሎትና ምስጋናን /1ኛ ተሰሎንቄ 5፡17-18/

ሐ. መልካም ሥራን መሥራት /1ኛ ጴጥሮስ 2፡15/

## 2. የመመራት መንገድ

ሀ. እግዚአብሔር በቃሉ በኩል ይመራል፤ እራስህን በጌታ ቃል አበልፅግ፣ የእሱ ፈቃድ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሐሳብ ጋር ተጋጭቶ አያውቅም

ለ. በውስጣችን በመንፈስ ቅዱስ የሚሰማን ማረጋገጫ /ሮሜ 8፡16፣ ሐዋሪያት ሥራ 13፡2 ፣ ዮሐንስ 16፡13/

ሐ. በሁኔታዎች እግዚአብሔር አንዳንድ በር ይዘጋል፤ ሌላውን ይከፍታል፤ ለጌታ ልጆች ድንገተኛ ክስተት የለም፡፡

መ. ተገቢ ያልሆነን ነገር ከኛ ማራቅ /ምሳሌ 6፡37-39/፤ ነገር ግን ሁሉም ሁኔታዎች የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብሎ ከማጠጋጋት መቆጠብ፡፡

## 3. የእግዚአብሔርን ምሪት ለማግኘት የጆርጅ ሙለር ቀመር

ሀ. የራስን ፈቃድ በመከተል በጉዳዮች ላይ ያለቀለትን ምርጫ አታድርግ፣ መካከለኛ ሁን!

ለ. በእግዚአብሔር ቃል በኩል የመንፈስን ፈቃድ ፈልግ፡፡

ሐ. መልካም የሆኑ መንግዶችን አስተውል፡፡

መ. ለምሪት ፀልይ፡፡

ሠ. እግዚአብሔርን ጠብቅ

***ውይይት፡-*** የእግዚአብሔርን ምሪት ያየህበት ነገር አለ ወይ? ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብለህ እንዴት ወሰንክ?

# ትምህርት 5፡- የፀጥታ ጊዜ

የፀጥታ ጊዜ የአማኞች ሚስጥራዊ የድል ጊዜ ነው፡፡ የፀጥታ ጊዜ ከሌለ መሸነፍ አለ፡፡

## 1. የጠዋት የፀጥታ ጊዜ የአብርሃም ጥሩ ምሳሌነት

ሀ. ጠዋት ይነሣል፣ ጥሩ ልምድ ነው!

ለ. እግዚአብሔርን ለማግኘት የግል ቦታ አለው፣ እኛም እንዲሁ እንሁን፡፡

ሐ. ይህን ትዝ ሲለው ብቻ ሳይሆን የየቀኑ ተግባሩ ነበር፡፡

መ. በጌታ ፊት ይቆማል፣ እስኪናገረውም ድረስ ይጠብቃል፡፡

## 2. ለፀጥታ ጊዜ የሚያስፈልጉ ነገሮች

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ፡- መጽሐፍ ቅዱስን ባቀድከው መሠረት አንብብ

ለ. ማስታወሻና እስክርቢቶ ከቃሉ ያገኘሽውን መጻፍ እትዘንጋ

ሐ. የፀሎት ጥያቄና የተመለሰልህን የምትጽፍበት መጽሐፍ ያዝ

## 3. የፀጥታ ጊዜ ዕቅድ

ሀ. ቢቻልህ በየቀኑ በተመሣሣይ ሰዓት ይሁን

ለ. በስልታዊ መንገድ 30 ደቂቃ ንባብና፣ 30 ደቂቃ ፀሎት በማድረግ አቅድ

ሐ. ግትር አትሁን፣ ፀሎትህን ቀጥል፣ መንፈስ ቅዱስ ከመራህና በውስጥህ ማንበብ ብቻ ከመጣ አንብብ፤ በእውቀት ተሞላም!

መ. የሚመከሩ ቅደም ተከተሎች

- አጭር ፀሎት
- መጽሐፍ ቅዱስ ማንበብ
- ፀሎት /ቃሉን ለፀሎትና ለልመና ሁሉ ተጠቀም/

# ትምህርት 6፡- መለየት /1ኛ ዮሐንስ 2፡15/

"አለምን አትውደድ" ፣ "ዓለም" የሚለው ቃል ምንድነው? ቀጣዩ ሐሳብ ያብራራዋል፡፡ አሁን ያለው በሰይጣን የተያዘው የዚህ አለም ሲስተም ነው፡፡

## 1. ማወቅ የሚገባን ስህተቶች፡-

ሀ. በአማኝና ባላመኑት መካከል ጋብቻ የተከለከለ ነው /2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14-17 እና አሞፅ 3፡3/

ለ. አለመቀደስና ሁሉም የጨለማ ሥራ /2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14/፤ ይህ የንግድ ሥራንም ያካትታል

ሐ. ውሸት፣ አረመኔነትና ሰይጣናዊ ሥራ /2ኛ ቆሮንቶስ 6፡15/

መ. ጣኦታት /2ኛ ቆሮንቶስ 6፡16/

ሠ. የሐሰት ትምህርት /1ኛ ጢሞቴዎስ 5፡5/

ረ. ሁሉም የኃጢአት አይነቶችና የሥነ-ምግባር ብልሹነት መስበርና ሌሎችም /1ኛ ጴጥሮስ 1፡16/፡፡

## 2. መከተል ያለብን ሐሳብ

ሀ. እምነትን ከእግዚአብሔር የሚሸረሽር ነገር መራቅ

ለ. መልካም ምስክርነትን ከሚያበላሹ ነገሮች መለየት
ሐ. መልካም ሥነ ምግባር ከሚያረክስና ወደ ኃጢአት ከሚመራ መሸሽ
መ. የማደርገውን ነገር ወንድሜን የሚያሰናክል ከሆነ መተው /1ኛ ቆሮንቶስ 8፡13/
ሠ. ማንኛውንም አካል፣ መንፈስና አዕምሮ ከሚጎዳ ነገር መለየት
ረ. ጌታን የሚያስደስት ከሆነ ማድረግ፣ ማድረግ ከሌለብን አለማድረግ/ 1ኛ ጴጥሮስ 2፡21/
ሰ. ታሪክን ያጠናክራል፣ ያደክማል /2ኛ ቆሮንቶስ 6፡17/

***ውይይት፡-*** ከኃጢአት ልምምድ መለየት አቅቶህ ያውቃል? እስከ ዛሬ የግጭት መንገዶች አሉ? እንዴት ልትፈታቸው ትችላለህ?

## ትምህርት 7፡- የእረኛ የግል ሕይወት

እረኛ ቆሞ በሚሰብከው ሕዝብ ፊትና እይታ የግል ሕይወቱ በጣም ወሳኝና አስፈላጊ እንደሆነ መዘንጋት የለበትም፡፡ ታላቁ ሐዋሪያ ጳውሎስ ወጣቱን ሰባኪ ጢሞቴዎስን ሲመክር ስለ ሕይወት ንጽህና ብሎም ኃይማኖትን ስለ መጠበቅ ያነሣሣው ነበር፡፡ ሰባኪው የተናገረውን የማይኖር ከሆነ ሕዝቡ ይታዘቡታል፡፡

1. እረኛ የኃይማኖት ሰው፣ ፃድቅና በጌታ ነገር የተነቃቃ መሆን አለበት፡፡
2. ***ከቤተሰቡና ከትዳር አጋሩ ጋር ጤናማ ሕብረት ያለው፤ በዚህም ለመንጋው ምሳሌ*** መሆን ይጠበቅበታል፡፡
3. የፀሎት ሰው ሊሆን ይገባል፤ ሕዝቡ ብዙ ጊዜያትንና ሰዓታትን እንደሚፀልይ ይጠብቃል፡፡ ይህም መንፈሳዊ ጥንካሬውን እንዲጠብቅ ይረዳዋል፡፡ ሰይጣን ወደ እግዚአብሔር ሰው ብዙ ፈተናዎችን ይልካል፡፡ ሁሉም ተግዳሮቶች እስኪወገዱ ድረስ ግን በጌታ ፊት መቆየት አለበት /ኢሳይያስ 52፡11/፡፡ ለመንጋው መፀለይ /1ኛ ሳሙኤል 13፡11፣ ቆላ 1፡9/፤ ፀሎቱም የሕዝቡን ስም አንድ በአንድ እየጠራ መፀለይ አለበት፡፡
4. ለጥፋት፣ ፍቅርንና ርህራሔ ያለው መሆን አለበት /ሐዋሪያት ሥራ 20፡31/

***ውይይት፡-*** ለአንተ ምሳሌ የሆኑ መሪዎች ካሉ ዘርዝር፤ ጥሩ ባህሪያቸውም እንደሆነ ግለጽ?

## ትምህርት 8፡- የውስጥ መነሳሳት

የእግዚአብሔር አገልጋይ በጤናማ ተነሳሽነት ለጌታ ክብር ሊያገለግል ይገባል። የጳውሎስ ተነሳሽነት ገንዘብና ዝና አይደለም፤ ነገር ግን ሰው በእምነት የሚያገኙትን መዳን ነው። በዚህም የሰዎች መዳን አስቸኳይነትና ሸክሙ ይገፋፋው ነበር /1ኛ ቆሮንቶስ 1፡15-18/። መብላትና መጠጣት እንኳ ቢሆን፣ ካመነበት ብቻ ነው የሚያደርገው /1ኛ ቆሮንቶስ 9፡4/።

ጥርጣሬን ለማስወገድና ነፍሳትን ለማሸነፍ በቆሮንቶስ ክፍያ ሲሰጠው እምቢ ብሏል። የተለያዩ ሰዎችን ባህሪይ የተለማመደ ነበር /1ኛ ቆሮንቶስ 9፡19-23/። ሰዎች የሚድኑ ከሆነ ልጆችንም፣ ቤተሰቡንም ሁሉ መተው አለበት። የጳውሎስ ድንቅ መልዕክት የጊዜው ማጠር፣ የሞት መቅረብ እና የኢየሱስ ክርስቶሰ መምጣት ሁሉንም ለክርስቶስ ክብር ያደረግ ነበር /ቆላስይስ 3፡17፣ 1ኛ ቆሮንቶስ 10፡31/።

***ውይይት***፡- ጳውሎስ ስለ አገልግሎቱ የከፈለው ዋጋ ምንድነው? ስታስበው ጠቃሚ ናቸውን? በዚህ ትምህርት ከተጠቀሱት አራቱ የጳውሎስ ተነሳሽነቶች ላይ ያለህን አስተያየት ስጥ።

## ትምህርት 9፡- የመንፈሳዊ መሪ መስፈርቶች

1. ኩነኔ የሌለበት፡- የተመሰከረለት፣ የተከበረና መልካም ባህሪይ ያለው /ቲቶ 1፡6/
2. የአንዲት ሚስት ባል /ቲቶ 1፡6/
3. ታማኞች፣ የሚታዘዙና ለወላጅ የሚገዙ ልጆች ያሉት /ቲቶ 1፡6/፤ ይህ ፈተና ነው እንዲህ አይነቱ ሰው የቤተክርስቲያን መሪ ሊሆን ይችላል
4. ራስ ወዳድና መጋቢ ሊሆን ይገባል /ቲቶ 1፡7/
5. የማይቆጣ ሊሆን ይገባል /ቲቶ 1፡7/፤ ቁጣንና ንዴት ቦታ የላቸውምና!
6. የማይጠጣ /የማይሰክር /ቲቶ 1፡7/
7. የማይጨቃጨቅ /ቲቶ 1፡7/
8. ረብ የማይፈልግ /ቲቶ 1፡7/፣ የቤተክርስቲያ ገንዘብ ወጥመድ እንዳይሆንበት!
9. እንግዳ ተቀባይ /ቲቶ 1፡8/ ለአማኞችና ለእንግዶች ፍቅር ያለው!

10. መልካም የሆነውን የሚወድ ንፁህና ግብረ ገብነት ያለው /ቲቶ 1፡8/

***ውይይት***፡- የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ለቤተክርስቲያን መሪ አስፈላጊ መሆናቸውን አስተውል፡፡ አንተ የምትጨምራቸው ሌሎች ባሪያት አሉን?

## ትምህርት 10፡- ዝሙት

ሰይጣን የእግዚአብሔርን አገልጋይ ለመፈተን የማያደርገው ነገር የለም፡፡ በአገልግሎቱ ከፍ ያለውን ሰው ከመጣል በላይ የሚያስደስተው ነገር የለም፤ በጣም ጠንካራና ፈታኝ ነው! ከዚህም አልፎ ጌታን የሚፈሩትን ጨምሮ ሊጥል ይፈልጋል፡፡ አስደንጋጭ እውነቱ ግን ብዙ የጌታ አገልጋዮች ከደረሱበት መንፈሳዊ ጫፍና የድል ደረጃ እንደሚወድቁ፣ ሕይወታቸው በሽለቆ ውስጥ በማስገባት ከቤታቸው ጋር ያለውን ነገር እንዲበላሽ ማድረጉ ነው፡፡ አገልግሎታቸው ይመታል፣ ባህሪያቸው የማይጠገን የሆናል፣ በዚህም የክርስቶስ ቤተከርስቲያን ትጎዳለች፡፡

የእግዚአብሔር አገልጋይ ሁልጊዜ ፈተናዎችን ለመቋቋም የፀና መሆን አለበት፡፡ አሁንም ነገር በለጋነቱ ማስወገድ ያስፈልጋል፡፡ ለሴቶች ሲፀልይ ወይም ሲመሰክር ከመሪዎች ጋር ወይም ከሚስቱ ጋር መሆን አለበት፤ ማንኛውም ትክክል ያልሆኑትን ነገሮች ማስወገድ አለበት፡፡

እግዚአብሔር ከሰይጣን ሐሳብ እንዲጠብቅህ ፀልይ፡፡ ነገር ግን ማንኛውም አደጋዎች ምልክታቸውን ተረዳ፤ ተጠበቅ፣ ፀልይም፡፡

***ውይይት***፡- ሳምሶንና ዳዊትን ተመልከት፤ ከሴቶች ጋር የነበራቸው ያልተገባ ህብረት ታላቅ ኃዘን ወደ ሕይወታቸው አምጥቷል፡፡

## ትምህርት 11፡- መሪነትና በቤተሰብ

የመድረክ አገልግሎት በቤት የጀመረ መሆን አለበት፡፡ ኤሊ ኃጢአተኛ የሆኑ ልጆችን መቆጣጠር ተስኖት እንደተቀጣ፤ አብረሃም ለቤቱ ታማኝ መሆኑን እግዚአብሔር አይቶ የላቀ ኃላፊነት እንዲሰጠው ማየት ይቻላል፡፡

1. **አማኝ የሆነ መሪ ጥሩ ባል መሆን አለበት፡፡** ለትዳር አጋሩ ያለው መነቃቃት፣ በመንገዱ ሁሉ በሴት እንዳይፈተን ይረዳዋል፡፡ ለሚስቱ የሚያደርገው እንክብካቤና ለቤት ልጆች ያለው አክብሮት በቤተክርስቲያን ያለውን አገልግሎት ይወስነዋል፡፡

2. **ልጆች በሥርዓት ያደጉ፣ የፍቅር ውጤት ሊሆኑ ይገባል።** 1ኛ ጢሞቴዎስ 3፡12 የሚታዘዙና የሚገዙ መሆን አለባቸው። ልጆች ሲያከብሩት ያላየ እንግዳ ሰው አባታቸውን ለማክበር ይቸገራል።

3. **የመሪዎች ቤት ለአማኞችና ለእንግዶች ክፍት መሆን አለበት።** ቲቶ 1፡8 ወደ ቤታቸው የሚሄዱ አማኞች ክርስቶስ ያለበት ቤት መሆኑን እንዲያውቁ የሚያደርግ አምላካዊ መንፈስ ሊኖር ይገባል።

***ውይይት፡-*** የአማኝ መሪ ልጆች ለሌሎች ወጣቶች ምሳሌ እንዲሆን የሚያደርግ ነገር ምንድነው? የት ነው ልምምዱ መጀመር ያለበት፡

## ትምህርት 13፡- ገንዘብ

በዚህ አለም ያሉ ሰዎችም ሆኑ አማኞች ያለባቸውን እዳ የሚከፍሉ ታማኞች መሆን አለባቸው። መጥፎ ነገሩ ይህ ሳይሆን፣ ብዙ የንግድ ሰዎች ለወንጌላዊያን ገንዘብ ለማበደር ፈቃደኛ አለመሆናቸው ነው። ምክንያቱም ደግሞ የወንጌላዊያን አለመታመንና ዋሾ መሆን ነው። አማኝ መሪ በጌታ ስም ተገቢ ያልሆነ ነገር ላይ መገኘት የለበትም። የጳውሎስ መመሪያ ግልጽ ነው፡- ከፍቅር በቀር የማንም እዳ አይኑርባችሁ /ሮሜ 13፡8/! የራሱንም ገንዘብ ሆነ የቤተክርስቲያንን ገንዘብ በጥንቃቄ መያዝ የአማኝ መሪ ተግባር ነው። ለመክፈል ቃል ከተገባ መከፈል አለበት፤ ካልሆነ ግን አገልግሎቱ ይዳከማል፣ የጌታም ስም ይነቀፋል።

***ውይይት፡-*** ሮሜ 12፡17ን አንብብ። በአንተ አመለካከት ትርጉሙ ምን ይመስላል? ገንዘባቸውን በሚገባ የማይዙ፣ ትኩረት የማይሰጡ እና የማይታመኑ አማኝ ሰራተኞችን ታውቃለህ?

## ትምህርት 14፡- የተሰወነ ጥናት

ጳውሎስ ወጣት አገልጋይ የሆነውን ጢሞቴዎስን ለማንበብ ትኩረት እንዲያደርግ ይመክረዋል /1ኛ ጢሞቴዎስ 4፡13/። ሁሉም ሰባኪ ለማንበብ የተዘጋጀ፣ ነገሮችን ሁሉ በማንበብ ስለ ሚሰብከው ቃል የጠለቀ እውቀት ሊኖረው ይገባል። የሚከተለውን አስተያየት ልብ በል፡- የሚሰሙህ ሰዎች ሁልጊዜ ከአንተ አዲስ ነገር መማር መቻል አለባቸው። በማብራሪያዎችና ጥናት የተደገፈ መጽሐፍ ቅዱስ በነፃነት መነበብ አለበት፤ ብዙ

የእግዚአብሔር ሰዎች የፃፉትንም ጨምሮ በተገቢ ሁኔታ ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋል፡፡

***ውይይት፡-*** በቃሉ የሚያጠናክር ነገር በቅርቡ ያነበብከው ምንድነው? አንዳንድ ሐሳቦች ጥቀሳቸው፡፡

## ትምህርት 15፡- አካልን ማብቃት

አካላችን የእግዚአብሔር ማደሪያ ስለሆነ በተገቢ ሁኔታ መያዝ አለበት /1ኛ ቆሮንቶስ 3፡16/፡፡ የተመጣጠነ ብላ እንጂ፣ ከአቅም በላይ አትብላ፡፡ በጊዜ ተኛ፣ በጊዜ ንቃ፤ እንቅስቃሴዎችን በየቀኑ አድርግ፡፡

ጥሩ የጤንነት ልማዶች ለጌታ ተጨማሪ አመታትን እንድታገለግል ይረዱሃል፡፡ ቀለል ያለ ኑሮና ብዙ ማሰብ /ማወቅ/ የሁል ጊዜ ተግባርህ ይሁን፡፡

***ውይይት፡-*** የአካል ብቃት ከሚደግፉ እንቅስቃሴዎች የተወሰኑትን ተግብር፡፡ ጤናን የሚጎዱ ሌሎች ነገሮች ካሉ ተነጋገሩ፡፡

## ትምህርት 16፡- ስንፍና

ጳውሎስ "ሞኞች ልንሆን አይገባም" /እብራውያን 6፡12/ ማለቱ በምክንያት ነው፡፡ አማኝ ሠራተኛ /አገልጋይ/ በስንት ሰዓት ገባህ? ምን ሠራህ? በስንት ሰዓት ወጣህ? የሚል ተቆጣጣሪ ላይኖርበት ይችላል፡፡ ሆኖም ወደ መድረክ ይወጣና ከዚህ በፊት የተናገረውን ስብከት ይደጋግማል፤ በፀሎት በቂ ዝግጅት ስላላደረገም የሚሰብና ትምህርት ሰጪ ሰው አይሆንም፡፡ ሕዝቡ እረኛ እንደሌለው ያስባል፤ ምክንያቱም ስለሕዝቡ ጥቂት ስለሚያስብና ጥቂት ስለሚያገለግል፡፡

የመከር ወቅት ጊዜው አጭር ነው፡፡ "በመከር የሚተኛ ልጅ የሚያሳፍር ነው" /ምሳሌ 10፡5/፤ "ከእንቅልፍ የምትነሱበት ሰዓት እሁን እንደደረሰ እወቁ" /ሮሜ 13፡11/፡፡ አንተ የክርስቶስ አገልጋይ ነህ ባለቤቱ ጠርቶህ የከበረ ሥራ ሰጥቶሃል፡፡

በጠዋት ተነሣ፣ የአምልኮን እቅድ ተከተል፣ አገልግሎቱንም አገልግል፣ ሰዓቶችህ ሁሉ ጠቃሚ ይሁኑ "አንተ የምትተኛ! ንቃ!" /ኤፌ 5፡14/፡፡

## ትምህርት 17፡- ምስጋና

ከመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ እየሄድክ ነው? በምድረ በዳ ግራ መጋባት ተከበሃል? በከንቱ ነገሮች አእምሮህን ታጨናንቃለህ? ጨለማውን ለማስወገድና ስንፍናን ለማራቅ ትልቁ ቁልፍ ነገር ምስጋና ነው፤ ምስጋና መድኃኒት ስለሆነ በአካልህና በመንፈስህ ታምራት ይሠራል /ምሳሌ 15፡13፤17፡22/፡፡ አመስግን! ስላለህበት ሁኔታ በእግዚአብሔርም ሆነ በሌሎች በማጉረምረም ጊዜህን አታጥፋ፡፡ አይንህን ከሁኔታዎች ላይ አንስተህ በጌታ ላይ ብቻ አድርግ፤ ህመምህንና ቁስልህን እርሳው፡፡ ችግርችህ ወደ ምስጋና የምትቀርብበት ዕድል ጨለማ እንኳ ቢሆን ምስጋና የሚገባውን ለአንድ አምላክ እንደሆነ ለአለም በመንገር ነው፡፡

አንዳንዴ ማመስገን ቀላል አይሆንም፤ ስለዚህም ነው ያለማቋረጥ የምስጋናን መስዋዕት ለጌታ እንድታቀርብ የምናስተምርህ፡፡ ለፀሎት ስትንበረከክ ልመናህን ተውና መዝሙር 103 እንዲሁም ሌሎችን የምስጋና ጥቅሶች በማንበብ በምስጋና ላይ ብቻ አትኩር፣ እርሱንም አምልክ፤ ደግሜም እላለው ደስ ይበልህ!

***ውይይት***፡- 2ኛ ቆሮንቶስ 20፡22 አንብብና የምስጋናን ውጤት ተመልከት፤ የመዝሙር መጽሐፍትንም ከልሰህ ለምስጋና የሚያዘጋጁ ሐሰቦችን ጥቀስ፡፡

## ትምህርት 18፡- ፈተና በሚመጣበት ጊዜ

ፈተና ወደ እግዚአብሔር አገልጋይ በሚመጣበት ጊዜ ራስን የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ለኃጢአት የተገፋህ በሚመስልህ ሰዓት መንፈስ ቅዱስ የሚከተሉትን ነገሮች በማድረግ እንደሚደግፍህ አስተውል፡-

1. እግዚአብሔርን አስታውስ /ዘፍጥረት 39፡9፣ 1ኛ ሳሙኤል 2፡ 22-25/
2. እራስህን አስብ /1ኛ ቆሮንቶስ 6፡18፣ ምሳሌ 6፡32/
3. ስለትዳር አጋርህ አስብ /ሚልኪያስ 2፡14-16/
4. ከአንተ ጋር በኃጢአት ውስጥ ያለውን አስብ /ማቴዎስ 18፡6/
5. ስለ ልጆችህ አስብ /ዘኁልቁ 14፡33/
6. ስለ ቤተሰብህ አስብ /ዘፍጥረት 12፡17፤ 20፡18/
7. ስለ ፀፀት አስብ /ምሳሌ 5፡11-14፤ 6፡32-33/

8. ቤተክርስቲያንን አስብ /1ኛ ቆሮንቶስ 5፡1-6፤ 1ኛ ሳሙኤል 2፡24/
9. ስላላመኑት አስብ /ሮሜ 2፡22 እና 24/
10. ስለ ወንጌል ጠላቶች የሆኑትን አስብ /2ኛ ሳሙኤል 12፡13-14/
11. ስለ አገልግሎትህ አስብ /መሳፍንት 16፡19-20፣ 1ኛቆሮንቶስ 9፡27/
12. ስለ እግዚአሔር ፍርድ አስብ /እዮብ 13፡4፣ ሕዝቅኤል 16፡38/
13. ስለ ዘላለም አስብ /ገላትያ 5፡19-21/
14. በመጨረሻም ኃጢአትን በማሸነፍ የወደፊት ክብርን አስብ /ራዕይ 14፡4/
15. ውይይት፡- ከላይ ከተዘረዘሩት የትኛው ነው በጣም ጠቃሚ የሚሆነው? ለምን?

## ትምህርት 19፡- ተከታዮች

ሰዎች መድረክ ላይ ያለን ሰው ወደዱም ጠሉም በክፉ ሆነ በመልካም መከተላቸው አይቀርም፡፡ ጳውሎስ በኤፌሶን 5፡1 ላይ እግዚአብሔር የምትከተሉ ሁኑ ይላል፡፡ መልካም ሰው መሪውን ይከተላል፤ መሪው ደግሞ ለመንጋው መልካም ምሳሌ የመሆን ኃላፊነት አለበት፡፡ መሪው ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ለመሄድ ጥንቃቄ የሚያደርግ ከሆነ፣ ተከታዮች በቅድስና መንገድ ለመጓዝ አይቸገሩም፡፡ ነገር ግን በኃጢአትና በከንቱ መንገድ ለመሄድ ቢያመችም ተከታዮቹ በኃጢአት መንገድ ለመሄድ የሚከለክላቸው የለም፡፡ የጠፋትን በመፈለግ፣ ነፍሳትን በመማረክ፣ ቀናተኛ ከሆነ አብረውት የሚሰብኩ ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች ያገኛል፡፡ ነገር ግን መሪ የጠፋትን ለመፈለግ የሚዘገይ ከሆነ፣ ተከታዮች የእሁድ አማኞች፣ ቃሉን ሰሚዎች ብቻ እንጂ ተግባሪዎች አይሆኑም፡፡ መሪው ሕይወቱን በመስጠት ምሳሌያዊ መስዋዕት አድርጎ ከሆነ፣ አማኞች የኪስ ቦርሣቸውን ከፍተው ለጌታ በመስጠት ደስተኞች ይሆናሉ፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ 1፡6 ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎችን “የጌታና የእኛ ተከታዮች ሁኑ” ሲል ያዛል፤ እንዲሁም ነቀፋ የሌለበትን ሕይወት ለመኖር ስለወሰነ፣ “እኔን እንድትመስሉ አደፋፍራችኋለሁ” /1ኛ ቆሮንቶስ 4፡16/ ይላል፡፡ ***ውይይት***፡- የአንተ የሕይወት ምሳሌ እንዲህ ነው ለማለት ያስችላልን?

## ትምህርት 20፡- ድል የተረጋገጠ ነው!

/ፊልጵስዩስ ምዕራፍ 3 እና 4 ን አንብብ/

ብዙ የእግዚአብሔር አገልጋዮች ውስጥን በሚከነክን የበታችነት ስሜት ይሰቃያሉ፤ ያልበረቱም ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም የእግዚአብሔር አገልጋይ ነኝ ብሎ ራስን ማስተዋወቅ ይሳናቸዋል፡፡ እግዚአብሔር ግን "የሠራዊት ጌታ አገልጋዮች" እንደ ሆኑ ይቆጥራቸዋል /ዳንኤል 3፡26/፡፡ ይህ እግዚአብሔርን ለማገልገል ያለው የጳውሎስ አስተሳሰብ ነው

/1ኛ ጢሞቴዎስ 1፡11-12/፡፡ እግዚአብሔር የኃይል መንፈስ ሰጥቶናል /ብሐዋሪያት ሥራ 1፡8/ "ኃይል" የሚለውን ቃል ትርጉሙ ዳይናማይት /dynamite/ ይባላል፡፡ ይህን መለኮታዊ ሃይል የሚቋቋም ማንም የለም፡፡

ታናሹ ጳውሎስ ታላላቅ ነገሮችን ያደረገው በእግዚአብሔር ኃይል ባለው መታመን ነበር፡፡ ኃይሉንም ማመን ብለም እንዲሠራ ማድረጉን አረጋግጥ፤ ታላቁን ኃይል በአንተ እንዲገልጥም ለእግዚአብሔር ዕድል ስጥ፡፡ እግዚአብሔር ***አንተን /አንቺን/*** ይፈልግሃል/ሻል፡፡

***ውይይት፡-*** እግዚአብሔር ትንንሽ ነገሮችን በመጠቀም የፈፀመበትን ሐሳብ የያዙ ጥቅሶችን አንብብ /ዘፀአት 4፡2፤ መሳፍንት 15፡15፤ 1ኛ ሳሙኤል 17፡40፣ ዘካሪያስ 4፡10፤ ማቴዎስ 13፡32 ዩሐንስ 6፡9/፡፡ ትልቅ እውነት ያለው በ1ኛ ቆሮንቶስ 1፡27-29 ስለ ሆነ አሰላስል፣ በቃልህም ተናገር፡፡

## የአብያተ ክርስቲያናት ሕብረት

### መግቢያ

ሁሉም አብያተ ክርስቲያናት የየራሱ የሆነ ባህሪያቶች አሉት፣ ለእያንዳንዳቸው እንደ የባህሪያቸው ይህንን ትምህርት አትሞ ማቅረብ አዳጋች ሊሆን ይችላል፡፡

አስተማሪዎቻቸው የሚከተሉትን መመሪያዎች በመጠቀም ለእያንዳንዳቸው እንደሚመች አድርገው ያስተምሩባቸው፡፡

ከትምህርቱ መጨረሻ ይህ አስተምህሮ በጥልቀትና በአዲስ መልክ /በዝርዝር/ የአገልግሎት ዘርፍን የሚያጠነክር መሆን አለበት፡፡

# ክፍል ስድስት
# የአብያተክርስቲያናት ሕብረት
## ቤተ ዕምነትህን አጥና
***ትምህርት አንድ፦*** ቤተ እምነትህ የሚመሩ ሰዎች ታሪካቸው፣ የቤተዕምነታችሁ የቀድሞ መስራችንና መሪዎች፣ የተመሠረተበት አላማ፡፡
***ትምህርት ሁለት፡-*** አገርህ የቤተእምነትህ ታሪክ፣ የሚሠራበት ሕዝብ፣ በእያንዳንዱ ብሔር መካከል ያለ ቤተክርስቲያን ብዛትና መሪዎቻቸው፡፡
***ትምህርት ሶስት ፣አራት፣ አምስት፡-*** የአስተምህሮ ልዩነቶች ከሌላው ቤተዕምነት እንዴት ይለያሉ፤ የተለየ ትኩረትና አገልግሎቶቻቸው፤ የልዩነቶቻቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት፡፡
***ትምህርት ስድስተ፦*** የቤተዕምነቱ አገራዊ መዋቅር፣ ዋና ቢሮና ሠራተኞች፣ የመሪዎች ብዛት፣ የአገልግሎት ዘመንና የአመራረጥ ዘዴዎች፡፡
***ትምህርት ሰባት፡-*** የቤተዕምነቱ ትምህርት ቤቶች፣ ሆስፒታሎች፣ የየክፍሉ
***ትምህርት ስምንት፡-*** የየአውራጃዎች መሪዎችና ቤታቸው፣ የአውራጃዎች ስብሰባና እቅዶች፡፡
***ትምህርት ዘጠኝ፦*** የማህበረሰቡ የትምህርትና የጤና አቅርቦት፣ በየአውራጃዎች ያሉ መንደሮችና አስተማሪዎቻቸው፡፡
***ትምህርት አስር፡-*** በየቤተዕምነቱ የነገ አገልጋዮች የሚማሩበት ትምህርት ቤት፡፡
***ትምህርት አሥራ አንድ፦*** አዲስ አስተማሪና የሚጠበቅበት የአገልግሎት ብዛት፡፡
***ትምህርት አሥራ ሁለት፡-*** አዲስ አማኞችን ለጥምቀት ማዘጋጀት፣ የቤተዕምነቱን ሥርዓት መከተል
***ትምህርት አሥራ ሶስት፡-*** አባላት በኃጢአት ሲወድቁ አስተማሪው ምን ማድረግ አለበት፣ ቤተዕምነቱ ችግሮችን የሚፈታበት መንገዶች
***ትምህርት አሥራ አራት፡-*** በጠንቋዮችና በባህል መሪዎች ተቃውሞ ቢገጥመው አስተማሪው ምን ማድረግ አለበት፡፡
***ትምህርት አሥራ አምስት፦*** የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች እንዴት ይዘጋጃሉ፡፡

***ትምህርት አሥራ ስድስት፡-*** አስራቶችን መቀበልና የቤተዕምነቱ የገንዘብ አስተዳደር፡፡

***ትምህርት አሥራ ሰባት፡-*** የቤተ እምነቱን ሕንፃ በመንደሮች መገንባት፡፡

***ትምህርት አሥራ ስምንት፡-*** የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናትና የወንጌል ቡድን፡፡

***ትምህርት አሥራ ዘጠኝ*** ፡- ለሳምንታዊ የወንጌል ሥርጭት አስተማሪዎችን በጋራ ማሠማራት፡፡

***ትምህርት ሃያ፡-*** ከባድና አስጨናቂ ሁኔታ በአማኞች መካከል ቢፈጠር አስተማሪዎች ከማን ምክር ያገኛሉ?

# ዋቢ መጻሕፍት

Alan, Douglas. *100 Bible Lessons*. Gospel Literature Service, Bombay, India.

Balchin, John. *Compact Survey of the Bible*. Bethany House Punlishers, Minnneapolis, MN.

Evans, William. *The Grerat doctrines of the Bible and How to Prepare Sermons.* Moody Bible Institute of Chicago, Moody Press. Used by Permisiion.

McGree, J. Vernon. *Books of the Bible and Brifing the Bible*. Thru the Bible Books, Pasadena, CA.

Mead, Henrietta. What the Bible Is All Abaout. Regal Books, Div.of Gospel Light, P.O. Box 3875, Venture, CA 93006. Used by permission.

Stanley, Dr. Liliane, The Ideal woman, and Stanley, Rev.R., Preachers and People Blessings Books, Post Bag 609, Vellore 632006, Indina

*ማስታወሻ* ፡-

ለተቀናጀ ትምህርት ቤት ጥቅም እንዲውል
እነኚህን መጽሐፍት ላሳተሙት ታላቅ
አክብሮትና እድናቆት እንገልጻለን፡፡

በአፍሪካ እና በኢሲያ የክርስቶስን ወንጌል ለመስበክ የነበሩት በሮችና ምላሾች እምብዛም ነበሩ፤ በዚህ ክፈለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ግን በተጠቀሱት አህጉራት በሚገኙ ሀገራት የኢየሱስ ክርስቶስ ቤተክርስቲያን በአሃዝ ከፍተኛውን ቁጥር እያስመዘገቡ እንደሆነ ጥናቶች ያረጋግጣሉ።
ምንም እንኳ ይህ የደስታችን ምክንያት ቢኾንም፣ ስራው እንደሚገባ አለመሰራቱን ግን መሸፈን አይቻልም። በአዳዲስ የወንጌል ሰበካ ቦታዎች ወደ ጌታ የመጡ አዳዲስ ነፍሳት ያለመጋቢ ብቻቸውን ቀርተዋል ምክንያቱም "በጎቼን መግቡ" የሚለው የእረኛው ትዕዛዝ ማንም ስለማይፈጽም! በሺዎች የሚቆጠሩ መንደሮች የእግዚአብሔር ቃል የሚያሰሙበት መድረክ፣ የማህበረ ምዕመናን /ጉባኤ/ ሕይወት እና ለመንጋው ግድ የሚለው እረኛ የላቸውም።

ይህን ዐብይ ፍላጎት ለመድረስ የተቀናጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ንቅናቄ በዛየር ተቀረጸ። እቅዱ ግልጽ ነው፡- የወንጌላውያን ቡድን በወንጌል ያልተደረሱ መንደሮችን ይጎበኛሉ፤ በእያንዳንዱ መንደር አገልግሎት ማብቂያ አማኞች ለስምንት ሳምንታት ለሚሰጠው አገልግሎት ማዘጋጃ ትምህርት አንድ ተወካይ ሰው ይመርጣሉ። ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ወደ የመንደራቸው በቀላሉ ተመልሰው ምግብና ሌሎች አቅራቦቶችን ማግኘት የሚያስችል ማዕከላዊ ቦታ ላይ ይሆናል። ከሁለት ወር በኃላ ተማሪዎቹ በየመንደሮቻቸው መጋቢያን ይሆናሉ።
በዛየር የተቀናጀ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምስረታ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ከአስራ አንድ ሺህ በላይ የሚኾኑቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተወካዮች፣ በመንደራቸው የሚገኙትን ማህበረ ምእመናን የሚመሩ ትምህርቱን አጠናቅቀዋል።

መጽሐፉ የተዘጋጀው በተቀናጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለስምንት ሳምንታት ያህል ነው፤ ሆኖም በቤት የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ፣ ለስብከት ዝግጅት፣ ለቤተሰባዊ አምልኮ እና መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጥቀም ይችላል።
የተቀናጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው አድረሻ መጠቀም ይቻላል፡-


Evangelism Resources
425 Epworth Avenu
Wilmore , Kentucky 40390
E-mail : eroffice @qx.net



ምንም እንኳ ይህ የደስታችን ምክንያት ቢኾንም፣ ስራው እንደሚገባ አለመሰራቱን ግን መሸፈን አይቻልም። በአዳዲስ የወንጌል ሰበካ ቦታዎች ወደ ጌታ የመጡ አዳዲስ ነፍሳት ያለመጋቢ ብቻቸውን ቀርተዋል ምክንያቱም "በጎቼን መግቡ" የሚለው የእረኛው ትዕዛዝ ማንም ስለማይፈጽም! በሺዎች የሚቆጠሩ መንደሮች የእግዚአብሔር ቃል የሚያሰሙበት መድረክ፣ የማህበረ ምዕመናን /ጉባኤ/ ሕይወት እና ለመንጋው ግድ የሚለው እረኛ የላቸውም።

ይህን ዐብይ ፍላጎት ለመድረስ የተቀናጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ንቅናቄ በዛየር ተቀረጸ። እቅዱ ግልጽ ነው፡- የወንጌላውያን ቡድን በወንጌል ያልተደረሱ መንደሮችን ይጎበኛሉ፤ በእያንዳንዱ መንደር አገልግሎት ማብቂያ አማኞች ለስምንት ሳምንታት ለሚሰጠው አገልግሎት ማዘጋጃ ትምህርት አንድ ተወካይ ሰው ይመርጣሉ። ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ወደ የመንደራቸው በቀላሉ ተመልሰው ምግብና ሌሎች አቅራቦቶችን ማግኘት የሚያስችል ማዕከላዊ ቦታ ላይ ይሆናል። ከሁለት ወር በኃላ ተማሪዎቹ በየመንደሮቻቸው መጋቢያን ይሆናሉ።

በዛየር የተቀናጀ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምስረታ የመጀመሪያዎቹ ስድስት ወራት ከአስራ አንድ ሺህ በላይ የሚኾኑቱ የኢየሱስ ክርስቶስ ተወካዮች፣ በመንደራቸው የሚገኙትን ማህበረምእመናን የሚመሩ ትምህርቱን አጠናቅቀዋል።

መጽሐፉ የተዘጋጀው በተቀናጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ለስምንት ሳምንታት ያህል ነው፤ ሆኖም በቤት የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት፣ ለስብከት ዝግጅት፣ ለቤተሰባዊ አምልኮ እና መጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጥቀም ይችላል።
የተቀናጀ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤትን አስመልክቶ ተጨማሪ መረጃ በሚከተለው አድረሻ መጠቀም ይቻላል፡-

Evangelism Resources
425 Epworth Avenu
Wilmore , Kentucky 40390

ይህ መጽሐፍ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ ለሆኑቱ፣ በከተማና ገጠር ድነት ለሚያስፈልጋቸው ሰዎች ሁሉ የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት ለሚሰብኩ ብሎም ታላቁን ተልዕኮ ለማገልገል ለተጠሩ ቡድኖች የተዘጋጀ ነው፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ለለየው ታማኝ አገልግሎት ለመዘጋጀት፣ ራስንም ለመመገብ እንዲቻል በጸሎት፣ በጥናት እና በአገልግሎት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡ መጽሐፉን ገንዘብ በማድረግ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የመምራት ብሎም ያልዳኑትን ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ በማምጣት የማሳደግን አደራ ይወጡ!

ከመስመር የወጣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ ባህሪይ ከአገልግሎታችን ማስወገድ አለብን፡፡ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር መስበክ፣ ኃጢአትን መታገስ ስለ ማይቻለው ቅድስና መናገር፣ ስለ ሲኦልና ገነት፣ ከጌታ ጋር ስላለው ሕብረት፣ መሰጠትና አገልግሎት፣ ስለ ወንጌል ስርጭትና ዘላቂ መንፈሳዊ መነቃቃት ከመናገር ዝም ልንል አይገባም፡፡

ይህ ግሩም ወቅታዊ መጽሐፍ አንባቢያን ራሳቸውንና ሌላውን ከማብቃት አንጻር መጽሐፉ የተዘጋጀበትን ዓላማ እንዲመቱ ያደርጋቸዋል፡-

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፡- ስድሳ ስድስቱ የብሉይና አዲስ ኪዳን ቅዱሳት መጻሕፍት የእግዚአብሔር ፍቃድ ለሠዎች ተጽፎ የተገለጠበት መጽሐፍ አቻ የለሽ የእምነት መሰረትና የህይወት መመሪያ መሆኑን በመገንዘብ ቅዱሳት መጽሐፍቱን በሁለንተናው እንዲያነቡት፣ እንዲያጠኑት፣ አንዲታመኑት፣ እንዲታዘዙትና ለሌሎች አንዲያስተላልፉት ያግዛል፡፡

አስተምህሮአዊ ፡- መሰረታዊ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የክርስትና አስተምህሮቶች ማለትም አስተምህሮተ እግዚአብሔር ፣ ክርስቶስ፣ መንፈስ ቅዱስ፣ ሰው፣ ድነት ፣ በቴተክርስቲያ ፣ መላዕክት፣ የመጨረሻው ዘመን የማሳሰሉትን በቅጡ በመረዳት ሌሎችን ማስረዳት የሚችሉ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

ነገረ-መለኮታዊ ፡- የእግዚአብሔርን ህዝብ ከመመገብና ከማብቃት አንጻር ኢየሱስ ክርስቶሰን (ቃሉን) ማዕከል ያደረገ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሰብከት አገልግሎት ፣ ዘላቂ የወንጌል ሥራ ባለአደራነትና መንፈሳዊ መነቃቃት እንዲሁም የቅድስና ህይወት መገለጥ ወሳኝነት ነገረ-መለኮት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ያስገነዝባል፡፡

Disign & Print Glory Ptining Service
+2519 44182525 | +251 912461654

ዋጋ 80 ብር